# የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ይዘት ትንተና፣ በተለይ ትግርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ለሆነ ተማሪዎች የተዘጋጀ፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ለድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ ጥናት

ለአማርኛ ማስተማር (TEAM) ኤም.ኤ. ዲግሪ
ማሟያነት የተሰናዳ

በ

ጥላሁን ገ/ክርስቶስ

ታህሳስ፣ 1990

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

# የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ይዘት ትንተና፤ በተለይ ትግርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ለሆነ ተማሪዎች የተዘጋጀ፡፡


በ

ጥላሁን ገ/ክርስቶስ

ቋንቋዎች ጥናት ተቋም


የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

[illegible] (ዶ/ር) ________

አማካሪ

[illegible] (ዶ/ር) ________

ፈታኝ

ገብረመድኅን ስምዖን (ዶ/ር) ________

ፈታኝ

# ም ስ ጋ ና

ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ ሳዘጋጅ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ሳይሰለቹ ረቂቁን በማረም፣ አስተያየት በመስጠትና በማበረታታት ያላሰለሰ ድጋፍ የሰጡኝ አማካሪየ ዶ/ር አረጋ ሀ/ሚካኤልን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ትምህርቱን እንድከታተል የፈቀደልኝ የስርአተ-ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩትን /ትምህርት ሚኒስቴርን/ ማመስገን እሻለሁ፡፡

በትግራይ ክልል የመሀከላይ፣ የምስራቃዊ፣ የደቡባዊና የመቀሌ ዞባ ትምህርት ቢሮ ባለሙያዎች፣ የስምንቱ ትምህርት ቤቶች ያራተኛ ክፍል ያማርኛ ቋንቋ መምህራንና ርሳነ-መምህራን ላደረጉልኝ መልካም ትብብር ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

ዶ/ር ታደለ አዳሙ፣ አቶ ተስፋዬ መንገሻ፣ አቶ አሰፋ በየነና አቶ አንበሱ ቢያዝን ያደረጉልኝ ሙያዊ አስተያየት ለስራዬ መቃናት ረድቶኛል፡፡ ወ/ሮ አዲስዓለም ሀ/ሥላሴ ጥናቱን በኮምፒዩተር በጥንቃቄ ስለተየቡልኝ አመሰግናለሁ፡፡

## ማውጫ


ገፅ

ምስጋና ........................................................................ i

አጠቃሎ ........................................................................ ii

ይዘት ........................................................................ iii

አባሪዎች ........................................................................ iv

የሰንጠረዦች ዝርዝር ........................................................ v

1.0 ዳራዊ ምልከታ

1.1 የጥናቱ አነሳሽ ችግር ከአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ምልከታ አንፃር ........................ 1

1.2 የጥናቱ አላማ ........................................................ 3

1.3 የጥናቱ ፋይዳ ........................................................ 3

1.4 የጥናቱ ክልል ........................................................ 4

1.5 የጥናቱ አደረጃጀት ................................................ 4

1.6 የቃላት፣ የሀረጋትና ምህፃረ-ቃላት ትርጉም........................ 5

2.0 ግምገማ ድርሳናት

2.1 የቋንቋና ትምህርት ትስስሮሽ ........................................ 7

2.2 የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ፋይዳ........................... 10

2.3 የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ........................ 12

3.0 የአጠናን ዘዴ

3.1 የፅሁፍ መጠይቅ

3.1.1 ለኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን ........................ 16

3.1.2 ለትምህርተ-አርታኢያንና ለርሳነ-መምህራን .......... 17

3.2 የመማሪያ-ማስተማሪያ መፃህፍት መገምገሚያ መስፈርቶች ................................................ 17

ገጽ


4.0 የጥናቱ ውጤት ትንተና

4.1 የአራተኛ ክፍል ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ /አማርኛ/ ትምህርት ይዘቶች ግምገማ ........................................ 18

4.2 ካማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ከትምህርተ-አርታኢያንና ከርሳነ-መምህራን የተገኙ መረጃዎች ትንተና..................... 32

5.0 ማጠቃለያና አስተያየት

5.1 ማጠቃለያ ........................................................................ 54

5.2 አስተያየት ...................................................................... 57

መረጃ ዕሁፎች ........................................................................ 59

## አባሪዎች

ገፅ


አንድ፡ ለኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን የተዘጋጀ የፅሁፍ መጠይቅ ........ 62

ሁለት፡ ለትምህርተ-አርታኢያንና ለርሳነ-መምህራን የተዘጋጀ የፅሁፍ መጠይቅ ........ 69

ሦስት፡ አማርኛ፣ አራተኛ ክፍል፣ የተማሪው መፅሀፍ ያካተታቸው ይዘቶችና በመሳሪያነት የቀረቡ ምንባቦች አርእስት ........ 75

አራት፡ የትምህርትን አላማዎች በተለይም የቋንቋን መማር-ማስተማር ፖሊሲ ለመተግበር ትኩረትን የሚሹ ነጥቦች.... 76

አምስት፡ ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው ........ 77

ስድስት፡ የትብብር ደብዳቤዎች ........ 80

# ሰንጠረዦች


ገፅ

1. ያራተኛ ክፍል ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ /አማርኛ/ መምህራን ዳራ ........ 33
2. የትምህርተ-አርታኢያንና የርሳነ-መምህራን ዳራ ........ 34
3. ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋን ለመማር የተማሪዎች ፍላጎት ........ 37
4. ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋን የመማር-ማስተማር አስፈላጊነት ........ 37
5. ላራተኛ ክፍል የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ ........ 38
6. የይዘቶች ቅንብር ........ 39
7. የይዘቶች አደራረስ ........ 40
8. የመልመጃዎች ዝግጅት ........ 41
9. የምሳሌዎችና ስእላዊ መግለጫዎች አቀራረብ ........ 43
10. የቋንቋው መማሪያ-ማስተማሪያ መፅሀፍ የህትመት ጥራት ደረጃ ........ 44
11. የሞክሼ ሆህያት ውስብስብ ችግር ........ 46
12. ንጥረ-ድምፃችን የመለወጥ ችግር ........ 47
13. ንጥረ-ድምፃችን በትክክል አለመጠቀም ........ 47
14. በኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት ውስጥ በዋናነት እንዲካተቱ የተጠቆሙ ይዘቶች ........ 48
15. የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋን ትምህርት ለማጠናከር የቀረቡ አስተያየቶች ........ 50
16. ለኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የተጠቆሙ ይዘቶች በክሂል ደረጃ ........ 52

# አጠቃሎ /Abstract/

በኢትዮጵያ ውስጥ 9,184 የመጀመሪያ እርከን ትምህርት ቤቶች /Elementary Schools/ የሚገኙ ሲሆን፣ የተማሪዎች ቁጥር 2,722,192 ነው። ከዚህ ውስጥ በትግራይ ክልል 627፣ በመቶኛ ሲሰላ 6.8ኛውን የሸፈኑ የመጀመሪያ እርከን ት/ቤቶች ሲገኙ፣ 303,603 ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ ናቸው /MOE. 1996/።

የዚህ ጥናት አላማ በትግራይ ክልል ከሚገኙ የአንደኛ እርከን፣ የመጀመሪያው ንኡስ እርከን /First Cycle/ 222,062 ተማሪዎች ውስጥ ለ49876፣ በመቶኛ ሲሰላ 22.5 ለሸፈኑት ትግርኛ የአፍ መፍቻቸው ለሆነ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀውን የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ /አማርኛ/ ትምህርት ይዘቶች መተንተን ነው። ጥናቱ የተካሄደው በትግራይ በአራት ዞባዎች ውስጥ በስምንት ወረዳዎች በናሙናነት በተመረጡ ስምንት የከተማና የገጠር ትምህርት ቤቶች ነው። በዚህ ጥናት ውስጥ ከስምንት ያማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ከስምንት ትምህርተ-አርታኢያንና (Supervisors) እና ከስምንት ርሳነ-መምህራን ባጠቃላይ ከሀያ አራት የትምህርት ባለሙያዎች ለይዘት ትንተና የሚረዱ አስተያየቶች ተካትተዋል።

ለጥናቱ ያገለገሉ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች ለቋንቋው መምህራን፣ ለትምህርተ-አርታኢያንና ለርሳነ-መምህራን የቀረቡ የፅሁፍ መጠይቆች ናቸው። ከነዚህም በተጨማሪ የመማሪያ-ማስተማሪያ መፃህፍትን መገምገሚያ መስፈርቶች (UNESCO, 1977:76-77) መሰረት በማድረግ፣ የቋንቋው ትምህት ይዘቶች ተገምግሟል። በመጨረሻም፣ ከተዛማጅ ፅሁፎች በተገኙ የጥናት ትወራዎች በመታገዝ የግምገማውን ሀሳብና ከባለሙያዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች በማስተያየት የጥናቱ ውጤት በጥንቃቄ ተተንትኗል።

ከጥናቱ በተገኘው ውጤት መሰረት ለክፍሉ ተማሪዎች የተዘጋጀው የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ /አማርኛ/ ትምህርት ይዘቶች አመራረጥና ቅንብር ብቃት፣የመማሪያ መፅሀፉ አደረጃጀት፣ የትምህርቱ ይዘቶች አደራረስና የቋንቋው ትምህርት አቀራረብ ገፅታ ከተማሪዎቹ የቋንቋ ዕድገት፣ የአእምሮ ብስለትና ስሜት ብሎም ማህበራዊ ዕድገት አኳያ ችግሮች አሉበት።

የስርአተ ትምህርት ዝግጅት የማያቋርጥ ሂደት (dynamic process)ነው። ስለሆነም፣ ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ለክልሉ የቋንቋዎች ትምህርት ሥ/ት/ዝግጅት ክፍል አስተያየቶች ተሰንዝረዋል።

## 1.0 ዳራዊ ምልከታ

### 1.1 የጥናቱ አነሳሽ ችግር ካዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ምልከታ አንፃር

የትምህርት ስርአትን፣ አቅጣጫን፣ አሰጣጥንና አቀባበልን በተመለከተ ኢትዮጵያ ስትከተል እንደነበረው ፍልስፍና በተለያዩ መስመሮች በመጓዝ አያሌ ዘመናት አልፈዋል:: ያገሪቱ የሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅት፣ (መርሀ-ግብሮችና መመሪያዎች) በማዕከል ደረጃ ሲመራ ቆይቷል:: በዚህም የተነሳ ያገራችን ትምህርት አላማዎች፣ የይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀት፣ የመፃህፍት አዘገጃጀት፣ አሰረጫጨትና አተገባበር ከሕዝብ ፍላጐት ጋር ሳይጣጣሙ ዘመናት አልፈዋል:: በትምህርትና በሥልጠና፣ በምርምርና በልማት ተስተጋብሮት /Interaction/ ቅንጅት ማጣት የተነሳ ያገሪቷ እድገት የታሰበውን ያህል ተፋጥኗል ማለት አይቻልም /አጠቃላይ ኢትፖ. መንደርደሪያ ጽሑፍ፣ ጥራዝ አንድ፣ 1985*/:: እነዚህንና የመሳሰሉትን የቆዩ ችግሮች ለማቃለል በአዲስ መልክ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ይፋ ሆኖ፤ የአፈፃፀሙ ሂደት ደረጃ በደረጃ በመከናወን ላይ ይገኛል::

በኢትዮጵያ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ማብራሪያ (1985*) መሰረት፣ የትምህርት አቀራረብ ማለትም የመማሪያ-ማስተማሪያ መሳሪያዎች (መርሀ-ትምህርት፣ የተማሪዎች መፅሀፍ፣ የመምህር መምሪያ፣ መርጃ መሳሪያዎች) ዝግጅት በማዕከልና በክልል ደረጃ ተለይቷል::

የቋንቋን ትምህርት በተመለከተ፣ ኢትፖ(86*:4 - 3.5.8) "የቋንቋ ትምህርቶች በጥራትና በተጠናከረ ሁኔታ እንዲሰጡ ተገቢው ጥረት ይደረጋል፤" በማለት በግልጽ ያመላከተ ሲሆን፣ በተለይ የክልሎች የሥራ ድርሻና ሃላፊነት ባዋጅ ቁጥር 41/85* ተገልጿል:: የጋራ ቋንቋ ምርጫን በተመለከተ፣ አማርኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ መግባቢያ ቋንቋ /Language of Wider Communication/ ሆኖ እንዲቀጥል የዜጎችን ፖለቲካዊና ዲሞክራሲያዊ መብት በሚመለከት ሰኔ 1983* የፀደቀው ቻርተር ያስገነዝባል:: ያገሪቷ ህገ-መንግስትም በአንቀፅ አምስት ስር "አማርኛ የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት የስራ ቋንቋ ይሆናል፤" ሲል፣ "በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረግ ግንኙነት አማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት ይሰጣል" ይላል/ኢትፖ.86* :13-3.5.4/::

· በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ያሉት አመተ-ምህረቶች (*) የሚል ምልክት ካልታከለባቸው በስተቀር በአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር የቀረቡ ናቸው::

ቋንቋና ትምህርትን አስመልክቶ (ኢትፖ.86*፡14) የቀረበው የፖሊሲ ሀሳብ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ከፖሊሲው የትምህርት አተገባበር ስልቶች አንፃር፣ ያገራቱን የትምህርት አላማዎች መሰረት አድርጐ የሚዘጋጀው የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ደረጃውን ጠብቆ ተገቢውን የተማሪዎች የባህርይ ገፅታ /Students Profile/ ማስገኘት ይበጠቅበታል። የመጀመሪያ እርከን (ከ1ኛ - 8ኛ ክፍሎች) ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለሁለተኛው እርከን (ከ9ኛ - 12ኛ ክፍሎች) መሰረት መጣያ ነው። ስለሆነም፣ ለማንኛውም የትምህርት አይነት የሚደረግ የስርአተ-ትምህርት አዘገጃጀት ሂደት (Curriculum Development Process) ጥናት፣ ዝግጅት፣ ሙከራ፣ ውጤተ-ግምገማ፣/feedback/ ማሻሻል፣ ማሰራጨት የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አዘገጃጀትንም የሚመለከት ነው።

የጀማሪዎች የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት /አማርኛ/ ከስርአተ-ትምህርት ዝግድች መርህና ከትምህርት ፖሊሲው ያፈፃፀም መርሀ-ግብር የጊዜ ሰሌዳ አንፃር፣ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ጎን ለጎን ዝግጅት በ1986*፣ ሙከራ 1987* እና ትግበራ 1988* ከሶስተኛ ክፍል ጀምሮ እንደሚሰጥ ይጠቁማል። /Ethiopian Education Polcy: Implementation Strategy Program, 1993/ ።

በትግራይ ክልል አማርኛን በኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋነት ለመማር-ማስተማር የተደረገው ጅምር በመልካም አርአያነቱ ይጠቀሳል። ይሁን እንጂ፣ የመማሪያ መጽሐፉ ከላይ የተዘረዘሩትን መሰረታዊ የትምህርት አዘገጃጀትንና የፖሊሲውን ያፈፃፀም ስልት መርሀ-ግብር ተከትሎ ሳይሆን ክልሉ በ1986* ባዘጋጀው የተማሪው መፅሀፍ የቋንቋው ትምህርት ከአራተኛ ክፍል እንዲጀመር ተደርጓል።

ያንድ ቋንቋ ትምህርት መፅሀፍ ለጀማሪዎች ሲዘጋጅና ሲተገበር ለቋንቋው መማሪያ መሰረት የሆነውን የክፍሉን መርሀ-ትምህርት /Syllabus/ ተከትሎ መደራጀት አለበት። አለበለዚያ በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የተቀረፁት አላማዎችና ግብ ያስመታሉ ተብለው የተመላከቱት ይዘቶች ቅንብር፣ አደራረስና አቀነባበር ችግሮች ሊንፀባረቁ ይችላሉ።

የዚህ ጥናት ትኩረት ከሆነው የአራተኛ ክፍል ያማርኛ ትምህርት ይዘቶች ትንተና አንፃር፣ በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ በየክፍለ-አመቱ /Semester/ ይሸፈናሉ ተብለው የተነደፉትና የተመረጡት አስራ ሰባት አላማዎችና ለግብ ማድረሻ የተመላከቱት ይዘቶች ከመማሪያ መፅሀፉ ጋር በተደረገው ማነፃፀር ሙሉ በሙሉ ተንፀባርቀው አይታዩም። ለክፍል ውስጥ መማር-ማስተማር ከንውን ስኬታማነት ይበጃሉ ተብለው በመርሀ-ትምህርቱ

ውስጥ የተመላከቱትን መርሆዎች /Principles/ ለማለማመድ ዝርዝር ይዘቶች በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ በተሟላ መንገድ አልተካተቱም፡፡ /ዝርዝር ሂሳዊ ግምገማውን የአራተኛ ክፍል ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ /አማርኛ/ ትምህርት ይዘቶች ግምገማ ከገፅ 18 - 32 ይመለከቷል/፡፡

ስለሆነም ችግሮቹን አስወግዶ የተሻለ የአራተኛ ክፍል የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ /አማርኛ/ ትምህርት ይዘቶችን ከአላማዎቹ ጋር በማጣጣም ተገቢነት ባላቸው መልመጃዎች አደራጅቶ የመማሪያ መፅሀፉን ማሻሻል ያሻል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አላማ

ትምህርትን በችግር-ፈቺ መሳሪያነት ተጠቅሞ አንገብጋቢና ማህበራዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት መጣጣር የህዝብን የጋራ ተሳስቦ ይጠይቃል፡፡ አቅም ላጠራቸውና የሙያ ድጋፍን ለሚሹ ክልሎች በየደረጃው በቅንጅት ሙያዊ እገዛ ማድረግ እንደሚገባ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ያበረታታል፡፡

ይህ ጥናት "ያራተኛ ክፍል ያማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መፅሀፍ ይዘት ትንተና፣ በተለይ ትግርኛ የአፍ መፍቻቸው ለሆነ ተማሪዎች የተዘጋጀ" በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን፣ የሚከተሉትን ዓላማዎች ከግብ ያደርሳል፣

- በትግራይ ክልል ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡት ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ከይዘት (አመራረጥ፣ ቅንብር፣ አደራረስ) እና ከአቀራረብ (መልመጃ፣ ምሳሌ፣ ቋንቋ፣ ህትመት) ገፅታ አንፃር ተጣጥመው መዘጋጀታቸውን ይመረምራል፡፡
- የቋንቋው መማሪያ መፅሀፍ ከክፍሉ መርሀ-ትምህርት ጋር ያለውን ተዛማጅነት ይመረምራል፡፡

## 1.3 የጥናቱ ፋይዳ/ጠቀሜታ

ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፣

- ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ /አማርኛ/ ትምህርት ይዘቶች በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ለማወቅ ያስችላል፡፡
- የቋንቋው መማሪያ መፅሀፍ ለክፍሉ ትምህርት መሰረት ነው ተብሎ ከተዘጋጀው መርሀ-ትምህርት ጋር ያለውን ዝምድና ለመገንዘብ ያግዛል፡፡

- ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይበጃሉ ተብለው የታሰቡና በትምህርት ባለሙያዎች የተመላከቱ የፍላጎት ይዘቶችን ለመለየት ይጠቅማል፡፡
- ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ለቋንቋው ትምህርት የተመረጡት ይዘቶች የተገቢነትና ያደረጃጀት ችግር ካለባቸው የመፍትሄ ሀሳቦችን ይጠቁማል፡፡
- በክልል አንድ የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋን በተመለከተ፣ በተለይም ጀማሪ ለሆኑ ተማሪዎች በተዘጋጀው ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ የተደረገ የይዘቶች ጥናት ስለሌለ፣ ያካባቢ ጥናት በመሆን ያገለግላል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ገደብ/ክልል

ከትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ያፈፃፀም ስልት መርሀ-ግብር አንፃር፣ ያማርኛ ትምህርት በኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋነት ይሰጣል፡፡ ጥናቱ የተከናወነው በትግራይ ክልል፣ በአራት ዞባዎች /Zones/ በስምንት ወረዳዎች ውስጥ ለጥናቱ በተመረጡ ስምንት የመጀመሪያ እርከን (1ኛ - 8ኛ ክፍል) ትምህርት ቤቶች ነው፡፡

በመጀመሪያ እርከን ከሚገኙ ክፍሎች ውስጥ አራተኛ ክፍል ለጥናቱ ተመርጧል፡፡ የዚህም ምክንያት ክልሉ የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋን/አማርኛን/ ትምህርት መማር-ማስተማር እንዲጀመር ያደረገበት ክፍል በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም፣ ቋንቋውን ለመማር መሰረት ወይም መነሻ ለሆነው የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡትን ይዘቶች አደረጃጀት መተንተን የጥናቱ ክልል ሆኗል፡፡

በናሙናነት በተመረጡት ት/ቤቶች የሚገኙ ያማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ርሳነ-መምህራንና የየወረዳው ትምህርተ-እርታኢያን /Supervisors/ ባጠቃላይ ሃያ አራት የትምህርት ባለሙያዎች በተጨማሪ በመረጃ ሰጪነት በጥናቱ ውስጥ ተሳትፈዋል፡፡

## 1.5 የጥናቱ አደረጃጀት

የአራተኛ ክፍል ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ /አማርኛ/ ትምህርት ይዘቶች ትንተና በአምስት አበይት ዘርፎችና በንኡሳን ክፍሎች ተደራጅቷል፡፡ የጥናቱ ዳራዊ ምልከታ፣ ግምገማ ድርሳናት፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የጥናቱ ውጤቶች ትንተና ማጠቃለያና አስተያየት የዋናው ጥናት አካል ናቸው፡፡ ከነዚህም ጋር አስፈላጊነት ባላቸው ቦታዎች ሁሉ ጥናቱ ተገቢ በሆኑ ሰንጠረዦች፣ መግለጫዎችና አባሪዎች ተጠናቅሯል፡፡

## 1.6 የቃላትና ሀረጋት ትርጉም

<u>የትምህርት እርከን /Structure/</u>፡ ያገሪቱን የትምህርት አላማዎች ለማሳካት የተቀረፀው ስርአተ-ትምህርት የተከፋፈለበት የ8-4 ደረጃ ነው/ኢ.ት.ፖ. ማብራሪያ 1985* /፡፡

<u>ንኡስ እርከን /Cycle/</u>፡ ከተማሪዎች ያካል ብቃት፣ ያእምሮ ብስለትና የመማር ዝግጁነት አንፃር፣ተገቢ እውቀትን ለመገብየት፣ክሂሎትን ለማዳበርና ዝንባሌን ለመፍጠር እያንዳንዱ እርከን የተከፋፈለበት ዋህድ (Unit) ነው /ኢ.ት.ፖ. ማብራሪያ 1985*/፡፡

<u>የባህርይ ገፅታ/Profile/</u>፡ በየእርከኑና ንኡስ እርከኑ በስርአተ-ትምህርቱ መሰረት-ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎች እንዲኖራቸው የሚጠበቀውን የእውቀት፣የክሂሎትና የዝንባሌ አቅጣጫ የሚያመለክት አሳቤ ነው /ኢ.ት.ፓ. ማብራሪያ 1985* /፡፡

<u>የትምህርት ይዘቶች /Contents/</u> ፡ አእምሮንና ብቃትን በማዳበር ረገድ በተማሪዎች ላይ የበጎ ባህርይን ለውጥ የሚያስገኙ ፋይዳዎች ናቸው /Tyler 1949/፡፡

<u>የማወቅ ባህርያት/Taxonomy of Education/</u>፡ ያንድን ሰው የተሟላ ሰብእና ለማዳበር የትምህርት አላማዎችና ይዘቶች የሚደራጁበት ሳይንሳዊ የትምህርት አደረጃጀት ሲሆን፣ አይነቶቹም የግንዛቤ፣ ያስተሳሰብ ለውጥና ተግባራዊ ባህርያት ናቸው /UNESCO 1977/፡፡

<u>ስነ-ትምህርት /Pedagogy/</u>፡ የትምህርት አላማዎችን አነዳደፍ፣ የይዘቶችን አመራረጥና አደረጃጀት፣ የመማር-ማስተማር ዘዴዎችን/ ስልቶችን፣ መርጃ መሳሪያዎችን፣ የግምገማ ስልቶችን አመራረጥና አጠቃቀም ባጠቃላይ የመማር-ማስተማር ሂደት መጣጣም የሚጠናበት ሳይንስ ነው /Dunkin 1987/፡፡

<u>የመማር-ማስተማር ሂደት /Learning-teaching Process/</u>፡ መማር እውቀትን ማካበት፣ ክሂሎትን ማዳበርና ዝንባሌን ማጎልበት ባጠቃላይ ሰብእናን መገንባት ነው፡፡ ማስተማር ደግሞ ተማሪዎች ለመማር እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ በሂደቱ ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ማቃለልና ተማሪዎችን መምራት ነው /Brown 1995/፡፡

<u>የመማር-ማስተማር ኡደት /Learning-teaching cycle/</u>፡ ቋንቋን በመማር-ማስተማር ሂደት በየእለቱ ጊዜን በመወሰን ሳያቋርጡ የሚደረግ ክንውን /መዘጋጀት፣ መለማመድ፣ መተግበር /መጠቀም ነው /Brewster 1982/፡፡

ዝርዝር ይዘተ-ሰንጠረዥ /Flow-chart/፡ ለመርሀ-ትምህርት ዝግጅት በየደረጃው የሚቀርቡት ይዘቶች በመርህና በልምምድ ደረጃ መለስተኛና ሙሉ ብቃት የሚገኝባቸውን አምዳዊ ግንኙነት (Vertical Relation or Organization) ሂደት የሚያመላክት የስርአተ-ትምህርት ዝግጅት መነሻ ሰነድ ነው /ICDR 1982*/፡፡

መርጃ መሳሪያዎች /Teaching Aids/፡ የመማር-ማስተማርን ሂደት በበለጠ ስኬታማ ለማድረግ እገዛ የሚደርጉ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ መርጃ መሳሪያዎች በሦስት ዘርፎች ይታያሉ፡፡ እነሱም፤ የመማሪያ-ማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች (ቴክኖሎጂ) እና የትምህርት ፋሲሊቲ ናቸው /Ellington and Race 1993/ ፡፡

ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ/Non-Native Language/፡ ከኢትፖ. 86* ማእቀፍ አንፃር፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ መግባበቢያ የሆነውን ቋንቋ (አማርኛ) የሚያመላክት ነው፡፡

መጠነ-ሰፊ ቋንቋ/Language of Wider Communication/፡ የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ማህበረሰቦች ለጋራ ተሳትፎና ጥቅም ለተለያዩ ማህበራዊ ፋይዳዎች ለንግድ ተግባራት ወይም በቋንቋቸው ውስጥ የማይገኙ የቴክኒክና የስነ-ፅሁፍ ስራዎችን ለመረዳት/ለመገንዘብ መሳሪያ የሆነ ቋንቋ ነው/Dubin 1992/፡፡

በአንድ አገር ውስጥ ተሰባጥረው የሚኖሩ ብሄር ብሄረሰቦች በአፍ መፍቻነትም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋነት ለእርስ በርስ ግንኙነት የሚጠቀሙበት ቋንቋ ነው/በብሄረሰብ ቋንቋዎች መደበኛ ትምህርት ለመስጠት የቀረበ ጥናት 1983*/፡፡

ICDR /Institute for Curriculum Development and Research/: የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት፣ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት

MOE / Ministry of Education/: ትምህርት ሚኒስቴር

TEB /Tigrai Education Bureau/: የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

TGE / Transitional Government of Ethiopia/: በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት

UNECA / United Nations Economic Commission for Africa/: በተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ምጣኔ ሀብት ኮሚሲዮን

UNESCO / United Nations Educational, Scientific, and Cultural Organization/: በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት

# 2.0 ግምገማ ድርሳናት

## 2.1 የቋንቋና ትምህርት ትስስሮሽ

የሰው ልጅ በህይወት ገጠመኙ ያዳበራቸውን እውቀቶች፣ ክሂሎች፣ ልምዶች እንዲሁም አዳዲስ ግኝቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፍበት ዘዴ ትምህርት ነው፡፡ የነፃነት፣ የመብትና ግዴታ፣ የማህበራዊ ኑሮ ወዘተ. ትርጉም፣ ግንዛቤና ያሰራር ልምድ በቋንቋ መሳሪያነት ይተላለፋል፡፡ በዚህም ምክንያት የቋንቋና ትምህርት ትስስሮሽ የጠበቀ ነው፡፡ የቋንቋ ጉዳይ ባንድ አገር የትምህርት ፖሊሲ ቀረፃ ውስጥ አንዱ አቢይ ዘርፍ ሆኖ ይገኛል፤

> የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ ያንድ አገር ብሄራዊ
> አላማዎች፣ ማህበረ-ፖለቲካዊ፣ ታሪካዊና ባገሪቷ
> ውስጥ በሚገኙ ቋንቋዎች ሁኔታ መካከል ያለ
> የተስተጋብሮት ውጤት ነው፡፡[1] (McNab, 1989:7)፡፡

ቋንቋና ትምህርት ሲባል የቋንቋን ትምህርትና የመማሪያ ቋንቋን ያመላክታል፡፡ የቋንቋ ትምህርት የቋንቋን ተግባቦተ-ክሂሎት /Communicative skills/ ለማዳበር በትምህርት አይነትነት የሚሰጥ ሲሆን፣ የትምህርት ቋንቋ ደግሞ ትምህርት የሚሰጥበት ቋንቋ ነው፡፡ የመማሪያ ቋንቋን በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎችና መምህራን በእውቀት ማስተላለፊያና መቀበያ (በማዳመጥ፣ በመናገር፣ በማንበብና በመፃፍ) ሳይቸገሩ በስርአት ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

የቋንቋና ትምህርት ትስስሮሽ ጉዳይ በኢትዮጵያ በትምህርት ፖሊሲ ደረጃ በህዝብ ዘንድ በጉልህ አይታወቅም ነበር፡፡ ቢሆንም ካገርኛ ቋንቋዎች ውስጥ አማርኛ ባገሪቷ ውስጥ በቋንቋ ትምህርት አይነትነትና በመማሪያ ቋንቋነት እስከተወሰኑ ደረጃዎች ድረስ ሲያገለግል ቆይቷል፡፡

በሰሜንና በመሃል ኢትዮጵያ ጥንታዊ የቤተ-ክህነት ትምህርት በተስፋፋባቸው ክልሎች ግእዝ የቋንቋ ትምህርትና የመማሪያ ቋንቋ ነበር፡፡ ቀጥሎም ኢትዮጵያ ከሌላው አለም ጋር በተጠናከረ ሁኔታ ግንኙነት በፈጠረችበት ወቅት፣ በሚሲዮናውያን አማካይነት መፅሀፍ ቅዱስና ሌሎች የሃይማኖት መፃህፍት ወደ አማርኛ ተተርጉመው ቀርበዋል፡፡ ከዚያም ባንዳንድ ያገሪቷ አካባቢዎች ትግርኛና ኦሮምኛ እስራ ላይ የዋሉ ሲሆን፣ በሌሎች አገርኛ ቋንቋዎችም ለመጠቀም እቅድና ጥረት ነበር፡፡

ከ1914 እስከ 1935* ድረስ ፈረንሳይኛ በትምህርት አይነትነትና በመማሪያ-ማስተማሪያ ቋንቋነት አገልግሏል፡፡ የቋንቋው ወደ ኢትዮጵያ መግባት ዘመናዊ አስተዳደርን ከመመስረትና በሃያኛው ክፍለ-ዘመን ዘመናዊ ትምህርትን ባገሪቷ ውስጥ ለማስፋፋት ከተደረገ ጥረት ጋር የተያያዘ ነበር፡፡ ዳግማዊ ምኒልክ የመንግሥት ት/ቤቶችን በመሰረቱበት ወቅት በአዲስ አበባና በድሬዳዋ "ኢኮሎፍራንሴ" የተሰኙ ትምህርት ቤቶችን በመደበኛነት ሲከፍቱ፣ በሁለቱም ከተሞች ፈረንሳይኛ በቋንቋ ትምህርት ዓይነትነትና በመማሪያ ቋንቋነት አገልግሏል፡፡ ከመንግስት ጥረት ጎን ለጎንም የተለያዩ የሚሲዮን ድርጅቶች /Lazarists, Catholics, Lutherists/ የሃይማኖት ስርጭት ስራቸውን ለማስፋፋት በፈረንሳይኛ ይጠቀሙ እንደነበር ተመራማሪዎች ይጠቁማሉ፡፡

በፋሽስት ወረራ ዘመናት ተዘግተው የነበሩ ት/ቤቶች ሲከፈቱ የትምህርት አወቃቀርና የት/ቤቶች ግንባታ እንደገና መገንባት ነበረባቸው፡፡ በዚህ መሰረት ከእንግሊዝ መንግስት አንዳንድ የሙያና ያሰራር ድጋፎች ላገራችን ይሰጡ ስለነበር፣የእንግሊዝኛ ቋንቋ ከፍተኛ ጠቀሜታ ታይቷል፡፡ እስከ 1955* መግቢያ ድረስ ቋንቋው በሁሉም ደረጃዎች በትምህርት አይነትና በመማሪያ ቋንቋነት አገልግሏል፡፡ አንዳንድ የውጭ ዜጎችም በግል ት/ቤቶች አረብኛ፣ ግሪክኛና ጣሊያንኛ ቋንቋዎችን ያስተምሩ እንደነበር ተወስቷል፡፡ ቀስ በቀስ ባገራችን በየሙያው ዘርፍ የተሰማራው የሰው ሃይል ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ምክንያት ያማርኛ ቋንቋ እየተጠናከረ ተስፋፋ፡፡ በመንግስት ስራ፣ በንግድና በፋብሪካዎች አካባቢ እንግሊዝኛ የነበረውን ከፍተኛ ስፍራ አጣ፡፡ ስለሆነም፣ ከ1955* ጀምሮ ላንደኛ ደረጃ ትምህርት ከቋንቋ ትምህርትነቱ ጋር አማርኛ የመማሪያ-ማስተማሪያ መሳሪያ ሆነ፡፡ የእንግሊዝኛ ቋንቋም እንደ አንድ የትምህርት አይነት ከሶስተኛ ክፍል ጀምሮ እንዲሰጥ ተደርጓል (Bender 1976, Pankhurst 1950, Gebre Medhin 1981*)፡፡

ካማርኛ ቋንቋ ሌላ ካገርኛ ቋንቋዎች ውስጥ ትግርኛና ኦሮምኛ፣ ካንደኛ ክፍል ጀምሮ እስከ ሶስተኛ ክፍሎች ድረስ በሳምንት ውስጥ ሁለት ክፍለ-ጊዜያት ተሰጥቷቸው አኪያም በአስራ አምስት የብሄር/ብሄረሰብ ቋንቋዎች ትምህርት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ የመማር-ማስተማሩም ሂደት በትምህርት መገናኛ ዘዴዎች በተጠናከረ መንገድ ሲታገዝ እንደነበር ጥናቶች ይጠቁማሉ (የኢትዮጵያ ትምህርት አቅጣጫ መመሪያ፣ 1973*)፡፡

የቋንቋ ትምህርትና የመማሪያ ቋንቋ ችግር ባገሪቷ ውስጥ በየዘመናቱ ለነበሩት መሪዎች ወይም መስተዳድሮች አሳሳቢ ሆኖ መቆየቱ የታወቀ ነው፡፡ ችግሩ ጥላቻን ውስጥ ውስጡን እያስፋፋ፣ ፖለቲካዊ ቅርፅና ይዘት እየተላበሰ ብሄር/ሄረሰባዊ ቅራኔን ለመፍጠር አንዱ ምክንያት ነበር፡፡

ስለ ቋንቋ ትምህርትና የመግሪያ ቋንቋ ሲወሳ፣ ቋንቋን ከመማር-ማስተማር አላማዎች አንፃር ያለውን ማህበራዊ ጠቀሜታ በመጠኑ መዳሰስ ተገቢ ይሆናል፡፡ ምሁራን የቋንቋን ምንነት ሲገልፁ፤ የቋንቋ ቀደምት አላማ ንግግር መሆኑንና የንግግር መሰረቱ ደግሞ ስርአተ-ድምፅ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ የቋንቋ መሰረቱ ስርአተ-ድምፅ ነው ሲባልም በማንኛውም ቁሳዊ ማዕበል (Mechanical Wave) የሚፈጠረውን ድምፅ ሳይሆን፣ በሰው አንደበት ስርአት ባለው መንገድ እየተቀናጀ መልእክት የሚያስተላልፈውን የመግናኛ ሂደት ማለት ነው፡፡

> ቋንቋ በዘፈቀደ በተመሰረቱ ትምህርቶች ላይ
> የተመሰረተ፣ የጋራ ባህል ያላቸውን የማህበረ
> ሰብ አባላት በስምምነትና በስርአት የሚያግባባ
> መሳሪያ ነው[2] (Finocchiaro, 1973:3)፡፡

ከቁሳዊ (Matter) አመለካከትና ከስነ-ማህበረሰብ (Sociology) ጥናት ትንታኔ አንፃር፣ ሰው ከተፈጥሮና ከአካባቢ ጋር ባደረገው የረጅም ዘመናት ተስተጋብሮት ቁሳዊና መንፈሳዊ ገፅታ ያላቸው እሴቶችንና ልምዶችን መስርቷል፡፡ እጅግ የተወሳሰቡ ባህርያት ያላቸው መሳሪያዎችን ሰርቷል፡፡ የማህበረሰብ ኑሮ በትግግዝ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ፣ በቋንቋ መሳሪያነት ራሱ በደነገገው ደንብና መመሪያ እየተመራ ያመርታል፤ ምርቱንም ይከፋፈላል፡፡ ራስን የመቆጣጠር ስርአትን፣ የምርት ስርአትንና የክፍፍል ስርአትን /System of social control, system of production and system of distribution/ ባህሉ አድርጎ ስራንና የቋንቋ ክሂሎቱን አዳብሯል፡፡ በዚህም አካባቢውን በስፋትና በጥልቀት ተገንዝቦ ለመጠቀም ችሏል፡፡ ቋንቋ፣ ትምህርት/ግንዛቤ/ እና ማህበረሰብ የጠበቀ ትስስሮሽ/ቁርኝት ስላላቸው በሂደት አንዱ ሌላውን በማጎልበት ላይ ይገኛል (Engels 1970: 66) ፡፡

> ቋንቋ በሰዎች ወይም በቡድኖች መካከል ትርጉም ላለው
> መግባባት አይነተኛ ቁልፍ ወይም ላለመግባባት እንቅፋት
> ሊሆን ይችላል፡፡ የአነስተኛ ጎሳና የብሄረሰቦች ማንነት
> በሚከበርበትና በታወቀበት ዘመናችን የስነ-ትምህርት ምሁ
> ራን፣ የመንግስት ባለአደራዎችና ምሲዮናውያን ለቋንቋ
> ከፍተኛ ትኩረት ይሰጡታል[3](Grimes, 1992: vi) ፡፡

Marland (1980:51) Hallidey ን በመጥቀስ የቋንቋን ተግባራትና ጠቀሜታ አስመልክቶ የፍላጎት ማሚያ፣ ማህበራዊ ግንኙነትንና አንድነትን መፍጠሪያ፣ ሰብእናን ማዳበሪያና መተንተኛ፣ አካባቢን መመርመሪያና ማወቂያ፣ ሀሳቦችን ወይም ነገሮችን መወከያ ወዘተ. መሆኑን ይገልፃል፡፡ እነዚህ ፋይዳዎች ዛሬ እለት በእለት የሚከናወኑ ጉዳዮችን ብቻ የሚመለከቱ ሳይሆን ለረጅም ዘመናት ሰዎች ሲያከናውኗቸው የቆዩትንም ሁሉ ያጠቃልላሉ፡፡ ስለሆነም፣ ጭብጦቹ ሚዛን ይደፋሉ፡፡

## 2.2 የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ፋይዳ

ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ አንድ ሰው አፉን ከፈታበት ቋንቋ ሌላ በህፃንነት ወይም በጎልማሳነት ዘመን ካካባቢው ወይም መደበኛ ት/ቤት ገብቶ የሚለምደው ወይም የሚማረው ቋንቋ ነው፡፡ የተለያዩ ምሁራን ጥናቶች እንደሚያስረዱት፣ የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ የመጀመሪያ ቋንቋን መሰረታዊ ክሂሎት ላሰረፀ ግለ-ሰብ የሚሰጥ ትምህርት ነው፡፡ ለዚህም የግለሰቡ እድሜ ከአራት አመት በላይና ቋንቋው በሚነገርበት አካባቢ ቢሆን ለመልመድ ወይም ለመማር አጋጣሚው እንደሚያመች ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ የመጀመሪያ ቋንቋ ሙሉ ችሎታ ከተገበየ በኋላ፣ በጎልማሳነት ዘመን ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋን መማር ይቻላል፤

> - - - - ሁለተኛ ቋንቋ የሚለው እሳቤ/ ፅንሰ-ሀሳብ ሁለት ትርጉሞች/ፍችዎች አሉት፡፡ አንደኛ፣የቋንቋን ትምህርት ቅደም ተከተል ያጣቅሳል፡፡ ሁለተኛ ቋንቋ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ በኋላ የተለመደ ወይም የሚለመድ ማንኛውም ቋንቋ ነው፡፡ የተወላጅ ቋንቋ ገና ባልዳበረ በት ወቅት የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የሚከና ወን ይሆናል፡፡በሌላ በኩል፣የመጀመሪያ ቋንቋ እውቀት በጎልማሳነት ዘመን በሚገባ ከተጠናቀቀ በኋላ ወይም በማዛገም ላይ እያለ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሊካሄድ ይችላል፡፡ አለዚያም፣ በእነዚህ በሁለቱ ጊዜያት መካከል ሊካሄድ ይችላል፡፡
>
> ሁለተኛ ደግሞ፣ 'ሁለተኛ ቋንቋ' የሚለው ብሂል የሚያጣቅሰው ከመጀመሪያ ወይም ከነባር ቋንቋ ጋር በተነፃፀረ መልኩ ያለውን የቋንቋ በሳልነት ደረጃ ነው[4](Stern, 1991:12 - 13)፡፡

ቋንቋውና ባህሉ የተከበረለት ብሄረሰብ የሌሎችን ቋንቋና ባህል ለማክበር ዝግጁ ይሆናል፡፡ በዚህ አይነቱ የመከባበርና የመተሳሰብ ግንኙነት ያገርን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ምጣኔያዊ ሀብት በጋራ ለማራመድ አንድ አገር አቀፍ ቋንቋ ያስፈልጋል፡፡ ልሳነ-ብዙነት /Multi-lingualism/ ባለበት አገር ውስጥ ለጋራ መግባቢያና እድገትን ለማፋጠን አንድ አገርኛ ቋንቋ በኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋነት እንዲያገለግል ይደረጋል፡፡ ይህ አገር አቀፍ ቋንቋ ደግሞ የሚመረጠው ከሌሎች ቋንቋዎች በተፈጥሮው ብልጫ አለው በማለት ሳይሆን፣ በተለያዩ ምክንያቶች አንድም በታሪክ ሂደት ወይም በህግ እውቅናን አግኝቶ ወይም በተለያዩ ዘርፎች በሚያሳየው የእድገት ደረጃው ሊሆን ይችላል፡፡

Stern (1991፡16) Paulston ን(1974) እና Marckwarst ን (1963) በማመላከት፣ ሁለተኛ ቋንቋ ባብዛኛው የስራ ቋንቋን ወይም ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ ከሚገኙ ቋንቋዎች መካከል አንድ ታዋቂ ቋንቋን ያመላክታል ይላል፡፡ በአንድ አገር ማህበራዊና ምጣኔያዊ ሀብት ህይወት ውስጥ የተሟላ ተሳትፎ ለማድረግ ወይም ለትምህርት መስጫ ሁለተኛ ቋንቋ ማስፈለጉን ያስገነዝባል፡፡

ከላይ የተንፀባረቁትን መሰረተ-ሀሳቦች የተለያዩ ጥናቶች ያጠናክሩታል፡፡ ከብዙዎቹ ውስጥ፤

> - - - የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ካካባቢያቸው ውጪ በሰፊው ለማይጠቀሙ ማህበረሰቦች መጠነ-ሰፊ የሆነ የወል ቋንቋን መጠቀም አስፈላጊያቸው ነው፡፡ ለእንደ ነዚህ አይነት ማህበረሰቦች የጋራ ቋንቋ የሚያስፈልገው ለንግድ ተግባራት ወይም በቋንቋቸው ውስጥ ለማይገኙ የቴክኒክና የስነ-ፅሁፍ ስራዎችን/ፅሁፎችን ለመረዳት ነው[5] (Dubin, 1992:71)፡፡

የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋን ትምህርት ባገር ውስጥ ያለው ቋንቋውን የመማር-ማስተማር አላማዎችና ያገልግሎት ድርሻ ይወስነዋል፡፡ ስለሆነም፣ ከኢትዮጵያ ማእቀፍ /Context/ አኳያ፣ ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማዎች ተማሪዎች የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎትን በማዳበር ይህንኑ ቋንቋ ከሚማሩ ብሄር/ ብሄረሰቦች ጋር ለጋራ ምጣኔያዊና ማህበራዊ ተሳስቦ እንዲገለገሉበት ነው፡፡

ተማሪዎች ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋን ሲማሩ የጠበበ ሁኔታና ብዙ ተፅእኖዎች ስለሚያጋጥማቸው ጥንካሬ ያሻቸዋል፤ መምህራንም የተማሪዎችን ችግር ለማቃለል ብርቱ ዝግጅትና ስራ ይጠብቃቸዋል፡፡ እንደ Finocchairo (1973፡ 12-13) አቀራረብ፣ ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋን በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ከሚከሰቱ አንዳንድ አሉታዊ ጎኖች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፡፡

- ከማህበራዊ ስነ-ልሳን አንፃር፣ ያንድ ብሄር/ ብሄረሰብ ቋንቋ ልማድ ወይም ባህል ካንድ አዲስ ቋንቋ ትምህርት ጋር ግጭትን ወይም ጣልቃ ገብነትን ያስከትላል፡፡
- ተማሪዎች ለአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ያላቸው የኩሩነት መንፈስና ለባህላቸው ያላቸው ከፍተኛ ግምት ሌላ ቋንቋንና ባህልን ሲማሩ የራሳቸውን የሚያጡ እየመሰላቸው/በራስ አለመተማመን/ሀሳባቸው ካዲሱ የቋንቋ ትምህርት ጋር ሊጋጭ ይችላል፡፡
- ከራስ ቋንቋ ሌላ ያዲስ ቋንቋ ትምህርት ሲካሄድ፣ የተማሪዎች ዝንባሌ፣ የእውቀታቸው መነሻ፣ በቋንቋው ያላቸው ችሎታ፣ የመምህሩ ስነቦናዊ፣ ስነ-ልሳናዊ እውቀትና ልምድ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡
- አዲሱን ቋንቋ በመማር ሂደት በቃላት፣ በትርጉም፣ በተመሳሳይ ቃላት ወዘተ. መካከል ያለው ግንኙነት በቀላሉ የሚጨበጥ አይሆንም፡፡
- ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋን የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ላይ የሚኖራቸው ዝንባሌ ግምት ይሰጠዋል፡፡

- ከትምህርት ቤት ውጭ ተማሪዎች ኢ-እፍ መፍቻ ቋንቋን ለመጠቀምና ለማዘውተር ያላቸው አጋጣሚ ግንዛቤ ውስጥ የሚገባ ነው፡፡

እነዚህና የመሳሰሉት ዝርዝር ችግሮች ኢ-እፍ መፍቻ ቋንቋን ከመማር-ማስተማር ያግዳሉ ማለት አይደለም፡፡ ዳሩ ግን በተቻለ መጠን እነዚህን ጎታች ሁኔታዎች አስወግዶ ተማሪዎች ቋንቋውን እንዳስፈላጊነቱ እንዲጠቀሙብት ማድረግ ያሻል፡፡ የኢ-እፍ መፍቻ ቋንቋን መማር-ማስተማር ሂደት ስኬታማ ለማድረግ ስነ-ትምህርታዊ፣ ስነ-ልሳናዊና ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንደሚገባ Lado (1964) እና Patrcie (1992) እንደሚከተለው ይጠቁማሉ፤

- በእለት ከለት ነባራዊ ኑሮ ውስጥ ጠቀሜታ ባላቸው ዘወትሯዊ ቃላት፣ ሀረጋት፣ አባባሎች ወዘተ. ላይ ትኩረት በማድረግ ያጠቃቀማቸውን ስልት ማጤን፣
- የቋንቋውን ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ከተማሪዎች ፍላጎትና ችሎታ ጋር ማዋሃድ፣
- የቋንቋውን ትምህርት በደንቦች ላይ ሳይሆን በተግባራዊ ሂደት ስልት ላይ በማትኮር የሚጠበቀውን የተማሪዎች ችሎታ ማጎልበት፣
- ልዩ ልዩ መልመጃዎችን በመስራት የቋንቋውን ትምህርት ማዳበር፣
- በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙቶች ወቅት /በስራ ስፍራ፣ በመዝናኛ ቦታ፣ በስብሰባ አካባቢ/ ወዘተ. ለመጠቀም ጥረት ማድረግ ውጤት ያስገኛል፡፡

## 2.3 የኢ-እፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች

የቋንቋ ትምህርት አላማዎችና ይዘቶች ሲመረጡና ሲደራጁ ከሰው ልጅ የማወቅ ባህርያት አይነቶች /Taxonomy of Education/ ማለትም ከግንዛቤ ባህርይ (Cognitive domain)፣ ካስተሳሰብ ለውጥ ባህርይ(Affective domain) እና ከተግባራዊ ባህርይ (Psycho motor domain) አንፃር ሚዛናዊነታቸውን ጠብቀው መዘጋጀት አለባቸው፡፡

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከአላማዎች ቀጥሎ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች የትምህርቱን አላማዎች ግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ይዘቶችንና ክንውኖችን መምረጥና ማደራጀት ነው፡፡ ይዘቶች አጠቃላይ አላማዎችን /aims/፣ ግቦችን /goals/ እና ባህርያዊ አላማዎችን /objectives/ ለማሟላት እንዲያስችሉ የሚመረጡ የእውቀት፣ የክሂሎትና ያመለካከት ጥንቅሮች ናቸው፡፡ የትምህርት ክንውኖች ደግሞ ተማሪዎች ይዘቶችን ከውጫዊ ሁኔታዎች ጋር ለማጣጣም የሚያደርጉትን ግንኙነት ወይም ተስተጋብሮት ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል የትምህርት ክንውኖች ተማሪዎች ይዘቶችን ለመማር እውቀትን በአእምሯቸው ውስጥ የሚያብሰለስሉትን ሂደት ነው፡፡ ይዘቶችንና ክንውኖችን የመምረጥ ፋይዳ ተስማሚ የሆኑትን ብቻ ለይቶ በመማርያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ለማንፀባረቅ ነው (UNESCO 1977: 42 - 44, UNECA 1985: 17 - 22, UNECA 1993: 22 - 25)፡፡

የትምህርት ይዘቶችን ከስነ-ትምህርት መርህና ከመማር-ማስተማር አመቺነት አንፃር መርጦ ወይም ለይቶ ስለ ማደራጀት ብዙዎቹ ባለሙያዎች ተመሳሳይ ሀሳቦችን ያመላክታሉ፡፡ UNESCO (1977፡ 67-69), Krashen (1989፡ 26), Dubin (1992፡ 45-48), ይዘቶች ከትምህርት አላማዎች ጋር ያላቸው ተገቢነት፣ የተማሪዎችን ፍላጎት የማሟላት ሁኔታ፣ መጣኝነት፣ ወቅታዊነት፣ ከካባቢያዊ ሁኔታ ጋር ያላቸው ተዛምዶ፣ ተለጣጣቂነት፣ መዋቅራዊ አደረጃጀት ወዘተ. ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ይጠቁማሉ፡፡

ባንድ አገር የትምህርት ሂደት ውስጥ በተለይ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ከባህልና ከህዝብ ምኞት፣ ከመማሪያ መፃህፍት ዝግጅትና አቅርቦት እንዲሁም ከመማር-ማስተማር ዘዴ ጋር ያለውን ስምምነት የሚያራምድ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ የዲሞክራሲ ባህልንና የእርቅ ማየትን/ ማስተዋልን ዝንባሌ ማጠናከር ከትምህርቱ ይዘቶች የሚጠበቅ ነው፡፡ ስለሆነም ስርአተ-ትምህርቱ ከማህበረ-ፖለቲካ፣ ከማህበረ-ምጣኔ ሀብትና ከማህበረ-ባህል አቅጣጫ ዝንባሌው ሊጎለብት ይገባል (UNECA 1995 : 9)፡፡

የትምህርት ይዘቶችን አስመልክቶ ከበርካታ የቋንቋ ምሁራን ጥናቶች ውስጥ የሚከተለው ሀሳብ ይጠቀሳል፤

> - - - - የተማሪዎችን ፍላጎት ባማከለ የትምህርት ስርአት ውስጥ ይዘት መመንጨት /መውጣት ያለበት ከተማሪዎች /ከማህበረሰብ ጋር በመመካከርና የስምምነት ድርድር ከማድረግ ሂደት ነው[6] (Nunan, 1988:55)፡፡

የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋን በመማር-ማስተማር ሂደት የይዘቶችን አቀራረብ ለማመቻቸት ትኩረት ያሻል፡፡ ለጀማሪ ክፍል የሚቀርቡ ይዘቶች ሰፋ ያለ ጠቀሜታ በመስጠት የሚከናወኑ ሲሆኑ ይገባል፡፡ ለዚህም ለውይይትና ለጭውውት የሚጋብዙ ይዘቶች ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እነዚህን መሰረታዊ ወይም አግባብነት ያላቸው ይዘቶች በተጨባጭ መልክ በአካል እንቅስቃሴና በስዕሎች አጋዥነት አስተማሪውም ሆነ የክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቧቸው ያስፈልጋል፡፡ በዚህ አይነት ክንውን በቋንቋው መምህር መሪነትና በተማሪዎች ከፍተኛ ተሳትፎ ይዘቶችን ስፋት እንዲኖራቸው ማድረግ እንደሚቻል Krashen (1989፡26) Asherን (1982) በመጥቀስ ያስገነዝቧል፡፡

ለአ-አፍ መፍቻ ቋንቋ /Language of Wider Communication/ ትምህርት መርሀ-ግብር ስኬታማነት በቅድሚያ ጥናት ያሻል፡፡ የፍላጎት እሰሳን ማካሄድ ለትምህርቱ አዘጋጅ ክፍል ተጨባጭ እውነታዎችን ለማመላከት ይረዳል፤ ቋንቋውን ለመማር-ማስተማር ተገቢ ይዘቶችንና ዘዴዎችን ለመጠቀም ያግዛል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት መደረግ እንዳለበት ብዙ ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡

መሰረታዊ የትምህርት ሰነዶችን ከመመርመር ባሻገር፤

ሀ - አጠቃላዩን ስርአተ-ትምህርት፣

ለ - በስራ ላይ ያሉትን የመማሪያ-ማስተማሪያ መፃህፍት፣

ሐ - ስነ-ዘዴዎችን፣

መ - የመምህራን ስልጠና መርሀ-ግብሮችን፤ የስራ ላይ ስልጠናንና ቅድመ-ቅበላን፣

ሠ - የመምህራንን፣ የተማሪዎችንና የወላጆችን አስተሳሰብ ማጥናትና ማወቅ ይገባል[7] (Dubin, 1992: 11)

የአ-አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ በጥንቃቄ ተመርጠው የተደራጁ ይዘቶችን አካትቶ ለማግባቢያዊ ቁምነገሮች ትኩረት በመስጠት በመግባቢያዊ ተግባራት (Communitive activities) በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ ተማሪዎችን የሚያለማምድ ቢሆን ይመረጣል፡፡ አለበለዚያ ቋንቋውን ለመማር-ማስተማር የተዘጋጀው መጽሐፍ ለተማሪዎች ዕውቀትን ያስጨብጣል፤ ክሂሎትን ያዳብራል፤ ጽኑና ጠንካራ ባህርይን ለማጉልበት መሣሪያ ይሆናል ማለት ያስቸግራል፡፡

የቋንቋን ትምህርት መርሃ-ትምህርትና የመማሪያ መጽሐፍ የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ዋና ጭንቀታቸው ይኸው የይዘቶች መረጣና አደረጃጀት ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተማሪዎች ቋንቋውን እንዴት ይማሩ? ለሚለው ሀሳብ አዘጋጆቹ በሚጠቁሟቸው ስልቶች በመታገዝ በተግባር ለመግለፅ ጥረት የሚያደርጉት መምህራን ድካማቸውና ትኩረታቸው ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ይህንን አስመልክቶ፣ ከምሁራን ጥናቶች ውስጥ Celce - Murcia (1979) የአ-አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፍ የተማሪዎችን ፍላጐት ከሚያመላክቱ ይዘቶች ጋር ቢዛመድ ተማሪዎች በሚገባ ተጠቅመውበት በቋንቋው ትምህርት የተሻለ ውጤትን ለማግኘት እንደሚችሉ በአንክሮ ታስገነዝባለች፡፡

## 3.0 የአጠናን ዘዴ

የጥናቱ ትኩረት ትግርኛ የአፍ መፍቻቸው ለሆነ ተማሪዎች የተዘጋጀውን ያራተኛ ክፍል ያማርኛ ቋንቋ መማሪያ ይዘቶች መተንተን ነው፡፡ ለዚህም ጥናቱ የተከተለው ገላጭ የምርምር ዘዴን ሲሆን ያሰራሩ ስልት፣

- በስራ ላይ የሚገኘውን የክፍሉን ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ከመርሀ-ትምህርቱ ጋር ተጣጥመው መደራጀታቸውንና ተገቢነታቸውን መመርመር/መገምገም፣
- የክፍሉን ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን፣ የትምህርተ-አርታኢያንንና የርዕሳነ-መምህራንን የፍላጐት ይዘቶች ማሰባሰብ፣
- ከተዛማጅ ፅሁፎች በተገኙ የጥናት ትወራዎች በመታገዝ ከመስክ የተገኙ መረጃዎችን በየፈርጃቸው በማደራጀት መተንተን እና
- በትምህርት ባለሙያዎቹ የተጠቆሙ ይዘቶችን በከሂል ደረጃ ፈርጆ ማቅረብ ነው፡፡

ላንድ የጥናትና ምርምር ስራ ስኬታማነት ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ትክክለኛነትና ብቃት ያላቸው የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎችን ማዘጋጀትና በስራ ላይ ማዋል ነው፡፡ ስለሆነም፣

ሀ - ለክፍሉ የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን፣ በየወረዳው በሚገኙ ትምህርተ-አርታኢያንና በየትምህርት ቤቱ ርሳነ-መምህራን የሚሞሉትን የፅሑፍ መጠይቆች /መሳሪያዎች/ ለዋናው ጥናት ስራ ላይ ከመዋላቸው በፊት፣ ለመጀመሪያው ቅኝት ስራ (Seminar i) የተዘጋጁትን መጠይቆች ከሁለተኛው ትምህርታዊ ጉባኤ (Seminar - ii) ተሳታፊ መምህራን፣ ከአማካሪዬና ከጥናትና ምርምር ባለሙያዎች በተገኙ ገንቢ ሀሳቦች በማሻሻል ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡

ለ - የፅሁፍ መጠይቆቹ በመስክ ስራ ላይ ከመዋላቸው በፊት፣

- ጥያቄዎቹ የተለያዩ ቀለሞች ባላቸው ወረቀቶች የመጀመሪያ ገፅ ላይ ብቻ እንዲተየቡ ተደርጓል፡፡
- መጠይቆቹ በበቂ ቁጥር ከመጠባበቂያ ጋር ተባዝተዋል፡፡
- መጠይቆቹን ለሚሞሉ መላሾች የጥናቱን አላማ በሚገባ ተገንዝበው ትክክለኛ መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

ሐ - በየደረጃው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮ. ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍል ጀምሮ የትብብር ደብዳቤ በማፃፍ ከክልሉ ዞባዎች የትምህርት ቢሮ በተዋረድ ለወረዳዎች ት/ቢሮ የትብብር ደብዳቤ ቀርቧል፡፡

መ - የመረጃ አሰባሰቡ ስልተ-ትግበራ በሚከተለው ሂደት ተተግብሯል፤

- የመረጃ ማሳሰቢያ መጠይቆቹን አላማና ፋይዳ ለክፍሉ የቋንቋው መምህራን፣ ለየወረዳው ትምህርተ-አርታኢያንና ለየትምህርት ቤቱ ርዕሰ-መምህራን የቋንቋውን መማሪያ-ማስተማሪያ መፅሀፍ ይዘቶች በጥንቃቄ ገምግመው ገንቢ ሂስ መስጠት እንደሚጠበቅባቸው ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡
- ለጥናቱ አስተያየት ሰጭዎች (ለቋንቋው መምህራን፣ ለትምህርተ-አርታኢያንና ለርዕሰ-መምህራን) ለግንዛቤ ያህል ስለ ትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ በተለይም ቋንቋና ትምህርትን አስመልክቶ መጠነኛ ገለፃ ተደርጓል፡፡
- ከየወረዳው በትምህርተ-አርታኢያን አጋዥነት /ተባባሪነት/ የዚህ ጥናት አቅራቢ በግንባር በመገኘት ባለሙያዎቹ የፅሁፍ መጠይቆቹን በጥንቃቄ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡
- የፅሁፍ መጠይቆቹን በገጠር ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የቋንቋውን መምህራንና ርዕሰ-መምህራን ለማስሞላት መጠነኛ የእግር ጉዞ በማድረግ ለማከናወን ተችሏል፡፡

## 3.1 የፅሁፍ መጠይቅ

### 3.1.1 ለኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን የተዘጋጀ የፅሁፍ መጠይቅ /መሳ.01/

መመሪያ፤ ይህ ቋንቋውን በሚያስተምሩ መምህራን የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ በሶስት ክፍሎች የተዘጋጀ ነው፡፡

ክፍል አንድ፣ ስለ መምህሩ/ሯ አጠቃላይ መረጃን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን፣

ክፍል ሁለት፣ ስለ አራተኛ ክፍል ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት (የይዘቶችን አመራረጥ፣ ቅንብርና አደራረስ) ከአቀራረብ አንፃር (የመልመጃዎችን፣ ምሳሌዎችንና ስእላዊ መግለጫዎችን፣ ቋንቋን እና የህትመትን ጥራት) የሚመለከቱ ጥያቄዎችን፣

ክፍል ሶስት ደግሞ፣ የቋንቋው መምህራን ከሙያቸውና ከልምዳቸው ብሎም ከማህበረሰቡ ፍላጎት አኳያ ላማርኛ ትምህርት በዝግጅቱ ውስጥ በዋናነት እንዲካተቱ የሚጠቆሙ ይዘቶችን የሚመለከቱ ባጠቃላይ ሃያ ዘጠኝ ዝግና አራት ክፍት ጥያቄዎችን አካትቷል፡፡

### 3.1.2 ለትምህርት ባለሙያዎች /ትምህርተ-እርታኢያንና ለርሳነ-መምህራን የተዘጋጀ የፅሁፍ መጠይቅ /መሳ.02/

መመሪያ፣ ይህ የፅሁፍ መጠይቅ በሶስት ክፍሎች የተዘጋጀ ነው፡፡ ክፍል አንድ፣ ስለ ርእሰ-መምህሩ/ሯ ወይም ትምህርተ-እርታእይ አጠቃላይ መረጃን፣ ክፍል ሁለት፣ ያራተኛ ክፍል ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን በተመለከተ መረጃን እና ክፍል ሶስት፣ የትምህርት ባለሙያዎቹ ለኢ-እፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የሚያመላክቷቸውን ይዘቶች በተመለከተ ባጠቃላይ ሃያ አንድ ዝግና አራት ክፍት ጥያቄዎችን አቅፏል፡፡

## 3.2 የመማሪያ-ማስተማሪያ መፃህፍት መገምገሚያ መስፈርቶች

የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፍትን አገማገም በተመለከተ፣ በርከት ያሉ ምሁራን በመስፈርትነት ሊያገለግሉ የሚችሉ ነጥቦችን (Possible evaluation criteria) ይጠቁማሉ፡፡ ከነዚህ መሠረታዊ ባህርያት ውስጥ፤ የዝግጅቱ ትክክለኛነት፣ ተስማሚነት፣ ተገቢነት፣ አስደሳችነት፣ አበረታታችነት፣ ተነባቢነት፣ የመግለጫዎች ተመጣጣኝነት በአጠቃላይ የይዘትና የአቀራረብ ገፅታን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የብዙዎቹ ጥናቶች የጋራ መግለጫዎች ናቸው፡፡ Jon (1992), Dubin (1992), Murphy (1989), Stidisho (1987), Strevens (1983), UNESCO (1977), Ergese (1986), ICDR, CEERC (1997).

የ UNESCO(1977 :76 - 77) ጥናት ከላይ የተዘረዘሩትን ሀሳቦች የሚያካትት በመሆኑ፣ በሥርዓተ ትምህርት አዘገጃጀት ሂደት እስከአሁን የምንጠቀምበት ሞዴል ስለሆነና ለብዙ ጥናቶች መሠረት ስለሆነ ለዚህ ጥናትም በተጨባጭ ጠቀሜታ ያላቸውን የመገምገሚያ መስፈርቶች በመምረጥ ለመጠቀም ተችሏል፡፡ ስለሆነም፣ ከትምህርት ሰጪነት ባህሪያት (Instructional Characteristics) ስምንት እና ከተግባራዊነት ባህሪያት (Practical Characteristics) አራት በጠቅላላ አስራሁለት መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ የቋንቋውን ትምህርት ይዘቶች ለመገምገም ተችሏል፡፡

መረጃ አተናተንን በተመለከተ፣ ጥቅል መረጃዎች ከላይ በተመለከቱት ሁለት የፅሁፍ መጠይቆችና በመማሪያ-ማስተማሪያ መፃህፍት መገምገሚያ መስፈርቶች አማካይነት ተሰብስበዋል፡፡ ቀጥሎም፣ መረጃዎች በየመልካቸው ተለይተው ተደራጅተዋል፡፡ በመጨረሻም፣ መረጃዎችን በግልፅ ለማሳየት እንዲቻል አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ቦታ ሁሉ ሰንጠረዦችንና ስሌቶችን በቁጥር፣ በመቶኛ በማስላት ብሎም የተመጣጣኝነትን የደረጃ ነጥብ በመለየት በጥንቃቄ መተንተን ተችሏል፡፡

## 4.0 የጥናቱ ውጤት ትንተና

### 4.1 የአራተኛ ክፍል የኢ-እፍ መፍቻ ቋንቋ /አማርኛ/ ትምህርት ይዘቶች ግምገማ

ስለቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ትንተና፣ ሲወሳ መሰረት የሆነውን የስርአተ-ትምህርት ምንነት በመጠኑ መዳሰስ አግባብነት ይኖረዋል፡፡

የትምህርትን ሂደት የሚመራው ስርአተ-ትምህርት መሆኑ ከታወቀ በኋላ፣ በተለያዩ ዘመናት ምሁራን ለስርአተ-ትምህርት የተለያየ ትርጉምንና ትንታኔን ሲሰጡት ቆይተዋል፡፡ ባለፉት አያሌ ዘመናት ውስጥ ለስርአተ-ትምህርት ይሰጠው የነበረ ፍች በጣም የጠበበ በመሆኑ፣ ተማሪዎች ምን መማር አለባቸው? የትምህርቱ አላማ ምንድን ነው? ትምህርቱ እንዴት ይዳረስ ? ወዘተ. ለሚሉና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መልሶችን መስጠት ችግር አይፈጥርም ነበር፡፡ ዳሩ ግን፣ የምርት ኃይሎች እየዳበሩ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት እየተሻሻለና የሰው ልጅ ፍላጎት በይበልጥ እየጎለበተ ሲመጣ፣ የስርአተ-ትምህርት ጽንሰ-ሃሣብም በዚያው መጠን እየሰፋ አዘገጃጀቱ እየዳበረ መሄድ ጀመረ፡፡ ስለሆነም፣ መሠረታዊ ጭብጦችን፣ መርሆዎችንና ትወራዎችን እያካተተ እየንዳንዱ አገር እንደሚከተለው ፍልስፍና፣ የፖለቲካና የመንግስት አመራር ትምህርት ነክ መንግስታዊ ሰነድ እስከ መሆን ደርሷል፡፡

አንዳንድ አገሮች ስርአተ-ትምህርትን እንደ መርሀ-ትምህርት፣ መርሀ-ትምህርትን ደግሞ እንደ ስርአተ-ትምህርት ይወስዱታል፡፡ ለምሣሌ፣ በእንግሊዝ ስርአተ-ትምህርት አንድ አገር ለእድገት አቅጣጫ አድርጎ የመረጠው፣ የትምህርት ስርአትን ማሳደግ ይችላል ተብሎ የታመነበትና ባቅጣጫ ጠቋሚነት ወይም ፋና ወጊነት የሚያገለግል ዝግጅት ነው፡፡ መርሀ-ትምህርት ደግሞ ያንድ ትምህርት አይነት ይዘት ነው የሚል አስተሳሰብ አለ፡፡

> 'ስርአተ-ትምህርት' ሲባል የታቀደና ለተማሪዎች
> የሚሰጥ ጥቅል የትምህርት ይዘት ሁሉ ነው፡፡
> 'መርሀ-ትምህርት' ሲባል ደግሞ የአንድ ትምህርት
> አጭር ንድፍ/ ረቂቅ ነው[8]/UNESCO, 1978: 12/፡፡

ያም ሆነ ይህ፣ ስርአተ-ትምህርት ያንድን አገር ችግሮችና ማህበራዊ ፍላጎቶች ባገናዘብ የትምህርት ፖሊሲ ላይ ተመስርቶ፣ ማህበራዊ ፋይዳ ያለው እውቀትን /ግንዛቤን፣ ክሂሎትንና ዝንባሌን ያቀፈ የትምህርት መርሀ-ግብር ነው/ ኢትፓ. ማብራሪያ፣ 1985*/፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት መሰረታዊ ጭብጦች አንፃር፣ የማንኛውም ትምህርት አይነት የመማሪያ-ማስተማሪያ መሳሪያዎች (መርሀ-ትምህርት፣ የተማሪው መፅሀፍ፣ የመምሁሩ መምሪያ፣ መርጃ መሳሪያዎች) ያንድ ስርአተ-ትምህርት ዝግጅት ዋና ውጤቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም፣ የቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መፃህፍት ዝግጅት ወይም የማሻሻል ስራ የተለያዩ ባለሙያዎችን ተሳትፎ ይጠይቃል፤ ምክንያቱም ቋንቋን ለመማር-ማስተማር በጣም የሚተኮርበት የማነቃቂያ ምንጭ የቋንቋው ሙያዊ ተፈላጊነት ብቻ አይደለም፡፡ ቋንቋውን ለመማር-ማስተማር የየደረጃው መፅሀፍ ዝግጅትና ትምህርታዊ አቀራረብ ጭምርም እንጂ፡፡

የቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ከመቀስቀስ አንፃር በጥንቃቄ መደራጀት እንደሚያሻው Rubangumya (1990) Muzeን (1978) ዋቢ በማድረግ እንደሚከተለው ያጠናክሯል፤

> - - - - ተማሪዎችን በቋንቋ ትምህርት ለማነቃቃት ሲባል፣ አንድን ነገር ለመማር፣ ለማድረግ፣ ሀሳባቸውን፣ ስሜታቸውን፣እውቀታቸውንና አስተያየታቸውን ለመግለፅ እንዲችሉ፣ የቋንቋው መማሪያ መፅሀፍ ልጆቻችንን ከማህበራዊነትና ከእውቀት ሰጪነት አንፃር ሁኔታዎችን የሚያስረዳ መሆን አለበት[9]/Rubangumya, 1990:66/፡፡

እነዚህን መሰረታዊ ሀሳቦች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ የጥናትና ሂሳዊ ግምገማ አማካይ መስፈርቶችን /UNESCO 1977: 76 - 77/ በመከተል፣ ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀውን የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ /አማርኛ/ ትምህርት ይዘቶች መገምገም ተችሏል፡፡

ሀ - የትምህርት ሰጪነት ባህርያት (Instructional Characteristics)፤

ሀ.1 የይዘቶች ከትምህርት አላማዎች ጋር መዛመድ (Contents related to instructional objectives)፣

ሀ.2 የይዘቶች ጠቃሚነትና አስተማማኝነት (Contents valid and reliable)፣

ሀ.3 የይዘቶች በተጠይቃዊ መንገድ/ በነገረ-ጥበብ በስርአት መደራጀት (Contents logically organized)፣

ሀ.4 ይዘቶች ለስነ-ልቦና ያላቸው ተገቢነት፤ ከመማር መርሆዎችና ከተማሪዎች የብስለት ደረጃዎች ጋር ያላቸው የተመጣጣኝነት፣ የመሳብና የማነቃቃት ሁኔታ (Contents psychologically relevant:: Conformity to the principles of learning and developmental stages of pupils interesting, and self-motivating)፣

ሀ.5 የቋንቋ አጠቃቀም፣ ትክክለኛነትና ተስማሚነት (Accuracy and suitability of language used)፣

ሀ.6 የስእላዊ መግለጫዎች ተስማሚነትና ተመጣጣኝነት (Suitable and appropriate illustrations)፣

ሀ.7 የመማር ልምዶች በሚገባ ተከታታይ መሆን (Appropriately sequenced learning tasks)፣

ሀ.8 ሁለ-ገብ የስሜት ህዋሳትን ለማነቃቃት የሚያስችል የመልመጃዎች አቀራረብ (Providing preferably multisensory. Simulation approach)፣

ለ - የተግባራዊነት ባህርያት (Practical characteristics) የመማሪያ መፅሀፉ አጠቃላይ ማራኪነት(Layout and Attractiveness )፤

ለ.1 ተገቢ የቀለም አጠቃቀም፣ የወጥነት ጥራት (Proper use of colour, quality of finish)፣

ለ.2 ላጠቃቀም ያለው አመቺነት (Easiness to use)፣

ለ.3 ዘላቂነት (Durability) ፣

ለ.4 በቂ መመሪያ፣ ለተማሪዎችና ለመምህራን (Adequate guide: instructions to students and teachers)፣

የአራተኛ ክፍል ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ /አማርኛ/ ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ግምገማ በአጥኚው እይታ፤

ሀ - የቋንቋው መማሪያ መፅሀፍ የትምህርት ሰጪነት ባህርያት፤

በትግራይ ክልል አማርኛን በኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋነት ለመማር-ማስተማር ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበው መፅሀፍ በሃምሳ አራት ገፅ የተደራጀ ነው፡፡ ይህ በትግራይ ትምህርት ቢሮ የስርአተ-ትምህርት ዝግጅት ጥናትምና ምርምር መምሪያ የተዘጋጀው የመማሪያ መፅሀፍ ከ1986* ጀምሮ ስራ ላይ ውሏል፡፡

በቋንቋው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች ለክፍሉ ተዘጋጀው መርሀ-ትምህርት ውስጥ ከተነደፉት አላማዎችና በክፍል ውስጥ መማር-ማስተማር ከንውን ስኬታማነት ይበጃሉ ከተባሉት መርሆዎች ጋር ምን ያህል ተዛምዶ እንዳላቸው መገምገም የዚህ ጥናት ቀዳሚ ተግባር ሆኗል፡፡

ላማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የተቀረፁ ዝርዝር አላማዎችና የይዘቶች አቀራረብ፡

| አንደኛ የትምህርት ክፍለ-አመት (First Semester) | | ሁለተኛ የትምህርት ክፍለ-አመት (Second Semester) | |
|---|---|---|---|
| አላማ | ይዘት | አላማ | ይዘት |
| 1. ስርአተ-ድምፆችን፣ቃላትንና አረፍተ-ነገሮችን አዳምጠው ይረዳሉ፡፡ | - ስርአተ-ድምፆች፣ ቃላትና አረፍተ ነገሮች፡፡ | 7. ያዳመጡትንና የተመለከቱትን ሀሳብ በቃል ይገልፃሉ፡፡ | - የተለያዩ ሀሳቦችን አዳምጦና ተመልክቶ በቃል መግለጽ፡፡ |
| 2. በማዳመጥ፣ በማየትና በክንውን የተገኘ ሀሳብን በንግግር ይገልፃሉ፡፡ | - በማዳመጥ፣በማየትና በክንውን የተገኘ ሀሳብን በንግግር መግለፅ፡፡ | 8. የቀለም አይነቶች ይለያሉ፡፡ | - የቀለም አይነቶች፡፡ |
| 3. ሰላምታ ይለዋወጣሉ፡፡ | - ሰላምታ መለዋወጥ፡፡ | 9. የተመለከቷቸውን ቁሳቁሶች መጠን ይቆጥራሉ፡፡ | - የልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን ብዛት መቁጠር፡፡ |
| 4.የሆሄያትን ድምፅና ቅርፅ ይለያሉ፡፡ | - የሆሄያት ድምፅና ቅርፅ፡፡ | 10. የቃላትን ቀጥተኛ ትርጉም ያውቃሉ፡፡ | - የቃላት ቀጥታ ትርጉም፡፡ |
| 5. በትክክለኛ የብእር አያያዝና አጣጣል ይጠቀማሉ፡፡ | - የብእር አያያዝና አጣጣል፡፡ | 11. በቃል ውስጥ የድምፅን መጥበትና መላላት ይለያሉ፡፡ | - በቃል ውስጥ የድምፅ መጥበትና መላላት፡፡ |
| 6. የቋንቋውን ስርአት ጠብቀው ቃላትን ይመስርታሉ፤ ይፅፋሉ፡፡ | - ከሆሄያት ቃላትን መመስረት፣ ማንበብና መፃፍ፡፡ | 12. በስርአተ-ነጥቦች (፡ ፡፡ ?) ይገለገላሉ፡፡ | - ሁለት ነጥብ፣ አራት ነጥብ፣ የጥያቄ ምልክት፡፡ |
| | | 13. አጫጭር አረፍተ-ነገሮን ያነባሉ፡፡ | - አጫጭር አረፍተ-ነገሮች፡፡ |
| | | 14. ከልዩ ልዩ መግለጫዎች የመረጃ ሀሳቦችን ያገኛሉ፡፡ | - ከስእሎች፣ ከፎቶግራፎች፣ ከቻርቶች መረጃ ሀሳቦችን ማግኘት፡፡ |
| | | 15. የተጠያቃዊ አስተሳሰብ ችሎታቸውን ያዳብራሉ፡፡ | - ነገሮችን ማነፃፀር፣ ማወዳደር፡፡ |
| | | 16. መመሪያዎችን ይከተላሉ፡፡ | - መመሪያዎችን መከተል፡፡ |
| | | 17. የቋንቋውን ስርአት ጠብቀው ይፅፋሉ፡፡ | - ሆሄያትን፣ ቃላትን፣ አረፍተ-ነገሮችን መፃፍ |

በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ በየትምህርቱ ክፍለ-እመት ይሸፈናሉ ተብለው የተነደፉትና የተመረጡት አስራ ሰባት አላማዎችና ይዘቶች በመማሪያ-ማስተማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተንፀባርቀው አይታዩም፡፡ ይህንን እውን የሚያደርገው ለክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ክንውን አላማዎችን ማሳኪያ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡት ዝርዝር ይዘቶች በመፅሀፉ ውስጥ አለመካተታቸው ነው፡፡ ለማስረጃነትም የሚከተሉት ቀርበዋል፤

በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ በአላማ አንድ ስር፣ ለመማር-ማስተማር ክንውን በመርሀ ደረጃ የተመላከቱት "ዋና ዋና የሆኑትን የአካል ክፍሎች መለየት (ገጽ 2)" እና "የክፍልና የቤት ቁሳቁሶችን መለየት (ገጽ 3)፣" የተሰኙትን ክንውኖች ለመተግበር የሚያስችሉ ዝርዝር ይዘቶች በመፅሀፉ ውስጥ ትኩረት አልተሰጣቸውም፡፡ ከዚህም ጋር በተለይ (ገጽ 3) በተ.ቁ. አምስትና አስራ አንድ እንዲተገበሩ የተጠቆሙትን ክንውኖች ለማስፈፀም የሚያስችል አቀራረብ አጥጋቢ አይደለም፡፡

ለአላማ ሁለት ግብ ማስመቻ "የድምፅ መጥበቅና መላላት፣ ተቀራራቢ ድምፆችና አስቸጋሪ ድምፆች (ገጽ 4)፣የቀለም አይነት፣ ባህላዊ መዝሙሮችና ዘፈኖች፣ የድርጊት አመልካች ቃላትን የሚያመላክቱ አረፍተ-ነገሮችን ማየትና ማስደመጥ፣ ተማሪዎችን ማለማመድ (ገጽ 5)፣" ተብለው የተዘረዘሩትን የክፍል ውስጥ ክንውኖች ለመተግበር የሚያስችሉ ዝርዝር ይዘቶች በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የሉም፡፡

አላማ ሶስትን አስመልክቶ፣ ለግብ ማስመቻ ይሆናል ተብሎ የተዘጋጀ ይዘት በምእራፍ ስምንት ስር ቀርቧል፡፡ ይሁን እንጂ፣ በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ ለክፍል ውስጥ መማር-ማስተማር ክንውን በተመላከተው መሰረት ቀላልና ግልፅ በሆነ ስልት አልቀረበም፡፡ ተማሪዎችን በሚስብ መልክ በስአላስአል ተደግፎ ተዘጋጅቶ ቢሆን ኖሮ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎትን ለማደበር የሚኖረው አስተዋፅኦ የላቀ ይሆን ነበር፡፡

የአላማ አራትን ተግባራዊነት ማንፀባርቅ የሚያስችሉና በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ለመማር-ማስተማር አስፈላጊ ናቸው ተብለው የተመላከቱት "በቅርፅና በድምፅ የሚመሳሰሉ ሆሄያትን ማቅረብና ማለማመድ፣ ህገኛ ቅርፅ ያላቸውና የሌላቸው ሆሄያት፣ መሪ ሆሄያትን አስቀድሞ ማስተዋወቅ፣ የሆሄያት አቀራረፅ (ገጽ 8-10)፣ ክንውኖችን የሚያንፀባርቁ ይዘቶች በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የሉም፡፡ በሌላ በኩል ግን፣ በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የውስብስብነት ባህርይ ያላቸው ሞክሼ ሆሄያት (ገጽ 1) ቀጥሎም፣ ዲቃላ ሆሄያት (ገጽ 3) የአማርኛ ትምህርት የመጀመሪያ ይዘቶች ሆነው በዝግጅቱ ውስጥ ቀርበዋል፡፡

አላማ አምስትን ተግባራዊ ለማድረግ፣ የመጽሐፉ ዝግጅት ተማሪዎች ያማርኛ ሆህያን ለመቅረጽ እንዲችሉ ከመሠረታዊ ምልክቶች (Basic strokes) ጋር አያስተዋውቅም፡፡ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ለእጅ ጽሕፈት አጣጣል የተመላከቱት ይዘቶች፤ "l = የቁም ሰረዝ፣- = አግድም ሰረዝ፣ ⊃ = ግራ ቅንፍ፣ ⊂ = ቀኝ ቅንፍ፣ 0 = ቀለበት (ገጽ 11)፣" በመጽሐፉ ውስጥ ጨርሶ አልተንፀባረቁም፡፡ የቋንቋ ትምህርት ድግግሞሽና ልምምድ ስለሆነ፣ መሠረታዊ ምልክቶች መነሻ ይዘት ሆነው ቢቀርቡ የቋንቋውን ትምህርት ጀማሪ ለሆኑት የክፍሉ ተማሪዎች የበለጠ ይጠቅማሉ፡፡

ለአላማ ስድስት መተግበር በተማሪው መፅሀፍ ውስጥ ይዘቶች ተካትተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ በተለይም (ገጽ 13-14) ከተ.ቁ. ስምንት እስከ ሃያ ድረስ የተዘረዘሩትን የክንውን መርሆዎች ለማለማመድ የሚያስችሉ ዝርዝር ይዘቶች በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ስፋት ባለው መንገድ ተጠናክረው ቢቀርቡ የተሻለ ይሆናል፡፡

የአላማ ሰባትን ተግባራዊነት ዕውን ለማድረግ ተማሪዎች በቃል እንዲገልፁና እንዲናገሩ የሚያስችሉ ይዘቶች በተማሪው መፅሀፍ ውስጥ በበቂ ሁኔታ የሉም፡፡ በተለይም በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሙትን "የድርጊት አረፍተ-ነገሮች፣ አወንታዊና አሉታዊ ንግግር፣ አጫጭር የጥያቄና መልስ ንግግር (ገጽ 15-16)፣" ክንውኖች በመፅሀፉ ውስጥ አይስተዋሉም፡፡

አላማ ስምንትን ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ይዘቶች በመፅሀፉ ውስጥ ጨርሶ አልተካተቱም፡፡ ስለሆነም፣ ለክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ክንውን ይበጃሉ ተብለው የቀረቡት መርሆዎች ትኩረት አልተሰጣቸውም ማለት ይቻላል፡፡

መጠንን ወይም ቁጥርን የሚመለከት ይዘቶችም በመፅሀፉ ውስጥ አልተካተቱም፤ ይህም አላማ ዘጠኝ መዘንጋቱን ያሳያል፡፡

አላማ አስርን ግብ የሚያደርሱ ይዘቶች በተለያዩ ምእራፎች በልዩ ልዩ መልመጃዎች አማካይነት በመፅሀፉ ውስጥ ተንፀባርቀዋል፡፡

አላማ አስራ አንድ የሚተገበርበት ይዘቶች በዝግጅቱ ውስጥ ፈፅሞ አልተካተቱም፡፡ ከመርሀና ከተግባራዊ ክንውን አንፃር ለአላማ አስራ ሁለት ግብ መምቻ በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ አስፈላጊው ይዘቶች በሚገባ ተካትተዋል፡፡

ከአላማ አስራ ሶስት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ይዘቶች በሚገባ በመፅሀፉ ውስጥ ተንፀባርቀዋል፡፡ ይህም ተማሪዎች የተለያዩ መልመጃዎችን ለመስራት ከሚያደርጓቸው ክንውኖች የሚስተዋል ነው፡፡

አላማ አስራ አራትንና አስራ አምስትን አስመልክቶ፣ ለተግባራዊነታቸው ተገቢነት ያላቸው ይዘቶች በዝግጅቱ ውስጥ አልተካተቱም፡፡ አላማ አስራ ስድስት ግን፣ ተማሪዎች የተለያዩ የመልመጃ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ በቀረቡት መመሪያዎች መሰረት በመፅሀፉ ዝግጅት ውስጥ ተግባራዊ ሆኖ ይገኛል፡፡

በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ በሁለቱ የትምህርት ክፍል-አመት ተለይተው የተመላከቱት አላማዎችና የይዘቶች አቀራረብ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ባመቱ ውስጥ ለቋንቋው ትምህርት ከተመደበለት የክፍለ-ጊዜያት ስርጭት አኳያ ተጣጥመውና ተለይተው አልተንፀባረቁም፡፡ ከዚህም ጋር በክፍሉ መርሀ-ትምህርት ውስጥ ላልተቀረፁ ዝርዝር አላማዎች ተዛማጅነት የሌላቸው ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካትተዋል፡፡ እነዚህም፣

". ተመሳሳይ ቃላት፣ ምእራፍ አምስት፣ (ገፅ 18)፣

. ድራማ መስራት፣ ምእራፍ ዘጠኝ፣ (ገፅ 32) ፣

. ነጠላ ሰረዝ፣ ምእራፍ አስራ አንድ፣ (ገፅ 37) ፣

. ድርብ ሰረዝ፣ ምእራፍ አስራ አንድ፣ (ገፅ 37) ፣

. ሪፖርት ማቅረብ፣ ምእራፍ አስራ አራት፣(ገፅ 52) ፣

. ግጥም፣ ምእራፍ አስራ ስድስት፣ (ገፅ 53-54)፣" የቋንቋውን ትምህርት ጀማሪ ለሆኑ ተማሪዎች ከእድገት ደረጃቸው ወይም ችሎታቸው ጋር የማይጣጣሙና ከባድ ይዘቶች ናቸው፡፡

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሚካተቱት ይዘቶች ጠቃሚነትና አስተማማኝነት የሚታየው ተማሪዎች የሚቀስሙትን እውቀትና የሚያዳብሩትን ክሂሎት ተግባራዊ ወይም እውን ለማድረግ ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ (ያስተሳሰብና ያሰራር ለውጥ) አንፃር ነው፡፡ የሚቀርቡት ይዘቶች በተማሪዎች አካባቢያዊ ህይወት ውስጥ ተጨባጭና ተአማኒ መሆን አለባቸው፡፡ አለበለዚያ ምናባዊ ምኞት ብቻ ሆነው ይቀራሉ፡፡ ቋንቋውን ለመማር የተዘጋጁት ይዘቶች በተማሪዎች ዘንድ ተፈፃሚነትን ካገኙ ጠቃሚነታቸው አያጠያይቅም፡፡ ይዘቶች ለተማሪዎች ግልፅና ማራኪ ሆነው በበቂ ሁኔታ በመልመጃዎች ተጠናክረው ከቀረቡ ለቋንቋው ትምህርት የተቀረፁትን አላማዎች ግብ ለማድረስ አስተማማኝ ይሆናሉ፡፡ ይዘቶች ስሜትን ወጥረው፣ ተማሪዎችን ለተሳትፎ በሚጋብዝ መንገድ መደራጀት ያሻቸዋል፡፡

በቋንቋው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረቡት የተለያዩ ይዘቶች የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎትን ከማጎልበት አኳያ ሲታዩ አስተማማኝነታቸው አጠያያቂ ነው፡፡ ይዘቶቹ በሚታዩ ነገሮች ላይ ተመስርተው፣ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ደረጃ በደረጃ የክፍሉን ተማሪዎች እንዲማሩ የማበረታታት አቅማቸው ደካማ ነው፡፡ ለዚህም በቂ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡

የትምህርቱ መጀመሪያ የሆነውን "የስርአተ-ድምፆች ብሎም የቃላት አመሰራረት (ገጽ 1)" ይዘቶች ስንመለከት፣ ከውስብስብ /ሞክሼ ሆህያት/ ትምህርቱን መጀመርና በቃላት ደረጃ ደግሞ "ሐብል፣ ሖመር፣ ስኒን፣ አቃዝ፣ ሆሳእና፣ ጉነኛ፣ ሰንሰለት፣ ኢንዱስትሪ፣ ኡደት፣ ዐልቦ፣ መንስኢ፣ ዕልህ (ገጽ 2)፣" ወዘተ. ለጀማሪ ተማሪዎች ተገቢነታቸውና ለትምህርቱ ስርፀት አስተማማኝነታቸው ያጠያይቃል፡፡ ከዚህም ጋር የረቂቅነት ባህርይ ያላቸውን ቃላት ያውም በስእላስእል ያልተደገፉ "እኸኸ፣ ይኸ፣ ይኼው፣ እልህ፣ ሆነ፣ ህይወት፣ ፃዕር፣ መሰል(ገጽ 2-3)፣" ወዘተ. የመሳሰሉት ሲታዩ ዝግጅቱን ጥያቄ ውስጥ ያስገባል፡፡

የቃላት ምስረታ ዋና የክፍሉ ትምህርት ይዘት ሆኖ እያለ፣ "የሚከተሉትን ቃላት አጥና (ገፅ 5)፣ የሚከተሉትን ቃላት አንብበህ ፍቾቻቸውን ተናገር፣ የሚከተሉትን ቃላት አንብበህ ፃፋቸው፣ ለሚከተሉት ቃላት ፍች ሰጥተህ አሳይ (ገፅ 6)፣" ወዘተ. በተሰኙ መመሪያዎች ብቻ ያውም ያለስዕላዊ መግለጫዎች ደርድሮ ማቅረብ ለቋንቋው ትምህርት ያለውን ጠቀሜታ አያሳይም፡፡

የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በተጠይቃዊ መንገድ ወይም በስርአት መደራጀት ይገባቸዋል፡፡ የይዘቶች በየደረጃው እያደጉ መሄድ፣ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከነጠላ ወደ ብዙ፣ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ ተመጥነው መቅረብ ባጠቃላይ ተከታታይነታቸው በመፅሀፉ ዝግጅት ውስጥ እንዲንፀባረቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህን አይነት አቀራረብ በመፅሀፉ ዝግጅት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ማየት አልተቻለም፡፡ በምእራፍ አንድ፣ ሞክሼ ሆህያትን ከማንበብ ቀጥሎ በመልመጃ ሁለት ስር፣ ከባለ ሶስት ሆህያት የተመሰረቱ ቃላትን በማስቀደምና በመሀል ደግሞ ከባለ ሁለት ሆህያት የተመሰረቱ ቃላትን አቅርቦ "አጥና" ማለት፣ በመሀል ደግሞ የዲቃላ ሆህያት ጥናት፣ ቀጥሎም ቃላትን መመስረትና ከባለ ሶስት፣ አራትና አምስት ቃላት የተገነቡ አረፍተ-ነገራትን "አንብብ" ማለት ያደረጃጀቱን ውስብስብነትና ምጣኔን አለመጠበቅ ያመላክታል፡፡

በምእራፍ ሁለት ስር ተመሳሳይ የሆነውን የቃላት ጥናት ይዘት ብንመለከት፣ በመልመጃ አንድ ስር ከባለ ሁለት ሆሄያት የተመሰረቱ ቃላትን በማቅረብ "እጥና" ይላል፡፡ ይህም ከከባድ የቃላት ጥናት ጀምሮ ወደ ቀላል የቃላት ጥናት አካሄድ ይስተዋልበታል፡፡ በምእራፍ አንድ ስር የቀረበው ይዘት በምእራፍ ሁለት፣ በምእራፍ ሁለት ስር የቀረበው በምእራፍ ሶስት ወዘተ. ጋር በመደጋገፍ አልቀረቡም፡፡

የይዘቶች ደረጃ ከተማሪዎች እድሜና የብስለት ደረጃ ጋር መመጣጠን አለባቸው፡፡ ስለዚህ፣ የመማሪያ መፅሀፉ ዝግጅት የክፍሉን ተማሪዎች የእድሜ ክልል በአመዛኙ ሊያጤን ይገባል፡፡ ይዘቶች ከተማሪዎች የብስለት ደረጃ ከፍ ወይም ዝቅ የሚሉ ከሆነ ስሜትን ለማሳብና አእምሮን ለማነቃቃት ብሎም ለግንዛቤ አይጋብዙም፡፡ ተማሪዎች በእድሜ የገፉ ከሆነና የትምህርቱ ይዘቶች ዝቅተኛ ከሆኑ፣ ስለማይመጥኗቸው የመናቅና ትኩረት ያለመስጠት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ በሌላም መንገድ የቋንቋው ትምህርት ይዘቶች በጣም ከፍ ወይም ከተማሪዎች የብስለት ደረጃ ከዘለሉ ተማሪዎች ለመረዳት ይቸግራቸዋል፡፡ ተገቢነት ወይም ተመጣጣኝነት የሌለው የትምህርት አቀራረብ ስነ-ልቦናዊ ችግሮችን ይፈጥራል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ለሚቀጥለው ደረጃ ትምህርት መሰልቸትንና ጥላቻን ሊጋብዝ ይችላል፡፡

ለጀማሪ ክፍል የሚዘጋጅ የቋንቋ ትምህርት በሚገባና በማያሻማ ሁኔታ መዘጋጀት አለበት፡፡ የቃላቱ አመራረጥ፣ የሀረጋቱ አሰካክና የዓረፍተ-ነገራቱ አቀነባበር ለክፍሉ ተማሪዎች መጣኝ ሊሆኑ ያሻል፡፡ ይህ ክፍል ለቋንቋው ትምህርት መሠረት መጣያ ስለሆነ፣ በሁሉም ዘርፍ ጥንቃቄን ይጠይቃል፡፡ በጽንሰ-ሀሳብ/በጭብጥ ደረጃም ቢሆን ባንዳንድ መልመጃዎች ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች ቋንቋውን ተረድተው ፍሬ ነገሮቹን ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማመሳከር ምላሾችን ይሰጣሉ ብሎ አፍ ሞልቶ ለመናገር ያስቸግራል፡፡ የሚከተሉትን ጥያቄያዊ አረፍተ-ነገራት ብንመረምር ያሰካክ ጉድለት፣ የሀሳብ መንዛዛት፣ የጥያቄዎች መደራረብና የምጣኔ ችግሮች ይታዩባቸዋል፡፡

- " . መሬት ቢሸጥ ቢለወጥ የሚያስከትለው ጉዳት አብራራ (ገፅ 51)፡፡
- . አድሀሪዎች መሬት ይሸጥ ይለወጥ የሚሉት ለምን ይመስልሃል (ገፅ 51)?
- . ለሽርሽር ወደ ፀሀይ መሄድ ይመቻልን? ለምን (ገፅ 54)?
- . የፀሐይ ሙቀት ከመሬት ሲደርስ የሚቀዘቅዘው ለምን ይመስልሃል (ገፅ 54)?
- . ብዙ ድመት ባለበት ቦታ ብዙ አይጦች ይመጣሉ (ገፅ 39)፡፡
- . ሀይሉ ከወንድሙ የተላኩለትን ደብዳቤ አንብቦ ጨርሶ ጥቂት ፀጥ ብሎ አሰበ ወዲያው ጠረጴዛውን አስተካክለ ብእርና ወረቀትም አቅርቦ ከዚያም የመልስ ደብዳቤ መፃፍ ጀመረ (ገፅ 38)፡፡

. በገጠርና በከተማ ውስጥ በቤተ-ሰብ መሀከል ሊኖር የሚችለውን የስራ ክፍፍል እክፍል ውስጥ በድራማ አሳዩ (ገፅ 32)።"

ለኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት የቃላት ጥናት ከፍተኛ ስፍራ አለው። በቋንቋው ትምህርት ውስጥ ለምንማራቸው ይዘቶች/ፅንሰ-ሀሳቦች ቃላት የሚሰጡት አገልግሎት ቀላል አይሆንም። ቃላት ሀሳብን ያንፀባርቃሉ፤ በማዳመጥና በማንበብ ሀሳብን ያስገኛሉ፤ መልሰንም ሀሳብን በመናገርና በመፃፍ እንድንገልፅ ይረዱናል። የየደረጃውን ተማሪዎች ግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ ቃላት ባግባቡ በአረፍተ-ነገራት ተቀናጅተው ሲቀርቡና አንቀፆች በሚገባ ሲደራጁ ያንድ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መፅሀፍ ዝግጅት ቋንቋ ብስለትና ብቃት አለው፤ ለደረጃው መጣኝና ተስማሚ ነው ማለት ይቻላል። ለጀማሪ ተማሪዎች የሚቀርቡ የቃላት ምስረታና ጥናት በመማሪያ መፅሀፍ ዝግጅት ውስጥ በስአላስአል መደገፍ አለባቸው። የክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ክንውኑ ደግሞ በተጨባጭ መርጃ መማሪያዎች ተጠናክረው ቢቀርቡ ትምህርቱን የበለጠ ግልፅና ተግባራዊ ያደርገዋል። ከዚህ አንፃር፣ የቋንቋው መማሪያ መፅሀፍ ዝግጅት ቋንቋ አጠቃቀም ባብዛኛው ለክፍሉ ተማሪዎች መጣኝ ሆኖ አይታይም። ይህንንም በሚከተሉት ጥቂት ማስረጃዎች ይመለከቷል፤

### የቃላትን ክብደት በተመለከተ፣

". ሁነኛ፣ ኡደት፣ መንስዔ፣ (ገፅ 2)፣
. ድግር፣ ማንጠቢያ፣ ባዕድ፣ (ገፅ 7፣ 16)፣
. ተመረዘ፣ ተሰራጨ፣ ተራባ (ገፅ 40)፣
. መቀልበስ፣ መንሳፈፍ (ገፅ 44)፣
. መንፈቀ-አመት፣ ተግባረ-ዕድ፣ ስርአተ-ትምህርት፣ ግብረ-ሃይል (ገፅ 52)፣" ወዘተ.

### የሀረጋትን አቀራረብ በተመለከተ፣

". ተጣማሪ ሀረጎች፣ እንጨት ሰብሬ፣ ልብሷን ለባብሳ (ገፅ 37)፣
. የማይረባ ማባከን፣ በከንቱ ማጥፋት (ገፅ 24)፣
. የሰደድ እሳት (ገፅ 20)፣
. የቤተ-ሰብ አሳዳሪ (ገፅ 31)፣
. ዲሞክራሲያን ሀይሎች፣ የጥያቄው ምላሽ፣ እሬትን በማር ሸፍነው፣ መሬት አልባ (ገፅ 50)፣" ወዘተ.

## የአረፍተ-ነገራትንና አነጋገሮችን በተመለከተ፣2

- ". በመደዳ ተደርድሮ የቀረበን ሀሳብ አንድ እንባቢ በቀላሉ ሊረዳው አይችልም (ገፅ 36)፡፡
- . ጥንታዊ የእህል መስፈሪያ (ገፅ 10)፡፡
- . ማለፊያ ጫማ ተጫምታለች (ገፅ 37)፡፡
- . አይኗን ተኳኩላለች (ገፅ 37)፡፡
- . ደመናው ከብዷል (ገፅ 37)፡፡
- . ሂሩት ህብስት ጋገረች (ገፅ 38)፡፡
- . እሬቱን በማር ሸፍነው ሊያጉርሱት፣ የሚተልሙት ቅዠት (ገጽ 50)፣" ወዘተ.

## ያንቀፅ አደረጃጀትንና የፅንሰ-ሀሳብን ክብደት በተመለከተ፣

"አርሶ አደሩ በትግሉ መሪ ድርጅት አግኝቶ ታግሎ እየታገለ ዛሬ በዲሞክራሲያውያን ሃይሎች አመራር የመሬቱን ባለቤትና ተጠቃሚ የመሆን ጥያቄው ምላሽ ያገኛል፡፡ ይሁን እንጂ አድህሪያን ተመልሶ ወደ ድህነት ቀምበር እንዲገባና መሬት በሀብታሞች እጅ እንዲገባ አርሶ አደሩ ያገኛትን መሬት የመሸጥና የመለወጥ መብት ይኑረው የሚል አጉል ልፈፋ እያደረጉ ናቸው፡፡ አድሃሪያን ለአርሶ አደሩ ያሰቡ መስለው እሬትን በማር ሸፍነው ሊያጎርሱት ይጣጣራሉ፡፡ ይህ ማለት ደግሞ መሬት አልባ ሆኖ ከሚኖርበት መንደር እንዲሰደድ የሚተልሙት ቅዠት ነው (ገፅ 50)፡፡" ወዘተ.

የተማሪው መጽሀፍ ተማሪዎች ከመምህራቸው ጋር አብረው ጎን ለጎን እየሰሩና በደረጃው እየተመራመሩ የሚማሩበት መሳሪያ ነው፡፡ መፅሀፉ ተማሪዎች በክፍልና በቤት ውስጥ በዋና ረዳትነት የሚጠቀሙበት ስለሆነ፣ለትምህርቱ አቀራረብ ከቋንቋው ግለፅነት ጋር ይዘቶች ተገቢነት ባላቸው ስዕሎች፣ ሰንጠረዦች፣ መግለጫዎችና ማስረጃዎች በተለያዩ ቀለማት ተውበው ቢቀርቡ ትምህርቱን ቀና ያደርገዋል፡፡ ይህ ከተደረገ መጽሐፉ የተማሪዎችን የመማር ስሜት እያነሳሳ የቋንቋውን ተግባቦተ-ክሂሎት ለማጎልበትና በምንባቦች መሳሪያነት የሚተላለፉ ጠቃሚ ጭብጦችን ለማስገንዘብ ያገለግላል፡፡

ለክፍሉ ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ በመፅሀፉ ውስጥ መሳሪያነት ከቀረቡት አስራ አንድ ምንባቦች ለስድስቱ ብቻ (ገፅ 4፣ 5፣ 9፣ 13፣ 42፣ 49) ጥቂል ስእሎች ያለ መግለጫ ይገኛሉ፡፡ የስእሎቹ መጨናነቅና ግልፅነት ማጣት እንዲሁም በቂ አለመሆን በጉልህ ይታያል፡፡ የተማሪዎችን ትኩረት ለመሳብ ያላቸው ሀይል ደካማ ነው፡፡

አንድ የመማሪያ መፅሐፍ ዝግጅት ተከታታይነት ያለው፣ አንዱ ባንዱ ላይ የተገነባ እንዲሆን ያስፈጋል፡፡ አለበለዚያ፣ የትምህርቱን ይዘቶች በስፋትና በጥልቀት ለመማር ችግር ይፈጥራል፡፡ ከአንድ ክፍል የተጀመረ ይዘት በመርህና በልምምድ ደረጃ እየተጠናከረ በቀጣይ ክፍሎች መለስተኛና በቂ ወይም የተሟላ ብቃት እንዲገኝበት ያሻል፡፡ ካልሆነ ግን የሚሰጠው ትምህርት ድንገተኛ ስለሚሆን ተማሪዎች በትምህርቱ ላይ ጥላቻን ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡

አራተኛ ክፍል ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት የተጀመረበት ደረጃ ስለሆነ፣ በመማሪያው መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች ሁሉ አዲሶች ናቸው፡፡ ስለሆነም፣ የቀጣዩ ክፍል ትምህርት ሲዘጋጅ ያራተኛውን ክፍል ትምህርት /ይዘቶች መሰረት ማድረግ አለበት፡፡ በምእራፍ አንድ፣ መልመጃዎች ስር የቀረበው "የቃላት ጥናት" በምእራፍ ሁለት፣ መልመጃዎች ስር ተከታታይነቱ ሲታይ፣ "የአረፍተ-ነገር ንባብ" ግን አልተንፀባረቀም፡፡ በምእራፍ ሁለት፣ መልመጃዎች ስር "የቃላት ፍች" በምእራፍ ሶስት መልመጃዎች ስር ተከታታይነቱ አይታይም፡፡ በምእራፍ ሶስት፣ መልመጃዎች ስር የቀረቡት "ቃላትንና አረፍተ-ነገሮችን ማንበብ፣ መፃፍ፣ አጫጭር መልሶችን መስጠት፣ መወያየት፣" ተከታታይነታቸው ይታያል፡፡ ከዚህ አኳያ፣ በየምእራፎቹ ውስጥ ተካትተው በየመልመጃዎቹ ስር ለልምምድ የሚቀርቡ ይዘቶች አደረጃጀት ጥንቃቄን ይሻሉ፡፡

የቋንቋው ትምህርት ይዘቶች ሲገመገሙ በመፅሀፉ ውስጥ የቀረቡትን መልመጃዎች መመርመር ለዚህም በቅድሚያ በመሳሪያነት የቀረቡትን ምንባቦች አይነትና ባህርይ መዳሰስ ያስፈልጋል፡፡

ለቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መሳሪያ ይሆናሉ ተብለው የተመረጡት ምንባቦች ጥንቃቄ ይኀድላቸዋል፡፡ West Michael (1966) እንደሚያስገነዝቡት፣ ማንኛውም አይነት ምንባብ ለቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ በመሳሪያት ሊያገለግል የሚችል ቢሆንም፣ በደረቅ ፅንሰ-ሀሳብና በደረቅ ቋንቋ በመሞላቱና በሌሎች ባህሪያቱም ምክንያቶች የትምህርት ተቀባዩን ስሜት የመሳብና የማስደሰት ሃይሉ አነስተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ፣ ተማሪዎችን የማያወያይ፣ የማያከራክር፣ የማያናግርና የማያፅፍ ስለሚሆን፣ የሚቀርቡት የክፍልና የቤት ስራ መልመጃዎች የቋንቋ ክሂሎትን ብሎም የመመራመርንና የፈጠራ ችሎታን የማይጠይቁ ይሆናሉ፡፡

ቋንቋን ለመማር-ማስተማር በመሳሪያነት የሚቀርብ ምንባብ ለዛ ያጣና ኪናዊ ልባስ የጎደለው ከሆነ፣ በቃላት ረገድ፣ ካገባብ አንፃር፣ አንብቦ ከመረዳት አኳያና ለጽህፈት ልምምድ የሚያስገኘው ፋይዳ እስከዚህም ነው፡፡

በአራተኛ ክፍል የቋንቋው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ በመሳሪያነት የቀረቡት ምንባቦች አስራ አንድ ናቸው፡፡ ስብጥራቸው ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል፤

- ማህበራዊ ነክ ምንባቦች፣ ሶስት (27%)
- ስነ-ፅሁፍ ነክ ምንባቦች፣ ሁለት (18%)
- ግብርና ነክ ምንባቦች፣ ሁለት (18%)
- ድርሰት ነክ ምንባቦች፣ ሁለት (18%)
- ጤና ነክ ምንባብ፣ አንድ (9%)
- ፖለቲካ ነክ ምንባብ፣ አንድ (9%)

(የምንባቦቹን አርእስት በአባሪ ሦስት ስር ይመለከቷል፡፡)

ከላይ በስሌት እንደተመላከተው ከምንባቦች ውስጥ ሁለቱ (18%) ስነ ጽሑፍ ነክ ምንባቦችና ሁለቱ (18%) ድርሰት ነክ ምንባቦች የተማሪዎችን አእምሮ እየኮረኮሩና እያዝናኑ የቋንቋውን ይዘቶች እንዲማሩ ከሌሎች በተሻለ ሁኔታ ያበረታታሉ፡፡ ምንባቦቹ ሁሉ በአራት፣ በአምስትና በሰባት አንቀፆች የተደራጁ ሲሆን፣ አብዛኞዎቹ ቃላት፣ ሀረጋት ብሎም ረጃጅም አረፍተ-ነገራት ከክፍሉ ተማሪዎች አቅም በላይ ናቸው፡፡ ተማሪዎች በግልፅ ይረዷቸዋል ማለት ያስቸግራል፡፡ በአስራ ዘጠኝ ስንኞች የተገጠመው ግጥም (ገፅ 53)፣ ከክፍሉ ተማሪዎች ችሎታ ጋር ተመጣጣኝና ተገቢ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ግን ምንባቦቹ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ጎናዊ ግንኙነት /horizontal relation/ አላቸው፡፡ በመርህ ደረጃ፣ ከምንባቦች ጋር የተያያዙት መልመጃዎች ተግባራቸው የቋንቋውን ትምህርት አላማዎች በሚጠበቀው ደረጃ ግብ ማድረስ ነው፡፡

> ተማሪው መለማመድ ያለበት ወደተጠቀሰው አላማ የሚያደርሰውን ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ማለት ተማሪው የንባብ ፍጥነትን ግብ ማስገኛ እንዲያግዝ መለማመጃው በንባብ ፍጥነት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል እንጂ ከዚህ ውጭ መሆን የለበትም፡፡ የእጅ ፅህፈትን እንዲያሻሽል የትምህርት አላማ ሲነደፍለት ለዚሁ የሚያግዘው ልምምድ ሊዘጋጅለት ይገባል እንጂ ስለ አትክልት እንክብካቤ ወይም ስለ መደብ አዘገጃጀት መለማመድ የለበትም፡፡
>
> /ተስፋየ ሸዋየ ፣ 1981*፡ 38/

ከዚህ አንፃር፣ ለቋንቋው መማሪያ የቀረቡት መልመጃዎች ሲታዩ በቅድሚያ የየምእራፉ መልመጃዎች አደረጃጀት የተዘበራረቀ ነው፡፡ ምእራፍ አንድ በአምስት መልመጃዎች፣ ምእራፍ ሁለት በአራት መልመጃዎች፣ ምእራፍ ሶስትና አራት በስድስት በስድስት መልመጃዎች፣ ምእራፍ አምስት በአምስት መልመጃዎች፣ ምእራፍ ስድስት በሶስት መልመጃዎች፣ ምእራፍ ሰባት በአራት መልመጃዎች፣ የቀረቡ ሲሆን፣ የቀሩት ምእራፎች መልመጃዎችም ከላይ ከተመላከቱት ቁጥር ውጭ አይደሉም፡፡

የቋንቋ ትምህርት መልመጃዎችን አይነትና አዘገጃጀት ስንመለከት፣ የማስተዋል ጥያቄዎችን በመልመጃ አንድ ስር፣ የአገባብ ወይም የሰዋስው ጥያቄዎችን በመልመጃ ሁለት ስር እና የአጠቃላይ እውቀት ማዳበሪያ ጥያቄዎችን በመልመጃ ሶስት ስር በማሰባሰብ ለተማሪዎች በማያደነጋግር መንገድ ማቅረብ ተመራጭነት እንዳለው ይታወቃል፡ በዚህ መሰረት አራቱን ተግባቦት-ክሂሎት ለማዳበር የሚያስችሉ፣ ከተማሪዎች ችሎታ፣ ፍላጎትና እድሜ ጋር የሚጣጣሙ፣ ተግባራዊ የሚሆኑ፣ ጠቃሚ መልእክት የሚያስተላልፉ፣ ከካባቢ ህይወት ጋር የሚዛመዱ፣ ተለጣጣቂነት ተደጋጋፊነት፣ ቅንጅትና ግልፅነት ያላቸው ጥያቄዎች ሚዛናቸውን ጠብቀው ሊንፀባረቁ ይገባል፡፡ ከዚህ አኳያ፣ ለክፍሉ የቀረቡት መልመጃዎች ቃላትና ሀረጋት ክብደት፣ የአረፍተ-ነገራቱ ርዝማኔና ጥልቀት ለደረጃው ተማሪዎች አንብቦ ለመረዳት ይከብዳሉ (ገፅ 52፣ 37፣ 50) ወዘተ.

በየመልመጃዎች ስር የሚቀርቡትን ጥያቄዎች ለመስራት መመሪያዎች /ትእዛዞች በጥንቃቄና ባገባቡ እንዲቀርቡ ያሻል፡፡ የማያሻሙ፣ በግልፅ ቋንቋ የተፃፉና ያልተንዛዙ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ መመሪያዎች ለተማሪዎች በቂ ጥቆማን በግልጽ በማስጨበጥ የተፈለገውን ሀሳብ የሚያስተላልፉ እንዲሆኑ ጥረት ማድረግ ይገባል፡፡ ከዚህ አኳያ፣ በምእራፍ አንድ ስር መልመጃ ሁለት (ገፅ 3)፣ መመሪያ የለውም፡፡ በምእራፍ ሁለት ስር የመልመጃ አራት (ገፅ 6)፣ መመሪያ ለደረጃው አሻሚ ነው፡፡ በገጽ ስድስት፣ ምእራፉ ሳይገለጽ ሁለት ሀሳቦችን የያዘ አንድ መመሪያ ከሥዕሎቹ ግርጌ ደግሞ "ስዕሊ 3" የሚል በትግርኛ ተጽፎ ቀርቧል፡፡ አንድ ትዕዛዝ ለአንድ ነጠላ ምላሽ ወይም ተግባር በግልጽ ቢቀርብ ተማሪዎችን ላያሻማና ላያደነጋግር ይችል ነበር፡፡ ከዚህም ሌላ ያንዳንድ መመሪያዎች ቋንቋ የመስተዋድድ፣ የተሳቢና የፆታ (ገፅ 12፣ 13፣ 18)፣ ወዘተ. ችግሮች አሉባቸው፡፡ የመመሪያዎች መርዘም (ገፅ 24፣ 27፣ 28) ሌላው ችግር ሲሆን፣ ተደራራቢና ለተግባራዊነታቸው ለክፍሉ ተማሪዎች የማይመጥኑ መመሪያዎች (ገፅ 32፣ 41፣ 48) ይስተዋላሉ፡፡

### ለ - የቋንቋው መማሪያ መፅሀፍ የተግባራዊነት ባህርያት፣

የአራተኛ ክፍል የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ገፅታ ሲገመገም፣ ያቀራረብ ገፅታውም አብሮ ይታያል፡፡ ስለዚህ፣ መፅሀፉ ከአጠቃላይ ባህርያት አንፃር ሲታይ ማራኪነቱ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

ለዝቅተኛ ክፍል የሚዘጋጅ የቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ከሽፋኑ ጀምሮ የውስጥ አደረጃጀቱ የተማሪዎችን ትኩረት የሚስብ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ አኳያ፣ በሽፋኑ ላይ የቀረበው መግለጫና የሽፋኑ የቀለም አጠቃቀም ገና ከጅምሩ የክፍሉን ልጆች ቀርቶ ያዋቂዎችን ስሜት እንኳን የሚማርክ አይደለም፡፡ የፊት ለፊት ሽፋኑ ስዕል (ዲዛይን) የለውም፡፡ ይህም የተማሪዎችን የመማር ፍላጎትና ትኩረት እናሳ ሊያደርግ የሚችል ሁኔታ ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ የቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ሲዘጋጅ አስፈላጊና በቂ ሀሳቦችን ያካተተ መግቢያ ሊዘጋጅለት ይገባል፡፡ ስለ መፅሀፉ ይዘቶች ተማሪዎችንና መምህራንን ግንዛቤ ማስጨበጥና ሊተኮርባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በግልፅ ቋንቋ ማመላከት ይጠበቅበታል፡፡ ምንም እንኳን በመማሪያው ጥራዝ መግቢያ ውስጥ የተጠቀሱት ነጥቦች ጠቃሚ ቢሆኑም፣ ሀሳቦቹ የተገለፁባቸው ቃላት፣ ሀረጋትና አረፍተ-ነገራት ለክፍሉ ተማሪዎች ይከብዳሉ፡፡ "ክሂሎት፣ ዲቃላ ሆህያት፣ ፓናል፣ አለምአቀፋዊ ተቀባይነት፣ ሁለ-ገብ ሰብእና፣ ብቁ ዜጋ" እና የአርትኦት ችግር በዝግጅቱ ውስጥ ጎልቶ ይታያል፡፡

## 4.2 ካማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ከትምህርተ-አርታኢያንና ከርሳነ-መምህራን የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ከብዙ የትምህርት ባለሙያዎች ውስጥ መምህራንና የትምህርት አስተዳዳሪዎች (teachers and educational administrators) እንደአካባቢውና ጥናቱ ተጨባጭ ሁኔታ የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፍን ገምጋሚ ሊሆኑ ይችላሉ (UNESCO 1977: 64)፡፡

ስለሆነም፣ የትምህርት ይዘቶችን ለመገምገም የሚያስችሉ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ /አማርኛ/ መምህራን፣ ትምህርተ-አርታኢያንና ርሳነ-መምህራን በጣም ከፍተኛ (5) ፣ ከፍተኛ (4)፣ መካከለኛ (3)፣ ዝቅተኛ (2)፣ በጣም ዝቅተኛ (1) እና አስተያየት መስጠት አልችልም (0) የደረጃ ነጥብ በማመላከት አስተያየት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

የቋንቋን ትምህርት አላማዎች ከግብ ለማድረስ የይዘቶችና የአቀራረብ ገፅታ ዝግጅት ደረጃ አጥጋቢ መሆን ያሻዋል፡፡ ስለሆነም፣ የትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ የይዘቶች ቅንብር፣ የይዘቶች አደራረስ፣ የመልመጃዎች አዘገጃጀት፣ የምሳሌዎች ብቃት፣ የስእሎች ማራኪነት፣ የመግለጫዎች ግልፅነት፣ የቋንቋ አጠቃቀምና የመማሪያ መፅሀፉ የህትመት ጥራት ደረጃ በዚህ ጥናት በዋና የመገምገሚያ መስፈርትነት ያገለገሉ ነጥቦች ናቸው፡፡

ሰንጠረዥ፡ 1፣ በከተማና በገጠር የሚገኙ የአራተኛ ክፍል የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን አጠቃላይ መረጃ /ዳራ/ በዞባ፣ በወረዳ፣ በትምህርት ቤት፣ በፆታ፣በእድሜ፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ በኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ፣ በት/ደረጃ፣ ባገልግሎትና በስልጠና ደረጃ፤

| | | | | ፆታ | | እድሜ | | | አፍ መፍቻ ቋንቋ | | ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ | | የት/ ደረጃ | ያገልግሎት ዘመን | | | አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የተደረገ ተጨማሪ ስልጠና | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተላውጦ | ዞባ | ወረዳ | ት/ቤት | ወ | ሴ | ከ20-30 | ከ31-40 | ከ41 በላይ | ትግርኛ | አማርኛ | አማርኛ | ትግርኛ | 12+ መማተ. | ከ1-5 | ከ6-10 | ከ11 በላይ | አግኝቻለሁ | አላገኘሁም |
| ከተማ | መሀከላዊ | ላእላይ ማይጨው | ወርኢ | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 |
| | ምስራቃዊ | ጋንታ አፈሹም | አግአዚ | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 |
| | መቀሌ | ሰሜን መቀሌ | ህንፀት | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 |
| | ደቡባዊ | ራያና አዘቦ | ደጎል | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 |
| ገጠር | መሀከላዊ | አድዋ | ማርያም ሽዊት | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 |
| | ምስራቃዊ | ሳእሲ ፃእዳ እምባ | ማይመገ ሊታ | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 |
| | | ኢሮብ | እንዳል ገዳ | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 |
| | ደቡባዊ | እንዳ መሆኒ | ተስፋ ፈረደ | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 |
| ድምር | 4 | 8 | 8 | 3 | 5 | 2 | 5 | 1 | 8 | 0 | 8 | 0 | 8 | 4 | 3 | 1 | 0 | 8 |

ሰንጠረዥ፡ 2፣ (ሀ) በከተማና በገጠር የተሰማሩ ትምህርት-አርታኢያን አጠቃላይ መረጃ (ዳራ) በዞባ፣ በወረዳ፣ በፆታ፣ በእድሜ፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ ፤ በኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ፣ በት/ደረጃ፣ ባገልግሎትና በስልጠና ደረጃ፤

| ተሳውጦ | ዞባ | ወረዳ | ፆታ | | እድሜ | | | አፍ መፍቻ ቋንቋ | | ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ | | የት/ ደረጃ | | ያገልገሉት ዘመን | | ለሙያቸው ብቃት የተካፈሉበት ተጨማሪ ስልጠና |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወ | ሴ | ከ20-30 | ከ31-40 | ከ41 በላይ | ትግርኛ | ሳሆኛ | ትግርኛ | አማርኛ | 12+ መማተ. | 12+ 2 | ከ6-10 | ከ11 በላይ | በትምህርተ-አርታኢ ያንነት |
| ከተማ | መሀከላዊ | ላእላይ ማይጨው | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 |
| | ምስራቃዊ | ጋንታ አፈሹም | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 |
| | መቀሌ | ሰሜን መቀሌ | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 |
| | ደቡባዊ | ራያና አዘቦ | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 |
| ገጠር | መሀከላዊ | አድዋ | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 |
| | ምስራቃዊ | ሳእሲ ፃእዳ እምባ | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 |
| | | ኢሮብ | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 |
| | ደቡባዊ | እንዳ መሆኒ | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 |
| ድምር | 4 | 8 | 8 | 0 | 0 | 3 | 5 | 7 | 1 | 0 | 8 | 7 | 1 | 1 | 7 | 8 |

ሰንጠረዥ፡ 2፣ (ለ) በከተማና በገጠር የተመደቡ ርሳነ-መምህራን አጠቃላይ መረጃ /ዳራ/ በዞባ፣ በወረዳ፣ በት/ቤት፣ በፆታ፣ በእድሜ፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ በኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ፣ በት/ደረጃ፣ ባገልግሎትና በስልጠና ደረጃ፤

| ተላውጦ | ዞባ | ወረዳ | ት/ቤት | ፆታ | | እድሜ | | | አፍ መፍቻ ቋንቋ | | ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ | | የት/ ደረጃ | | ያገልግሎት ዘመን | ለሙያው ብቃት ያገኙት ተጨማሪ ስልጠና |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወ | ሴ | ከ20-30 | ከ31-40 | ከ41 በላይ | ትግርኛ | አማርኛ | አማርኛ | ትግርኛ | 12+ መማተ. | 12+2 | ከ11 በላይ | በርእሰ-መምህርነት |
| ከተማ | መሀከላዊ | ላእላይ ማይጨው | ወርኢ | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 |
| | ምስራቃዊ | ጋንታ አፈሹም | አግአዚ | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| | መቀሌ | ሰሜን መቀሌ | ህንፀት | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 |
| | ደቡባዊ | ራያና አዘቦ | ደጎል | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 |
| ገጠር | መሀከላዊ | አድዋ | ማርያም ሸዊት | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 |
| | ምስራቃዊ | ሳእሲ ፃእዳ እምባ | ማይመገልታ | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | |
| | ደቡባዊ | አሮብ | እንዳልገዳ | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 |
| | | እንዳ መሆኒ | ተስፋ ፈረደ | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 |
| ድምር | 4 | 8 | 8 | 8 | 0 | 0 | 3 | 5 | 8 | 0 | 7 | 1 | 7 | 1 | 8 | 8 |

በሰንጠረዥ አንድ መሰረት፣ ጥናቱ ያቀፋቸው ያማርኛ ቋንቋ መምህራን በፆታ፣ በእድሜ በአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ በሁለተኛ ቋንቋ፣ በትምህርት ደረጃ፣ ባገልግሎት ዘመንና በስልጠና ደረጃ ተፈርጀዋል፡፡ ከስምንቱ መላሽ መምህራን ውስጥ ሶስቱ ወንዶችና አምስቱ ሴቶች ሲሆኑ፣ ሁሉም በትምህርት ደረጃቸው የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ምሩቆች ናቸው፡፡ አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር በሚረዱ ተጨማሪ ኮርሶች ላይ ያልተሳተፉ ናቸው፡፡ የሁሉም መምህራን አፍ መፍቻ ቋንቋ ትግርኛ ሲሆን፣ አማርኛ ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ነው፡፡ ካገልግሎት ዘመን አንፃርም ሰባቱ አስር አመት፣ አንድ ሴት መምህርት ካስራ አንድ አመት በላይ ያገለገሉ ሲሆን፣ የሴት መምህራን ተሳትፎ በከተማ ውስጥ ከወንዶች ልቆ ይገኛል፡፡ በገጠር ውስጥ ግን መሳ ለመሳ ነው፡፡ በዕድሜ አንፃር፣ አምስቱ ከ31 - 40 ባለው ማዕቀፍ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፣ ሁለቱ ከ20 - 30 አንዱ ደግሞ ከ40 ዓመት በላይ ናቸው፡፡

ሰንጠረዥ ሁለት (ሀ) እንደሚያመላክተው፣ በየወረዳዎች ከሚገኙት ትምህርተ-አርታኢያን ውስጥ ሰባቱ አፍ መፍቻቸው ትግርኛ ሲሆን፣ አንዱ ደግሞ ሳሆኛ ነው፡፡ ስምንቱም በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ሰልጥነው ለሙያው ብቃት በሚረዳቸው የትምህርተ-አርታኢያንነት ስልጠና የተሳተፉ ናቸው፡፡ ያገልግሎት ዘመናቸው ካንዱ በስተቀር ሰባቱ ካስራ አንድ አመት በላይ በስራው ላይ ቆይተዋል፡፡ አምስቱ ትምህርተ-አርታኢያን ከ41 ዓመት በላይ ሲሆኑ፣ ሦስቱ ከ31 - 40 ባለው ማዕቀፍ ውስጥ ይገኛሉ፡፡

ከስምንቱ ርሳነ-መምህራን ውስጥ ሰባቱ የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ምሩቃን ሲሆኑ፣ አንዱ የ12+2 የትምህርት ደረጃ አላቸው፡፡ ሁሉም ርሳነ-መምህራን ለሙያው ብቃት የሚያገለግላቸውን የርሳነ-መምህርነት ስልጠና በተጨማሪ አግኝተዋል፡፡ የሁሉም አፍ መፍቻ ቋንቋ ትግርኛ ሲሆን፣ ከአስራ አንድ አመት በላይ ያገለገሉ መሆናቸውን ሰንጠረዥ ሁለት (ለ) ይጠቁማል፡፡ በዕድሜ አንፃር አምስቱ ከ41 ዓመት በላይ ሦስቱ ደግሞ ከ31-40 ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ እንደሚገኙ አመላክተዋል፡፡

ከመምህራኑ በተገኘው ምላሽ መሠረት፣ ቋንቋውን በመማር ሂደት የተማሪዎችን የክሂል አጠቃቀም አስመልክቶ፣ አምስቱ የቋንቋው መምህራን ማለት (62.5%) ተማሪዎቻቸው የመናገር ችግር እንዳለባቸው ይጠቁማል፡፡ የቀሩት ሶስቱ (37.5%) መምህራን ደግሞ ተማሪዎቻቸው የመናገርና የማንበብ ችግሮች እንዳሉባቸው የሰጡት አስተያየት ያመላክታል፡፡ ይህ የሚያስረዳው በክሂሎት ደረጃ ያለው የችግር መጠን ይለያይ እንጂ በተናጠልም ሆነ በተጣምሮ የክፍሉ ተማሪዎች አሳሳቢ የመናገር ክሂል ችግር እንዳለባቸው ነው፡፡

ቋንቋውን በመማር ሂደት ለትምህርቱ ከቀረቡት የትምህርት ክፍሎች ወስጥ አራት የቋንቋው መምህራን (50%)ቱ ምንባቦቹ ክብደት እንዳላቸው አስተያየት ሲያቀርቡ፣ ሶስቱ (37%)ቱ ደግሞ የቋንቋው ትምህርት ቃሎች ለደረጃው ተማሪዎች ከችሎታቸው በላይ እንደሆኑ አስገንዝበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ፡ 3፣ ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር ያላቸው ፍላጎት፤**

| አስተያየት ሰጪዎች | አስተያየቶች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከፍተኛ | | መጠነኛ | | ዝቅተኛ | | አያስፈልግም | |
| | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| የቋንቋው መምህራን | 4 | 50 | 4 | 50 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ትምህርተ-አርታኢያን | 5 | 62.5 | 3 | 37.5 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ርሳነ-መምህራን | 5 | 62.5 | 2 | 25 | 1 | 12.5 | 0 | 0 |

የከፍተኛና የመጠነኛ ፍላጎት መግለጫ ደረጃ ተዳምሮ በቋንቋው መምህራን 100% ፣ በትምህርተ-አርታኢያን 100% እና በርሳነ-መምህራን 85.5% የተገኘው አስተያየት ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸውን ከፍተኛ ፍላጎትና የሰጡትን ትኩረት ያመላክታል፡፡

**ሰንጠረዥ፡ 4፣ አማርኛን በኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋነት በክልሉ ውስጥ የመማር-ማስተማር አስፈላጊነት**

| አስተያየት ሰጪዎች | አስተያየት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በጣም | | በመጠኑ | | አያስፈልግም | |
| | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| የቋንቋው መምህራን | 5 | 62.5 | 3 | 37.5 | 0 | 0 |
| ትምህርተ-አርታኢያን | 8 | 100 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ርሳነ-መምህራን | 8 | 100 | 0 | 0 | 0 | 0 |

በሰንጠረዥ አራት መሰረት፣ በመማር-ማስተማር ደረጃ 62.5% የቋንቋው መምህራን፣ 100% ትምህርተ-አርታኢያንና ርሳነ-መምህራን አማርኛን በኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋነት በክልሉ ውስጥ መስጠት በጣም አስፈላጊ መሆኑን አምነውበታል፡፡ ባጠቃላይ ሲታይ ማናቸውም አስተያየት ሰጪ አያስፈልግም የሚል ምላሽ ስላልሰጠ፣ በሁሉም ዘንድ አስፈላጊነቱ ጎልቶ ይታያል፡፡

ቋንቋውን ለማስተማር የሚረዳ ተጨማሪ ስልጠና ስለማግኘትና አለማግኘታቸው ስምንቱም የቋንቋው መምህራን ተጠይቀው ከሁለ-ገብ ያንደኛ ደረጃ መምህርነት ስልጠና በስተቀር አንዳችም ተጨማሪ ስልጠና ወይም ኮርስ እንዳላገኙ ገልፀዋል፡፡ ስምንቱ ትምህርተ-አርታኢያንና ስምንቱ ርሳነ-መምህራንም ይህንኑ ምላሽ አረጋግጠዋል፡፡

**ሰንጠረዥ፡ 5፣ የቋንቋው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፤**

| የቋንቋው ትምህርት ይዘቶች ገፅታ መግለጫ | አስተያየት ሰጪዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የቋንቋው መምራን | | | | | | ትምህርተ-አርታኢያን | | | | | | | ርሳነ-መምህራን | | | | | | |
| | የደረጃ ነጥብ | | | | | | የደረጃ ነጥብ | | | | | | | የደረጃ ነጥብ | | | | | | |
| | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ | አስተያየት ያልሰጡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ | አስተያየት ያልሰጡ |
| የይዘቶች ፍላጐትን የማሟላት ብቃታቸው | 0 | 0 | 1 | 6 | 1 | 2.0 | 0 | 0 | 1 | 4 | 2 | 1.8 | 1 | 0 | 0 | 2 | 4 | 1 | 2.1 | 1 |
| ይዘቶች ከተማሪዎች አካባቢያዊ ህይወት ጋር ያላቸው ግንኙነት | 0 | 1 | 3 | 3 | 1 | 2.8 | 0 | 0 | 2 | 3 | 2 | 2.0 | 1 | 0 | 0 | 2 | 4 | 1 | 2.1 | 1 |
| የይዘቶች መጣኝነት | 0 | 0 | 1 | 3 | 4 | 1.6 | 0 | 0 | 2 | 3 | 1 | 2.1 | 0 | 0 | 0 | 2 | 4 | 1 | 2 | 0 |
| የይዘቶች ወቅታዊነት | 0 | 0 | 4 | 3 | 1 | 2.3 | 0 | 0 | 3 | 3 | 2 | 2.1 | 0 | 0 | 0 | 4 | 4 | 0 | 2.5 | 0 |

ለቋንቋው ትምህርት የተመረጡት ይዘቶች የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማሟላት ያላቸውን ብቃት አስመልክቶ፣ ስምንቱ የቋንቋው መምህራን በአማካይ 2፣ ስምንቱ ትምህርተ-አርታኢያን በአማካይ 1.8 እና ስምንቱ ርሳነ-መምህራን በአማካይ 2.1 የደረጃ ነጥብ ሰጥተዋል፡፡ የሁሉንም የትምህርት ባለሙያዎች ያስተያየት ነጥቦች በማዋሀድ 2.1 አማካይ የደረጃ ነጥብ እናገኛለን፡፡ ይህም የትምህርቱ ይዘቶች የሚገኙበትን ዝቅተኛ ደረጃ ያሳያል፡፡

የትምህርቱ ይዘቶች ከተማሪዎች አካባቢያዊ ህይወት ጋር ስላላቸው ግንኙነት፣ መምህራን 2.8፣ ትምህርተ-አርታኢያን 2 እና ርዕሰ-መምህራን 2.1 የደረጃ ነጥብ በመስጠት አመላክተዋል፡፡

ሶስቱ የትምህርት ባለሙያዎች የሰጡት አማካይ የ1.9 የደረጃ መለኪያ ነጥብ የይዘቶቹን ለክፍሉ ተማሪዎች አለመመጠን ይጠቁማል፡፡ ከወቅታዊነትም አንፃር ሲታይ፣ መምህራን 2.3 እና ርዕሰ-መምህራን 2.5 በአማካይ 2.4 የደረጃ ነጥብ ተንፀባርቋል፡፡ ከዚህ አኳያ ከሌሎቹ ይልቅ የይዘቶች ወቅታዊነት በተሻለ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መገመት ይቻላል፡፡

**ሰንጠረዥ፡ 6፣ የትምህርቱ ይዘቶች ቅንብር፣**

| የትምህርቱ ይዘቶች ቅንብር መገለጫ | አስተያየት ሰጪዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የቋንቋው መምህራን | | | | | | ትምህርተ-አርታኢያን | | | | | | | ርዕሰ-መምህራን | | | | | | |
| | የደረጃ ነጥብ | | | | | | የደረጃ ነጥብ | | | | | | | የደረጃ ነጥብ | | | | | | |
| | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ | አስተያየት ያልሰጡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ | አስተያየት ያልሰጡ |
| የማዳመጥ ክሂልን የማዳበር ሁኔታ | 0 | 0 | 4 | 3 | 1 | 2.4 | 0 | 0 | 3 | 3 | 0 | 2.5 | 2 | 0 | 0 | 3 | 5 | 0 | 2.3 | 0 |
| የመናገር ክሂልን የማዳበር አቅም | 0 | 0 | 3 | 4 | 1 | 2.3 | 0 | 0 | 2 | 2 | 0 | 25 | 2 | 0 | 0 | 4 | 4 | 0 | 1.8 | 0 |
| የማንበብ ክሂልን የማዳበር አቅም | 0 | 0 | 3 | 3 | 2 | 2.2 | 0 | 0 | 2 | 4 | 0 | 2.3 | 2 | 0 | 0 | 3 | 4 | 1 | 2.4 | 0 |
| የመፃፍ ክሂልን የማጎልበት አቅም | 0 | 0 | 3 | 4 | 1 | 2.3 | 0 | 0 | 3 | 2 | 0 | 2.6 | 3 | 0 | 0 | 0 | 5 | 2 | 2.0 | 2 |
| የይዘቶችና የክፍለ-ጊዜያት መመጣጠን | 0 | 0 | 0 | 3 | 5 | 1.4 | 0 | 0 | 0 | 6 | 2 | 1.8 | 0 | 0 | 0 | 0 | 4 | 3 | 1.6 | 1 |

የቋንቋውን ተግባቦት-ክሂሎት ከማጎልበት አንፃር፣ እያንዳንዱን ክሂል በተናጠል ያዳብራሉ ተብለው በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የተመላከቱ ይዘቶች የሉም፡፡ ይህም የሚያሳየው የክፍሉ ትምህርት ይዘቶች በተቀናጀ ሂደት የቀረቡ መሆናቸውን ነው፡፡ ይሁን እንጂ የቋንቋው መጽሐፍ ዝግጅት ተማሪዎች እያንዳንዱን የክሂል አይነት ለማጎልበት እንዲችሉ ከማድረግ አኳያ ይዘቶች ያላቸውን ብቃት ለማወቅ ተችሏል፡፡ የመምህራን 2.4፣ የትምህርተ-አርታኢያን 2.5 እና የርሳነ-መምህራን 2.3 ያስተያየት ደረጃ ነጥቦች ይዘቶቹ ከሌሎቹ ክሂሎት ይልቅ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር ያላቸው አስተዋፅኦ ሻል ያለ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ሶስቱ የትምህርት ባለሙያዎች ይዘቶቹ የመናገር ክሂልን ምን ያህል እንደሚያዳብሩ የሰጡት አማካይ 2.2፣ የማንበብ ክሂልን ከማጎልበት አንፃር 2.4 እና የመፃፍ ብቃትን 2.4 ጣምራ የደረጃ ነጥቦች ይዘቶቹ ሶስቱን ተግባቦት-ክሂሎት ለማዳበር ያላቸው የአስተማማኝነት ደረጃ አናሳ መሆኑን በይፋ ያሳያል፡፡

**ሰንጠረዥ፡ 7፣ የይዘቶች አደራረስ፡**

| የትምህርት ይዘቶች አደራረስ መገለጫ | አስተያየት ሰጪዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የቋንቋው መምህራን | | | | | | ትምህርተ-አርታኢያን | | | | | | | ርሳነ-መምህራን | | | | | | |
| | የደረጃ ነጥብ | | | | | | የደረጃ ነጥብ | | | | | | | የደረጃ ነጥብ | | | | | | |
| | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ | አስተያየት ያልሰጡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ | አስተያየት ያልሰጡ |
| የይዘቶች ቅደም ተከተል | 0 | 0 | 3 | 5 | 0 | 2.3 | 0 | 0 | 1 | 4 | 1 | 2.0 | 2 | 0 | 0 | 1 | 4 | 2 | 1.8 | 1 |
| የይዘቶች ወጥነት | 0 | 0 | 2 | 6 | 0 | 2.2 | 0 | 0 | 3 | 4 | 1 | 2.9 | 0 | 0 | 0 | 2 | 3 | 0 | 2.9 | 3 |

ይዘቶች ቅደም ተከተልን/ ስነ-ትምህርታዊ አቅጣጫን ስለመያዛቸው ስምንቱ የቋንቋው መምህራን 2.3፣ ስድስቱ ትምህርተ-አርታኢያን 2 እና ሰባቱ ርሳነ-መምህራን 1.8 አማካይ የደረጃ ነጥቦችን አመላክተዋል፡፡

በይዘቶች አደራረስ ስር ወጥነትን አስመልክቶ፣ የሶስቱ ባለሙያዎች ጣምራ አማካይ የደረጃ ነጥብ ሲታይ 2.5 ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህም ከይዘቶች ቅደም ተከተል አደረጃጀት ይልቅ የወጥነታቸው ደረጃ ሻል ያለ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

**ሰንጠረዥ፡ 8፣ የቋንቋው ትምህርት መልመጃዎች ዝግጅት፣**

| የመልመጃዎች አቀራረብ መግለጫ | አስተያየት ሰጪዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የቋንቋው መምራን | | | | | | ትምህርት-አርታኢያን | | | | | | | ርዕሰ-መምህራን | | | | | | |
| | የደረጃ ነጥብ | | | | | | የደረጃ ነጥብ | | | | | | | የደረጃ ነጥብ | | | | | | |
| | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ | አስተያየት ያልሰጡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ | አስተያየት ያልሰጡ |
| የተለያዩ ጥያቄዎች የመካተታቸው ሁኔታ | 0 | 0 | 2 | 5 | 1 | 2.1 | 0 | 0 | 4 | 3 | 1 | 2.4 | 0 | 0 | 0 | 3 | 4 | 0 | 2.4 | 1 |
| የጥያቄዎች በበቂ መጠን መቅረብ | 0 | 0 | 3 | 5 | 0 | 2.4 | 0 | 0 | 2 | 5 | 1 | 2.1 | 0 | 0 | 0 | 2 | 4 | 1 | 2.1 | 1 |
| የጥያቄዎች አመራማሪነት | 0 | 0 | 3 | 4 | 1 | 2.2 | 0 | 0 | 3 | 3 | 2 | 2.4 | 0 | 0 | 0 | 3 | 5 | 0 | 2.4 | 0 |
| የጥያቄዎች ተግባራዊነት | 0 | 1 | 2 | 4 | 0 | 2.3 | 0 | 0 | 3 | 3 | 1 | 2.1 | 1 | 0 | 0 | 4 | 3 | 1 | 2.4 | 0 |
| የመመሪያዎች ግልፅነት | 0 | 0 | 4 | 4 | 0 | 2.5 | 0 | 0 | 4 | 3 | 1 | 2.4 | 0 | 0 | 0 | 3 | 3 | 1 | 2.3 | 1 |

በትምህርቱ መልመጃዎች ዝግጅት ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች በዓይነት የተለያዩ ስለመሆናቸው የቋንቋው መምህራን 2.1፣ ትምህርተ-አርታኢያን 2.4 እና ሰባት ርዕሰ-መምህራን 2.4 የደረጃ ነጥብ ሰጥተዋል፡፡ የሁሉንም ባለሙያዎች አስተያየት ባማካይ ስንመለከት 2.5 ይሆናል፡፡ ይህም መልመጃዎቹ የተለያዩ ጥያቄዎችን በማካተት ረገድ ደህና ናቸው፡፡

የቋንቋው መምህራን የሰጡት 2.4 የደረጃ ነጥብና የቀሩት የሶስቱ ክፍል ባለሙያዎች አስተያየት ተመሳሳይ የሆነ 2.1 አማካይ የደረጃ ነጥብ የየመልመጃው ጥያቄዎች በበቂ መጠን እንዳልቀረቡ ያስገነዝባል፡፡ በመልመጃዎች ስር የቀረቡት ልዩ ልዩ ጥያቄዎች የክፍሉን ተማሪዎች በማነቃቃት ወይም በማመራመር ረገድ፣ መምህራኑ 2.2፣ ትምህርተ-አርታኢያኑ 2.4 እና ርዕሰ-መምህራኑ 2.4 የደረጃ ነጥብ አመላክተዋል፡፡ ከዚህም ጋር የጥያቄዎችን ተግባራዊነት በተመለከተ፣ የሶስቱ ባለሙያዎች 2.3 አማካይ የደረጃ ነጥብ ጥያቄዎቹ ያላቸውን የብቃት ዝቅተኛነት ያንፀባርቃል፡፡ በሌላ በኩል ግን፣ የየመልመጃውን ጥያቄዎች መመሪያዎች /ትእዛዞች/ ግልፅነት በተመለከተ፣ የሶስቱም ባለሙያዎች አስተያየት አማካይ የደረጃ ነጥብ 2.4 ነው፡፡ ይህም የጥያቄዎቹ መመሪያዎች አቀራረብ ሻል ያለ ሆኖ መገኘቱን ይገልፃል፡፡

ሰንጠረዥ፡ 9፣ የምሳሌዎችና ስእላዊ መግለጫዎች አቀራረብ፡

| የምሳሌዎችና ስእላዊ መግለጫዎች አጠቃቀም መግለጫ | አስተያየት ሰጪዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የቋንቋው መምህራን | | | | | | ትምህርት-አርታኢያን | | | | | | | ርዕሰ-መምህራን | | | | | |
| | የደረጃ ነጥብ | | | | | | የደረጃ ነጥብ | | | | | | | የደረጃ ነጥብ | | | | | |
| | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ | አስተያየት ያልሰጡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ |
| ከትምህርቱ ይዘቶች ጋር ያላቸው ተገቢነት | 0 | 0 | 0 | 3 | 5 | <u>1.4</u> | 0 | 0 | 0 | 5 | 2 | <u>1.7</u> | 1 | 0 | 0 | 1 | 5 | 2 | <u>1.9</u> |
| ማራኪነታቸው | 0 | 0 | 1 | 2 | 5 | <u>1.8</u> | 0 | 0 | 0 | 6 | 2 | <u>1.8</u> | 0 | 0 | 0 | 0 | 3 | 5 | <u>1.4</u> |
| ግልፅነታቸው | 0 | 0 | 1 | 1 | 6 | <u>1.8</u> | 0 | 0 | 1 | 4 | 3 | <u>1.8</u> | 0 | 0 | 0 | 0 | 5 | 3 | <u>1.6</u> |

በሰንጠረዥ ዘጠኝ በግልፅ እንደተመላከተው፣ የቋንቋውን ትምህርት ጀማሪ ለሆኑት ተማሪዎች ለየርእሰ- ትምህርቱ የተሰጡት/የቀረቡት የየመልመጃው ምሳሌዎችና የየምንባቡ ስእላዊ መግለጫዎች ተገቢነት ወይም መጣኝነት በመምህራን 1.4፣ በትምህርት-አርታኢያን 1.7 እና በርዕሰ-መምህራን 1.9 ያስተያየት ደረጃ ተጠቁሟል፡፡ በሶስቱ የትምህርት ባለሙያዎች የተሰጡት ደረጃዎች ሲነፃፀሩ ብሎም በጣምራ አማካይ የደረጃ ነጥብ 1.6 ሲታይ፣ ችግሩ የጎላ መሆኑን ባልተራራቀ የደረጃ ነጥብ መረጃነት ለማየት ይቻላል፡፡

የትምህርቱን ስእላዊ መግለጫዎች ማራኪነት አስመልክቶ የቋንቋው መምህራን 1.8፣ ትምህርት-አርታኢያን 1.8 እና ርሳነ-መምህራን 1.4 ደረጃ ሰጥተዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው የዝግጅቱ ምሳሌዎችና ስእላዊ መግለጫዎች በሶስቱም ክፍል የትምህርት ባለሙያዎች አይን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ነው፡፡

በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡት ምሳሌዎችና ስእሎች፣ ብሎም የመግለጫዎችን ግልፅነት በተመለከተ፣ መምህራን 1.8፣ ትምህርት-አርታኢያን 1.8 ርሳነ-መምህራን 1.6 ነጥብ በመስጠት ደረጃውን ጠቁመዋል፡፡ ከሶስቱም መላሾች ያስተያየት ነጥብ አንፃር፣ የንቋንቋው ትምህርት ምሳሌዎችና መግለጫዎች ግልፅነት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

የትምህርቱ ይዘቶች የቀረበበት የቋንቋ አጠቃቀም ለቃላቱ ተገቢነት ስምንቱ የቋንቋው መምህራን 2.3፣ ለአረፍተ-ነገሮቹ አሰካከና ተነባቢነት 2.1 እና ለምንባቦቹ መጣኝነት 2 አማካይ የደረጃ ነጥቦችን አመላክተዋል፡፡ ስለሆነም፣ የአረፍተ-ነገሮቹና የምንባቦቹ ግልፅነትና ተነባቢነት ለደረጃው ተማሪዎች ከአቅማቸው በላይ ወይም በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን የተሰጡት አስተያየቶች ያስገነዝባሉ፡፡

**ሰንጠረዥ፡ 10፣ የቋንቋው መማሪያ መጽሐፍ የህትመት ጥራት ደረጃ፤**

| የቋንቋው መማሪያ መፅሀፍ የህትመት ጥራት ደረጃ መግለጫ | አስተያየት ሰጪዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የቋንቋው መምራን | | | | | | ትምህርት-አርታኢያን | | | | | | ርሳነ-መምህራን | | | | | |
| | የደረጃ ነጥብ | | | | | | የደረጃ ነጥብ | | | | | | የደረጃ ነጥብ | | | | | |
| | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | አማካይ |
| የፊደሎቹ /ሆሄያቱ/ ጉልህነት መጠን | 0 | 0 | 1 | 5 | 2 | 19 | 0 | 0 | 5 | 2 | 1 | 2.5 | 0 | 0 | 1 | 3 | 4 | 1.6 |
| የወረቀቱ ጥራት | 0 | 0 | 0 | 1 | 7 | 1.1 | 0 | 0 | 1 | 2 | 5 | 1.5 | 0 | 0 | 0 | 2 | 6 | 1.3 |
| የመፅሀፉ መጠን /ላያያዝ ያለው አመቺነት | 0 | 0 | 0 | 1 | 7 | 1.1 | 0 | 0 | 0 | 3 | 5 | 1.3 | 0 | 0 | 0 | 1 | 7 | 1.1 |
| አጠራረዙ | 0 | 0 | 0 | 2 | 6 | 1.3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 8 | 1.0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 6 | 1.3 |
| የሽፋኑ ስእል (ዲዛይን) ማራኪነት | 0 | 0 | 0 | 0 | 8 | 1.0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 8 | 1.0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 8 | 1.0 |

የቋንቋው መማሪያ መፅሀፍ የፊደሎች /ሆሄያት የጉልህነት መጠን ለጀማሪዎች ሊቀርብ ከሚገባው ሁኔታ አንፃር ሲታይ መምህራን 1.9፣ ትምህርተ-አርታኢያን 2.5 እና ርዕሰ-መምህራን 1.6 ያስተያየት ነጥብ በመስጠት የጉልህነት ደረጃውን ፈርጀዋል፡፡ የሁለቱ ባለሙያዎች ተመሳሳይ የደረጃ ነጥብ የፊደሎቹን መጠን ዝቅተኛነት ይጠቁማል፡፡

በመምህራን 1.1፣ በትምህርተ-አርታኢያን 1.5 እና በርዕሰ-መምህራን 1.3 በተሰጠው ያስተያየት ደረጃ መሰረት የቋንቋው መማሪያ መፅሀፍ የጥራት ችግር አለበት፡፡ በሌላም በኩል ከሶስቱም ባለሙያዎች በተገኘው 1.5 አማካይ የደረጃ ነጥብ መረጃነት መፅሀፉ ለክፍሉ ተማሪዎች ላያያዝ አመቺ አይደለም፡፡ አጠራረዙም ተራ የሆነና ሽፋኑም ያልጠነከረ ሲሆን፣ ስእል (ዲዛይን) ጨርሶ እንደሌለው መላሾቹ አመላክተዋል፡፡

ባማርኛ ቋንቋ  ትምህርት ሂደት ከትግርኛው ትምህርት ጋር እየተምታቱ የክፍሉን ተማሪዎች የሚያስቸግሩ ንጥረ-ድምፆች ይገኛሉ፡፡ "ሀ፣ ሃ፣ ሐ፣ ሓ፣ ኸ፣ ኻ፣ አ፣ ኣ፣ ዐ፣ ዓ" ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ባማርኛ የድምፅም ሆነ የትርጉም ለውጥ የማያመጡ፣ ነገር ግን በትግርኛ ትምህርት ሂደት የድምፅና የትርጉም ለውጥ የሚያመጡ ያማርኛ ሞክሼ ሆሄያት በተማሪዎች ዘንድ ችግር እየፈጠሩ እንደሚገኙ ስምንቱም የቋንቋው መምህራን ተመሳሳይ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

ሰንጠረዥ፡ 11፤ የሞክሼ ሆሄያት ውስብስብነት፤

| ንጥረ-ድምፅ (Phoneme) | ንጥረ-ድምፃዊ አነባብ | የትግርኛ ቃል | ስነ-ድምፃዊ አፃፃፍ (Phonetics) | ያማርኛው ትርጉም |
|---|---|---|---|---|
| ሀ | /hə/ | አብርሀ<br>አድሀበ | [ʔabrɨthə]<br>[ʔadhəbə] | አበራ<br>አተኮረ |
| ሃ | /ha/ | በሪሃ<br>ሃፍቲ | [bəriha]<br>[hafti] | በራች<br>ሀብት |
| ሐ | /ħə | ሠርሐ<br>ፀብሐ | [sərħə]<br>[səbħə] | ሰራ<br>ጠባ |
| ሓ | /ħa/ | ሓረስታይ<br>ሓዳር | [ħarəstay]<br>[ħadar] | ገበሬ<br>ትዳር |
| ኸ | /xə/ | ተኸደን<br>እንተረብካዮ | [təxədən]<br>[ʔɨntərəxəbkayyo] | ልበስ<br>ካገኘኸው |
| ኻ | /xa/ | ድኻ<br>ኻሊእ | [dɨxa]<br>[xaliʔ] | ደሀ<br>ሌላ |
| አ | /ʔə/ | ቀንአ<br>አርአየ | [qənʔə]<br>[ʔarʔəyə] | ቀና<br>አሳየ |
| ኣ | /ʔa/ | ኣድጊ<br>ኣብኡ | [ʔadgi]<br>[ʔabʔu] | አህያ<br>እዚያ |
| ዐ | /ʕə/ | በልዐ<br>ጠርዐ | [bəlʕə]<br>[tərʕə] | በላ<br>አቤቱታ |
| ዓ | /ʕa/ | ዓሰርተ<br>ዓርኪ | [ʕassərtə]<br>[ʕarki] | አስር<br>ጓደኛ |

ከላይ ከተጠቀሱት ችግሮች በተጨማሪ ከትግርኛው ቋንቋ የውስጥ ባህርያት አንፃር፣ የክፍሉ ተማሪዎች አማርኛን ሲማሩ "ሰ፣ ሸ፣ ዐ፣ ከ፣ አ፣ ሐ፣ ጨ፣ ፀ፣ የ፣ ለ፣ ኸ፣ ተ፣ ቸ" ንጥረ-ድምፆችን የማለዋወጥ ችግር እንዳለባቸው መምህራኑ ጠቁመዋል፡፡

ሰንጠረዥ፡ 12፣ ንጥረ-ድምፆችን የመለወጥ ችግር፤

| ንጥረ-ድምፅን መለወጥ | አማርኛ | ትግርኛ |
|---|---|---|
| ሰ → ሸ | ቁስ | ቁሽ |
| ሀ → ከ | ሁኔታ | ኩኔታ |
| አ → ሐ | አዲስ | ሐዲሽ |
| ጨ → ፀ | አጭር | ሐፂር |
| የ → ለ | የኩቴት | ለኩቴት |
| ከ → ኸ | ማእከል | ማእኸል |
| ከ → ቻ | ሚካኤል | ሚቻኤል |
| ተ → ቸ | ምናልባት | ምናልባቺ |
| የ → ሀ | ሻይ | ሻሂ |

ንጥረ-ድምፆችን ከማምታታት ችግር ጋር ተገቢ ቅደም ተከተላቸውን የመጠበቅ ችግርም ሌላው ነው፡፡

ሰንጠረዥ፡ 13፣ የንጥረ-ድምፆችን ትክክለኛ ድምፅ አለመጠቀም፤

| ንጥረ-ድምፅን መለወጥ | አማርኛ | ትግርኛ |
|---|---|---|
| 1 (ግእዝ) → 7 (ሳብእ) | አለ | አሎ |
| 4 (ራብእ) → 6(ሳድስ) | ነፃነት | ነፅነት |
| 5 (ሀምሳ) → 6(ስድሳ) | ጤና | ጥእና |
| 5 (ሀምስ) → 1(ግእዝ) | ሰኔ | ሰነ |
| 6 (ሳድስ) → 3(ሳልስ) | ትምህርት | ትምህርቲ |
| 6 (ሳድስ) → 1(ግእዝ) | ግምገማ | ገምጋም |
| 1 (ግእዝ) → 4(ራብእ) | ደሀ | ዳሀ |

ስለሆነም፣ በሰንጠረዥ 11፣ 12 እና 13 የተመላከቱትንና የመሳሰሉትን ችግሮች ለማቃለል ልማዳዊ የቋንቋውን የፊደል ገበታ በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ማዘጋጀት ያሻል፡፡ ይህም የቋንቋውን ንጥረ-ድምፆች ለማዳመጥ፣ ለመናገር፣ ለማንበብና ለመፃፍ እንዲቻል በጎና የተጠናከረ ልምምድ ለማድረግ ያግዛል፡፡

ስምንቱ የቋንቋው መምህራን፣ ስምንቱ ትምህርተ-እርታኢያንና ስምንቱ ርሳነ-መምህራን አማርኛ የፌዴራሉ መንግስት የስራና የብሄር/ብሄረሰቦች የጋራ መግባቢያ ቋንቋ/Language of Wider Communication/ ስለሆነ፣ ቋንቋውን መማር-ማስተማር በጣም

አስፈላጊ እንደሆነ አጥብቀው ይናገራሉ፡፡ የክፍሉ ተማሪዎችም ቋንቋውን ለመማር ካላቸው ከፍተኛ ፍላጎት አንፃር፣ ከጅምሩ የቋንቋውን ትምህርት ተምረውና አዳብረው አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ባገሪቷ ክልሎች ውስጥ ለመጠቀም መቻል እንደሚገባቸው አስተያየታቸውን አቅርበዋል፡፡

ሰንጠረዥ 14፣ ከቋንቋው መምህራን፣ ከትምህርተ-አርታኢያንና ከርሳነ መምህራን ጥቆማ አንፃር በቋንቋው ትምህርት ዝግጅት ውስጥ በዋናነት እንዲካተቱ የሚፈለጉ ይዘቶች፣

| የፍላጎት ይዘቶች መግለጫ | አስተያየት ሰጪዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | መምህራን | | ትምህር-አርታኢያን | | ርሳነ-መምህራን | |
| | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| የፊደል ገበታ | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| በክፍል ውስጥ፣ በቤት ውስጥና ባካባቢ የሚገኙ በስእል የተደገፉ ስብስብ የቁሳቁሶች ስያሜ/ቃሎችን ገላጭ መጠይቃዊ ቃሎችን ማጥናት | 8 | 100 | 5 | 63 | 8 | 100 |
| አጫጭር ተረቶች | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| በሁለትና በሶስት ሆሄያት የተመሰረቱ ቃሎች ምስረታና ንባብ | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| የሰላምታ ልውውጥ | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| ነገሮችንና ሁኔታዎችን ተመልክቶ መናገር | 8 | 100 | 6 | 75 | 8 | 100 |
| አጫጭር ጭውውት | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| የእጅ ፅህፈት (አጣጣሎች፣ መስመር መጠበቅ፣ አስመስሎ መቅረፅ) | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| በሁለት፣በሶስትና ባራት ቃሎች የተመሰረቱ አረፍተ ነገሮች ማንበብና መፃፍ | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| አጫጭር ጥያቄና መልስ | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| አጫጭር ትእዛዞችን/መመሪያዎችን መከተል | 8 | 100 | 7 | 88 | 8 | 100 |
| መሰረታዊ ያማርኛ ቁጥሮችን መቁጠር<br>• ፩-፱<br>• ፲-፳ | 8 | 100 | 6 | 75 | 8 | 100 |

በሰንጠረዥ አስራ አራት እንደተመላከተው፣ ሁሉም የቋንቋው መምህራን፣ ትምህርተ-አርታኢያንና የርሳነ-መምህራን ያማርኛ የፊደል ገበታ እንደ አንድ የቋንቋው ትምህርት ይዘት በዝግጅቱ ውስጥ እንዲካተት ሀሳብ አቅርበዋል፡፡

ስምንቱ መምህራንና ሁሉም ርሳነ-መምህራን፣ እንዲሁም 63%ቱ ትምህርተ-አርታኢያን በስእሎች የተደገፉ የክፍልና የቤት ውስጥ ብሎም ባካባቢ የሚገኙ ስብስብ ቃላትን የማጥናት አስፈላጊነትን ጠቁመዋል፡፡

ሁሉም መምህራን፣ ትምህርተ-አርታኢያንና ርሳነ-መምህራን በቋንቋው ትምህርት ዝግጅት ውስጥ አጫጭር ተረቶች እንዲካተቱ ጠይቀዋል፡፡

የቋንቋው መምህራን፣ ትምህርተ-አርታኢያንና ርሳነ-መምህራን መቶ በመቶ በሁለትና በሶስት ሆህያት ቃሎችን የመመስረት ትምህርት ልምምድ በተጠናከረ ሁኔታ እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል፡፡

የሰላምታ ልውውጥ በሁሉም ክፍል አስተያየት ሰጪዎች ሙሉ በሙሉ የተጠቆመ ሲሆን፣ ነገሮችንና ሁኔታዎችን ተመልክቶ መናገርን በተመለከተ፣ ስምንቱ መምህራንና ስምንቱ ርሳነ-መምህራን፣ እንዲሁም 75%ቱ ትምህርተ-አርታኢያን የይዘቱን አስፈላጊነት ጠቁመዋል፡፡

አጫጭር ጭውውት የቋንቋውን ተግባቦት-ክሂሎት ለማጎልበት የሚበጅ መሆኑን ሁሉም ባለሙያዎች በተመሳሳይ ደረጃ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

የእጅ ፅህፈት አጣጣሎች፣ በሁለት፣ በሶስትና ባራት ቃላት የተመሰረቱ አረፍተ-ነገሮችን ማንበብ፣ መፃፍ እና አጫጭር ጥያቄና መልስ ለጀማሪ ተማሪዎች ቋንቋውን በመማር-ማስተማር ሂደት ጠቀሜታ ያላቸው ይዘቶች መሆናቸውን ሁሉም የትምህርት ባለሙያዎች ያቀረቡት አስተያየት አስፈላጊነታቸውን መቶ በመቶ ያጠናክረዋል፡፡

ሰንጠረዥ፡ 15፣የንኡስ እርከኑን /4ኛ ክፍል/ ያግርኛ ቋንቋ ትምህርት ለማጠናከር የቋንቋው መምህራን፣ ትምህርተ-እርታኢያንና ርዕሰ-መምህራን ያቀረቡት አስተያየት፤

| ያስተያየት መግለጫ | አስተያየት ሰጪዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | መምህራን | | ትምህርተ-እርታኢያን | | ርዕሰ-መምህራን | |
| | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| የቋንቋውን ትምህርት ይዘቶች በጥናት ላይ ተመስርቶ ከፍላጎት አንፃር ማሻሻል | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| የመማሪያ መፅሀፉን ለተማሪዎች ማቅረብ | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| የቋንቋውን ትምህርት ክፍላተ-ጊዜ መጨመር | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| ለቋንቋው መምህራን በየደረጃው ስልጠና መስጠት | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| የቋንቋውን ትምህርት በሬድዮ መርሀ-ግብር ማጠናከር | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| የትምህርቱን ይዘቶች በተለያዩ ቀለሞች በተሳሉ ስእሎች በማስደገፍ ማቅረብ | 8 | 100 | 6 | 75 | 8 | 100 |
| ሶስቱንም የቋንቋው መማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎች (መርሀ-ትምህርት፣ የተማሪ መፅሀፍና የመምህር መምሪያ) ለቋንቋው መምህራን ማቅረብ | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| የቋንቋውን የመልመጃ ጥያቄዎች ከደረጃው ተማሪዎች ጋር በሚመጥን ሁኔታ ማዘጋጀት | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| የመልመጃ ጥያቄዎችን ሰፋ ማድረግ | 8 | 100 | 0 | 0 | 8 | 100 |
| የቋንቋውን ትምህርት ይዘቶች በቃል መማር ማስተማር ዘዴ በመደጋገም ማቅረብ | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| የቋንቋውን ትምህርት ካንደኛ ክፍል መጀመር | 7 | 88 | 5 | 63 | 6 | 75 |
| የቋንቋውን ትምህርት ከሶስተኛ ክፍል መጀመር | 1 | 13 | 3 | 38 | 2 | 25 |
| በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች መጠቀም | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| የቋንቋ ክፍሉን (ዲፓርትመንት) ማጠናከር | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| የመማሪያ-ማስተማሪያ ክፍሉን ድባብ ማደራጀት | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |

በሰንጠረዥ አስራ አምስት በግልፅ እንደሚታየው፣ የ4ኛ ክፍል ያማርኛ ቋንቋን ትምህርት ለማጠናከርና ውጤታማ ለማድረግ መምህራን፣ ትምህርት-አርታኢያንና ርዳነ-መምህራን ሰፋ ያለ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ የቋንቋውን ትምህርት ይዘቶች በጥናት ላይ ተመስርቶ ማሻሻልና ለተማሪዎች ማቅረብ፣ የክፍለ-ጊዜያቱን መጠን መጨመር፣ ለቋንቋው መምህራን በየደረጃው ስልጠና መስጠት፣ ትምህርቱን በሚዲያ ማጠናከር፣ ወርሃ-ትምህርቱን፣ የተማሪውን መፅሀፍና የመምህሩን መምሪያ ለቋንቋው መምህራን ማቅረብ፣ የትምህርቱን መልመጃዎች ከደረጃው ተማሪዎች አቅም ጋር መመጠን፣ የማስተማር ስነ-ዘዴዎችን ማጠናከር፣ በመርጃ መሳሪያዎች መጠቀም፣ የየትምህርት ቤቱን የቋንቋ ትምህርት ክፍልና የመማሪያ-ማስተማሪያ ክፍሉን ድባብ ማደራጀት እንደሚያሻ ሁሉም ባለሙያዎች መቶ በመቶ በተመሳሳይ ደረጃ አስተያየታቸውን አስፍረዋል፡፡ ለጀማሪ ተማሪዎች የሚዘጋጅ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በስእሎች ተደግፎ መቅረብ እንደሚገባው ሁሉም መምህራንና ርዳነ-መምህራን እንዲሁም 75%ቱ ትምህርተ-አርታኢያን ጥቆማ አድርገዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ 88%ቱ የቋንቋው መምህራን፣ 63%ቱ ትምህርተ- አርታኢያንና 75%ቱ ርዳነ-መምህራን ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት ካንደኛ ክፍል፣ 13%ቱ የቋንቋው መምህራን፣ 38%ቱ ትምህርተ-አርታኢያንና 25%ቱ ርዳነ-መምህራን ደግሞ ከሶስተኛ ክፍል ቢጀመር በማለት ሙያዊ ሀሳብ አቅርበዋል፡፡ አማርኛን በኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትነት ካንደኛ ክፍል መጀመር ያስፈልጋል የሚለው አስተያየት ግን ሚዛን እንደሚደፋ ከመረጃዎቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡

የቋንቋ ትምህርት ዝግጅት በሁለት አበይት ዘርፎች ስር ይደራጃል፡፡ ስለሆነም፣ በቋንቋ ስርአተ-ትምህርት አደረጃጀት ሂደት ቋንቋውን ባገልግሎት ደረጃ የምናውቅበት የጥበብ ዘርፍ (Art Component) እና ስለቋንቋው የምናሳውቅበት የሳይንስ ዘርፍ (Science Component) ትኩረት የምናደርግባቸው ናቸው (Rogers, 1968: 5-6)፡፡

የክልሉ ያራተኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን በኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋነት ለመማር ካላቸው አላማዎችና ከትምህርቱ ይዘቶች ፍላጎት አንፃር፣ የቋንቋው መምህራን፣ ትምህርተ-አርታኢያንና ርዳነ-መምህራን ካላቸው ችሎታና ልምድ አስተያየት አቅርበዋል፡፡ ለደረጃው ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር-ማስተማር የጠቀሙትን ይዘቶች በክሂል ደረጃ ፈርጆ ማመላከቱ ለቋንቋው ስርአተ-ትምህርት አዘጋጅ ክፍል ፍንጭ መስጠት ወይም የሙያ ድጋፍ ማድረግ ነው፡፡

በሰንጠረዥ አስራ አራት በዝርዝር እንደተመላከተው፣ ለአራተኛ ክፍል ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት አስራ ሁለት የፍላጎት ይዘቶች ተጠቁመዋል፡፡ ስለሆነም፣ ከስርአተ ትምህርት አደረጃጀት ሂደትና ከአጥኚው የሙያ ልምድ አንፃር፣ ይዘቶች በሚከተሉት የክሂሎት ደረጃና የቃላት ጥናት አኳያ ተፈርጀው ቀርበዋል፡፡ ይህን ማድረግ ማለት ግን ከላይ ለማስገንዘብ እንደተሞከረው፣ ለስርአተ-ትምህርቱ አዘገጃጀት በዝርዝር ይዘተ-ሰንጠረዥ (flow chart) ውስጥ የይዘቶችን አደራደር ለማመቻቸት እንጂ በመማር-ማስተማሩ ሂደት አንድ ይዘት አንድ ክሂልን ወይም ውስን ክሂሎትን ብቻ ለማዳበር ይረዳል ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ ባብዛኛው በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ሂደት አራቱ ተግባቦተ-ክሂሎት (ማዳመጥ፣ መናገር! ማንበብና መፃፍ) በተቀናጀ መልክ የሚተገበሩ ሆነው እናገኛቸዋለንና ነው፡፡

**ሰንጠረዥ፡ 16፣ ለኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ (አማርኛ) ትምህርት የተጠቆሙ ይዘቶች በክሂል ደረጃ፣**

| የትምህርት ዘርፍ | ክሂል | የፍላጎት ይዘት |
|---|---|---|
| የቋንቋ ጥበብ | ማዳመጥ | - ልዩ ልዩ ድምፆችን ማዳመጥ<br>- የፊደሎችን ድምፆች ማዳመጥ<br>- መሠረታዊ ያማርኛ አሀዞችን ማዳመጥ<br>- ቃላትን፣ ሀረጋትንና አረፍተ-ነገራትን ማዳመጥ<br>- አጫጭር ጭውውቶችን ማዳመጥ<br>- የመምህራንን ገለፃና አጫጭር ትእዛዞች ማዳመጥ |
| የቋንቋ ጥበብ | መናገር | - የቋንቋውን የፊደል ገበታ መለየት<br>- ሰላምታ ልውውጥ<br>- አጫጭር ጥያቄና መልስ<br>- ነገሮችንና ሁኔታዎችን ተመልክቶ/አስተውሎ መናገር<br>- መሰረታዊ ያማርኛ አሀዞችን መናገር<br>- አጫጭር መመሪያዎችን ተገንዝቦ መናገር<br>- አጫጭር ጭውውቶችን ማድረግ<br>- አጫጭር ተረቶችን መናገር |
| የቋንቋ ጥበብ | ማንበብ | - የፊደል ገበታ/ የተደመጠንና የታየን ሆሄ/ ማንበብ<br>- መሠረታዊ ያማርኛ አሀዞችን ማንበብ<br>- በሁለትና በሶስት ሆሄያት የተመሰረቱ ቃላትን ማንበብ<br>- በሁለት፣ በሶስትና ባራት ቃላት የተመሰረቱ አረፍተ-ነገራትን ማንበብ<br>- በስእሎች የተደገፉ ቃላትን መለየት<br>- አጫጭር መመሪያዎችን ማንበብ |

| የትምህርት ዘርፍ | ክሂል | የፍላጎት ይዘት |
|---|---|---|
| የቋንቋ ሳይንስ | መፃፍ | - የእጅ ፅህፈት አጣጣል<br>. ቁም ሰረዝ ( / )<br>. ጎናዊ ሰረዝ ( - )<br>. ግራ ቅንፍ ( ⊂ )<br>. ቀኝ ቅንፍ ( ⊃ )<br>. ቀለበት ( ○ )<br>- የፊደል ገበታ/ የተደመጠንና የታየን ሆሄ/ መፃፍ<br>- መሠረታዊ ያማርኛ አህሎችን መፃፍ<br>- በሁለትና በሶስት ሆህያት ቃላትን መመስረት<br>- በሁለት፣ በሶስትና ባራት ቃላት የመተሰረቱ አረፍተ-ነገራትን መገልበጥ |
| መሰረታዊ መደበለ-ቃላት<br>/Basic stock of words/ | | - የክፍል ውስጥ ቁሳቁሶች ስያሜ ስብስቦች<br>- የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ስያሜ ስብስቦች<br>- ያካባቢ ቁሳቁሶችና ነገሮች ስያሜ ስብስቦች<br>- ገላጮች<br>- መጠይቃዊ ቃላት |

# 5.0 ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

አማርኛ የልዩ ልዩ ብሄር/ ብሄረሰቦች የጋራ መግባቢያ ቋንቋ/Language of wider communication/ ሆኖ እንዲያገለግል ሰኔ 1983* የፀደቀው ቻርተር ሲያመላክት፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረግ ግንኙነትም ሆነ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ይሰጣል ይላል/ኢ.ት.ፖ. 1986*፡ 13/፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ልሳነ-ብዙ አገሮች ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ሌላ ቢያንስ አንድ ተጨማሪ ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋን ማወቅ/መማር ጠቀሜታ አለው፡፡ ምክንያቱም፤

- ብሄር/ ብሄረሰቦችን የቋንቋ ጉዳይ ሳያግዳቸው በየትኛውም ክልል ሰርተው መኖር ይችላሉ፡፡
- በሁለንተናዊ ዘርፍ መቀራረብ ይጠናከራል፤ ያካባቢን ተፈጥሯዊ ሀብትም በጋራ ተሳስቦ መጠቀም ይቻላል፡፡
- ከልሳነ-ዋህድነት ያላቅቃል፡፡
- ባህለ-ክልኤነትን ያዳብራል፡፡
- ያንድነትን ስሜት ያጎለብታል፡፡

ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት በትምህርት አይነትነት በመጀመሪያው ንኡስ እርከን ከሶስተኛ ክፍል ጀምሮ በተጠናከረ መንገድ እንዲሰጥ የትምህርት ፖሊሲው ያፈፃፀም ስልት መርሀ-ግብር ያስገነዝባል፡፡ የዚህ እርከን ትምህርት ያመለካከት ቀረፃ፣ መሰረታዊ ትምህርት ማቅሰሚያና ለቀጣዩ ሁለተኛ እርከን መሰረት መጣያ ነው፡፡

> የአንድ አገር የትምህርት ጥራት ከስርአተ-ትምህርት በማመንጭ ይዘትና በመምህራን ጥራት ይንፀባረቃል፡፡ ስለሆነም የስርተአ-ትምህርት ይዘት የዚያን ያንድ የተለየ ማህበረሰብ፣ህብረተሰብ ወይም ብሄር ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ባህላዊና ምጣኔያዊ ሀብት ፍላጎቶችና አላማ ዎች ማንፀባረቅ አለበት፡፡ በተጨማሪም፣ የስርአተ-ትም ህርት መሳሪያዎች/መፃህፍት/ ሁሉ ከመርሀ-ትምህርቱ ጋር ያላቸውን ተገቢነትና መጣጣም በሚያረጋግጥ መልክ በጥንቃቄ መዘጋጀት አለባቸው[10] / UNECA 1993: 27 /፡፡

ስለዚህ፣ የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋን ትምህርት ይዘቶች /contents/ አመራረጥና አደረጃጀት ከደረጃው ተማሪዎች ሁለንተናዊ እድገት አንፃር/አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ማህበራዊና

ስሚታዊ/ ብሎም ከእርከኑ ተማሪዎች የባህርይ ገፅታ/Students profiles/ አኳያ፣ ትምህርቱ ተፈላጊውን የባህርይ ለውጥ/የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታ እንዲያስገኝ ዝግጅቱን ማጠናከር ያሻል፡፡

በዚህ መሰረት፣ ትግርኛ የእፍ መፍቻቸው ለሆነ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ /አማርኛ/ ትምህርት ይዘት ትንተና ከመስክ የተገኙ መረጃዎችንና የቋንቋውን መማሪያ መፅሀፍ አዘገጃጀት በመገምገም የጥናቱ ውጤት እንደሚከተለው ተጠቃልሏል፡፡

የትምህርቱ ይዘቶች አመራረጥ የክፍሉን ተማሪዎች የመማር ፍላጎት ከማሟላትና ከአካባቢያዊ ህይወታቸው ጋር ከማዛመድ አንፃር ሲታይ፣ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የይዘቶቹ ቅንብር የቋንቋውን ተግባቦተ-ክሂሎት ከማጎልበት አኳያ፣ በማዳመጥ ደረጃ ሻል ያሉ ቢሆንም የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎትን ለማዳበር ያላቸው ብቃት ዝቅተኛ መሆኑን ከጥናቱ ውጤት ለመገንዘብ ይቻላል (ሰንጠረዥ፣ 6)፡፡

በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች አደራረስ ቅደም ተከተል ስናጤን ትምህርቱ በሞክሼ ሆሄያት ይጀምራል፡፡ ቀጥሎም በሶስት ንጥረ-ድምፆች የተመሰረቱ ቃሎችን በማስቀደም በሁለት ንጥረ-ድምፆች የተመሰረቱ ቃላትን አስከትሎ "አጥና" ይላል፡፡ ከዚያም ወደ ዲቃላ ሆሄያት ሽግግር ተደርጓል፡፡ ይህም የትምህርቱ ይዘቶች ከውስብስብነት ደረጃ የመነሳታቸውን ባህርይ ያሳያል፡፡ ባጠቃላይ የይዘቶቹ ቅደም ተከተል የቋንቋውን ትምህርት ጀማሪ ለሆኑ ተማሪዎች አጥጋቢ አለመሆኑን ጥናቱ ያስረዳል (ሰንጠረዥ፣ 7)፡፡

የመማሪያ መፅሀፉ አዘገጃጀት የተማሪዎችን እውቀት፣ ክሂሎትና አማለካከት ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይጠበቅበታል፡፡ የክፍሉ ተማሪዎች መሰረታዊ የቋንቋውን የፊደል ገበታ ባላጣሩበትና የሆሄያቱን ቅርፅና ድምፅ በተጠናከረ መንገድ ባልተለማመዱበት ሁኔታ ከችሎታቸው በላይ በሆኑ አስራ አንድ ምንባቦች መሳሪያነት አራቱን ተግባቦተ-ክሂሎት /ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ/ ያዳብራሉ ማለት ያስቸግራል፡፡

በመፅሀፉ ውስጥ ላመቱ የተካተቱት የቋንቋው ትምህርት ይዘቶች መጠንና የክልሉ ትምህርት ክፍል ለቋንቋው ትምህርት በሳምንት የመደበለት የሁለት ክፍለ-ጊዜያት ስርጭት አይመጣጠንም፡፡ ይህም ይዘቶቹን በአመቱ የትምህርት ቀናት ውስጥ ለማጠናቀቅ እንደሚያስቸግር የጥናቱ ውጤት ይጠቁማል፡፡ Education and Training Program : Including period Allotment and Contents Selection Criteria (1994:8) አንፃር፣ ለቋንቋው ትምህርት የተመደበለት የክፍለ-ጊዜያት መጠን በሳምንት ስድስት ነው፡፡

ምድረ-በዳ፣ ዳመናው ከብዷል፤ ማለፊያ ጫማ ተጫምታለች፤ አይኗን ተኳኩላለች፣ ወዘተ. በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ከተካተቱት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ባብዛኛው የትምህርቱ ቋንቋ አጠቃቀም ለክፍሉ ተማሪዎች አይመጥንም፡፡ በረጃጅም አረፍተ-ነገራት (ድርብና ድብልቅ) የታጨቁ፣ በአራት፣ በአምስትና በሰባት አንቀፆች ጥቅጥቅ ያሉና ኪናዊ ውበትን ያልተላበሱ ደረቅ ምንባቦች ቀርበዋል፡፡ ይህንንም ከቀረበው ግምገማና መረጃዎች ይረዷል፡፡ ስለሆነም፣ ገና በሰስትና በአራት ቃላት የተመሰረቱ አረፍተ-ነገራትን በውል አዳምጠው መናገርና ማንበብ መልሰውም ለሌላው ለመናገር ከሂላቸውን ላላጎለበቱ ተማሪዎች ምንባቦቹ ይከብዳሉ፡፡ ከነዚህ ሁሉ ጋር ቋንቋውን ለሚያስተምሩ መምህራን ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋን ለማስተማር የሚረዳ ተጨማሪ ስልጠና እንዳልተሰጣቸው መረጃዎቹ ይጠቁማሉ፡፡

ለጀማሪ ተማሪዎች የቋንቋውን ይዘቶች በትኩረት አጢኖ ለመማር የፊደሎች መጠን አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ ዳሩ ግን፣ የየምእራፉና የየርእሱ ፊደሎች ጉልህነት መጠን ከሌሎቹ ጽሁፎች ማለትም ቃላትና አረፍተ-ነገራት ፊደሎች መጠን ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ይገኛል፡፡ ባጠቃላይ የቋንቋው ትምህርት ዝግጅት ፊደሎች መጠን ለደረጃው ዝቅተኛ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡

የቋንቋው መማሪያ መፅሀፍ ሳይሆን በብዜት መልክ የቀረበ ጥራዝ ነው፡፡ ሽፋኑና አጠራረዙ ተራ መሆኑን፣ በፊት ለፊት ሽፋኑ ላይ ምንም አይነት ስእል (ዲዛይን) እንደሌለውና በዚህ እድሜና ንቃት ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች መስህብነት እንደሌለው የጥናቱ ውጤት ያረጋግጣል፡፡

## 5.2 አስተያየት

ጥናቱ ያመላከታቸውን አሉታዊ ጎኖች ለማሻሻል የተጠቆሙ አበይት አስተያየቶች፤

ሀ - የቋንቋው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ ከክፍሉ ተማሪዎች እድሜ፣ ብስለት፣ የባህርይ ገፅታ፣ አካባቢያዊ ጭብጦችና ፍላጎት አንፃር በጥናት ላይ ተመርኩዞ ቢቀርብ፣

ለ - የትምህርቱ ይዘቶች ቅንብር ከኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አላማዎች፣ከስርአተ-ትምህርት አዘገጃጀት ሂደትና፣ ካገሪቱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ያፈነፀም ስልት መርሀ-ግብር አኳያ ቢመቻች፣

ሐ - የይዘቶች አደራረስ ከስነ-ትምህርትና ከስርአተ-ትምህርት አዘገጃጀት ሂደት መርህ የክፍሉን ተማሪዎች አእምሮ እየኮረኮረ የአይረሴነትን ስሜት ለመፍጠር በሚያስችል መልክ በቀለማት በተዋቡ ስእሎች፣ በበቂ ምሳሌዎችና መግለጫዎች በአጥጋቢ ሁኔታ ቢዘጋጅ፣

መ - የቋንቋውን ትምህርት አላማዎች ግብ ለማድረስ የተመረጡት ይዘቶች በመልመጃ ዎች መሳሪያነት የሚተገበሩ ስለሆነ፣ ከየምእራፉ ትምህርት በኋላ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ትኩረት መሰጠት ያሻል፡፡ መልመጃዎች ከስነ-ትምህርትና ለመማር-ማስተማር ሂደት ካላቸው አመቺነት አኳያ በሶስት ደረጃዎች ተፈርጀው ግንዛቤን ለማስፋት፣ ክሂሎትን ለማዳበርና ጠንካራ ባህርይን ለማጎልበት የሚያስችሉ እንዲሆኑ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ጥያቄዎቹ ከክፍሉ ተማሪዎች ችሎታ፣ክፍለ-ጊዜያት ስርጭት ከመምህራን ብቃት፣ከመማሪያ መፃህፍትና ከመርጃ መሳሪያዎች ወዘተ. አቅርቦት አንፃር ተጣጥመው ቢዘጋጁ፣

ሠ - የመማሪያ-ማስተማሪያ መፅሀፍ ዝግጅት በደራሲው ወይም በአዘጋጁ ክፍል፣ በአርታ ኢያኑ፣ በሰአልያኑና በአሳታሚው ምክክር ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል / Margaret 1988/፡፡ ስለዚህ የቋንቋው መማሪያ መፅሀፍ ዝግጅት የህትመት መርህንና የስርአተ-ትምህርት አዘገጃጀት ሂደትን ጠብቆ ጥራትና ብቃት ባለው ሁኔታ ቢሻሻል፣

ረ - ቋንቋን ለመማር ማስተማር በሚደረግ ዝግጅት ለዓላማዎች መረጣና ለይዘቶች አደረ ጃጀት የሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆች፣ የቋንቋ መምህራንና አግባብነት ያላቸው የማ ህበረሰቡ አባላት ቅንጅታዊ አሰራር ጠቀሜታ ስላለው በተጠናከረ ሁኔታ ትኩረት ቢሰጠው /ለዝርዝሩ አባሪ አራት ይመለከቷል/፡፡

## መረጃ ጽሑፎች (Bibliography)

Ary, Donald. 1990. Introduction to Research in Education. 4th ed. Florida: Holt, Rinehart and winston, Inc.

Bender. 1976. Language in Ethiopia. London: OUP.

Brewster, E and Elizabeth, B. 1982. Language Acquisition Made Practical 4th ed.California: SIL.

Brown, H. Douglas, 1995. Principles of Language Learning and Teaching .3rd ed. New Jersy: Prentice Hall.

Celce - Murcia, Mariame. 1979. Teaching English as a Second of Foreign Language. California: Univ. of California.

Chaudron, Craig. 1990. Second Language Classroom. 3rd ed. Cambridge: CUP.

Davis, M. Patrice. 1992 . "Teaching Second Language Communicatively." A Handbook for Bilingual Education .Vol. II, ICDR.

Dubin, Fraida and Elite, Olshtain. 1992. Course Design: Developing Programs and Materials for Language Learning. 6th ed. Cambridge: CUP.

Dunkin, Michael J. ed. 1987. The International Encyclopedia of Teaching and Teacher Education. Oxford: Pergoman Books Ltd.

Ellington, Henry and Race, Phil. 1985. Producing Teaching Materials: A Handbook for Teachers and Trainers. 2nd ed. London: Kogan Page Limited.

Finocchiaro, M. 1973. The Foreign Language Learner: A Guide for Teachers. NewYork: Regents Publishing Company. Inc.

Gebre Medhine, Kidane. 1981*. የኢትዮጵያ ትምህርት መስፋፋትና እድገት ከ1934 - 80። አዲስ አበባ፣ ት/ሚ.

Genesee, Fred . 1994. Educating Second Language Children: The Whole Child, the Whole Curiculum, the Whole Community. Cambridge: CUP.

Grimes, Barbara. 1992. Ethnologue: Language of the World. 12th ed. Dallas: SIL.

Halliday, M. 1964. The Linguistic Sciences and Language Teaching . Indiana: Univ. of Indiana.

ICDR. 1997. Formative Evaluation of the Tryout Project of the New Curriculum Materials: Content Analysis. Addis Ababa: CEERC

__________ . 1985*. የአማርኛ ቋንቋ ሲሰበስ ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች። አዲስ አበባ፣ ትመማማድ.

Jon, Nixon. 1992. Evaluating Whole Curriculum. Philadelphia: Open University Press.

Koul, Lonesh. 1988. Methodology of Educational Research. 2nd ed. New Delhi: Vicas Publication House, Ltd.

Krashen, SD. 1989. Language Acquistion and Language Education Extensions and Applications. London: Prentice Hall Int. Ltd.

Lado, Robert. 1964. Language Teaching Ascientific Approach. NewYork: McGraw-Hll, Inc.

Little Wood, W. 1994. Foreign and Second Language Learning. 10th ed. Cambridge: CUP.

Margaret R., Marshall. 1988. An Introduction to the World of Children's Books. 2nd ed. England: Aldershot, Hants.

Marland, M. 1989. Language Across the Curriculum. Oxford: Heineman.

Marx and Engels. 1970. "The Part played by Labour in The Transition From Ape To Man" Selected Works. Moscow: Volume 3, Progress Publishers.

McArthur, Tom. 1984. A Foundation Course for Language Teachers. Cambridge: CUP.

McNab, Christine. 1989. "Language Policy and Language Practice. Implementation Dilemas in Ethiopian Education." Ph.D. Dissertation, Stockholm: Stockholm Univ.

MOE. 1994. Ethiopian Education and Training Policy Implementation Strategy. Addis Ababa: ICDR.

________ 1994. Education and Training Program: Including Period Allotment and Contents Selection Criteria. Addis Ababa: ICDR.

________ 1996. Annual Education Statistics. Addis Ababa: EMPDA.

________ 1986. The Evaluation Research on the General Education System of Ethiopia (Ergese). Addis Ababa: EMPDA.

Murphy, Patricia and Moon, Bob. 1989. Development in Learning and Assessment. London: Open University.

Nunan, D. 1988. The Learner-Ceatred Curriculum. Oxford: Heineman.

Pankhurst, Sylvia. 1955. Ethiopia: A cultural History London: Fletcher & Son Ltd.

Prabu, N.S. 1987. Second Language Pedagogy. Oxford: OUP.

Rogers, Mary. 1968. New Design in the teaching of English. London: International Textbook Company.

Rubagumay, C.M. 1990. Language in Education in Africa. Clevedon: Multilingual Matters Ltd.

Stern, H.H. 1991. Fundamental Concepts of Language Teaching. 7th ed. Oxford: OUP.

# አባሪዎች፣

# አባሪ አንድ

መሳ.፬1

**በትግራይ ክልላዊ መስተዳድር ባንደኛ እርከን፣ በመጀመሪያው ንኡስ እርከን /4ኛ ክፍል/ አማርኛ ቋንቋን በሚያስተምሩ መምህራን የሚሞላ መጠይቅ!**

አላማ፣

. የዚህ መጠይቅ አላማ በትግራይ ክላላዊ መስተዳድር አማርኛን በኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋነት ለሚማሩ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው መጽሐፍ ያካተታቸውን ይዘቶች ከቋንቋ ትምህርት ትወራ፣ ከስነ-ትምህርት ከስርአተ-ትምህርት አዘገጃጀት መርሆዎችና ከትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ አንፃር ከመስከ የተገኙ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማጠናቀርና በመተንተን ለክልሉ የቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆች የሙያ እገዛ ማድረግ ነው፡፡

ለመልካም ትብብርዎ ከልብ እናመሰግናለን!

መመሪያ፣

የትምህርት ጉዳይ የጋራ ነው፡፡ ይህንኑ በመገንዘብ በቀና አመለካከት ሙያዊ ኃላፊነትዎን ይወጡ ዘንድ ትክክለኛ መልስዎንና አስተያየትዎን እንዲሰጡን በትህትና እንጠይቃለን፡፡

ይህ መጠይቅ ሃያ ስምንት ዝግና አምስት ክፍት መሰረታዊ ጥያቄዎችን አካትቷል፡፡

ስለዚህ፤

. ለያንዳንዱ ዝግ ጥያቄ አማራጭ መልሶች ተሰጥተዋል፡፡ ላማራጭ መልሶቹ አራት ማዕዘን ያላቸው የመልስ መጠቆሚያ ሣጥኖች ተዘጋጅተዋል፡፡ ለያንዳንዱ ጥያቄ የሚመርጡትን መልስ ለመልሱ በተዘጋጀው ቦታ የ /× / ምልክት በማድረግ ይጠቁሙ፡፡

. ክፍት የሆኑት ጥያቄዎች ነፃ አስተያየትን የሚሹ ስለሆኑ፣ በጥያቄዎቹ መሰረት በተሰጡት ክፍት መስመሮች ላይ መልስዎን ይፃፉ፡፡

ጥር 1989 ዓ.ም.

## ክፍል አንድ፣

### ስለ መምህሩ/ሯ አጠቃላይ መረጃ፤

1.0 ጾታ፣ ወንድ ☐ ሴት ☐

2.0 እድሜ ______

3.0 የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም ______________

4.0 ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት

4.1 ዞብ ______________

4.2 ወረዳ ______________

4.3 ከተማ ______________

4.4 አካባቢ

4.4.1 ከተማ ☐

4.4.2 ገጠር ☐

5.0 የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃና ምድብ ______________

6.0 አፍ መፍቻ ቋንቋዎ የትኛው ነው ?

6.1 ትግርኛ ☐

6.2 አማርኛ ☐

6.3 ሌላ ☐ ሌላ ከሆነ ምን ? ______________

7.0 ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ ያውቃሉ ? ☐ የሚያውቁ ከሆነ ምን ?______

8.0 የትምህርት ደረጃ

8.1 12ኛ ክፍል ☐

8.2 12 ክፍል + 1 ☐

8.3 12ኛ ክፍል + 2 ☐

8.4 የኮሌጅ ዲፕሎማ ☐

9.0 ባማርኛ ቋንቋ በመምህርነት የቆዩበት ያገለግሎት ዘመን ባመት

9.1 ከ1.5 ☐

9.2 ከ6.10 ☐

9.3 ከ11 በላይ ☐

10.0 መምህር/ት ለመሆን ያለፉበት የስልጠና ደረጃ

- 10.1 በቀጥታ ቅጥር/ያለምንም ስልጠና ☐
- 10.2 በመደበኛ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም መርሀ-ግብር ☐
- 10.3 ባጭር ጊዜ የመምህርነት ስልጠና ☐
- 10.4 በመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ዲፕሎማ መርሀ-ግብር ☐

11.0 አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር በሚረዱ ተጨማሪ ኮርስ ወይም ስልጠና

- 11.1 ተሰጥቶኛል ☐
- 11.2 አልተሰጠኝም ☐

## <u>ክፍል ሁለት፣</u>

### <u>ስለ አራተኛ ክፍል ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት መረጃ፣</u>

12.0 ስለ ትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ

- 12.1 መጠነኛ ግንዛቤ አለኝ ☐
- 12.2 የተሟላ ግንዛቤ አለኝ ☐
- 12.3 ግንዛቤ የለኝም ☐

13.0 የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች ያማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

- 13.1 አላቸው ☐
- 13.2 የላቸውም ☐

14.0 በተ.ቁ. "13" ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "13.1" ከሆነ አንድ መጽሐፍ ለስንት ?

- 14.1 አንድ መጽሐፍ በነፍስ ወከፍ ☐
- 14.2 አንድ መጽሐፍ ለሁለት ተማሪዎች ☐
- 14.3 አንድ መጽሐፍ ለሶስት ተማሪዎች ☐
- 14.4 አንድ መጽሐፍ ለአራት ተማሪዎች ☐

15.0 የክፍሉ ተማሪዎች በየትኛው የቋንቋ ክሂል ችግር አለባቸው ? (መልሱ ካንድ በላይ ሊሆን ይችላል፡፡)

- 15.1 ማዳመጥ ☐
- 15.2 መናገር ☐
- 15.3 ማንበብ ☐
- 15.4 መፃፍ ☐

16.0 ተማሪዎችዎ አማርኛ ቋንቋን ሲማሩ በየትኛው የትምህርቱ ዋህድ/ዘርፍ ችግር አለባቸው ? (መልሱ ካንድ በላይ ሊሆን ይችላል።)

16.1 የንጥረ ድምፅ /የፊደሎች አጠራር ☐

16.2 የቃል ምስረታ ☐

16.3 ያረፍተ-ነገር አሰካክ ☐

16.4 የምንባቦችን ፅንሰ-ሀሳብ መረዳት ☐

17.0 በክልሉ ውስጥ ባማርኛ ቋንቋ ስርአተ ትምህርት ዝግጅት መርሀ-ግብር ተግትፈው ያውቃሉ ?

17.1 አዎን፣ ተግትፈያለሁ ☐

17.2 የለም፣ አልተሳተፍኩም ☐

18.0 ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በተጨማሪ ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት በክልሉ መሰጠት ምን ያህል ያስፈልጋል?

18.1 በጣም ☐

18.2 በመጠኑ ☐

18.3 አያስፈልግም ☐

19.0 የክፍሉ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ፍላጎታቸው

19.1 ከፍተኛ ነው ☐

19.2 መጠነኛ ነው ☐

19.3 ዝቅተኛ ነው ☐

19.4 አይፈልጉም ☐

20. ወላጆች ልጆቻቸው አማርኛ ቋንቋን እንዲማሩ ያላቸው ፍላጎት

20.1 ከፍተኛ ነው ☐

20.2 መጠነኛ ነው ☐

20.3 ዝቀትኛ ነው ☐

20.4 አይፈልጉም ☐

ከዚህ በታች በዝርዝር የተመላከቱትን አስተያየቶች መሰረት በማድረግ ስለ እያንዳንዱ አስተያየት በሰንጠረዡ ውስጥ ከተጠቀሙት ደረጃዎች አንዱን በመምረጥ ደረጃ ይስጡ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5. | በጣም ከፍተኛ | 2. | ዝቅተኛ |
| 4. | ከፍተኛ | 1. | በጣም ዝቅተኛ |
| 3. | መካከለኛ | 0. | አስተያየት መስጠት አልችልም |

መሳሪያ1

| ተራ ቁ. | አስተያየቶች | ደረጃ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 21 | ለክፍሉ የተዘጋጀው የቋንቋው መማሪያ መጽሐፍ ይዘቶች መሰረት ያደረጉት የክፍሉን መርሀ-ትምህርት ነው | | | | | | |
| 22 | ከይዘት ገፅታ አንፃር፡ የቋንቋው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ | | | | | | |
| | 22.1 ለደረጃው የተቀረፁት የቋንቋው ትምህርት አላማዎች ይዘቶቹ ጋር ይዛመዳሉ | | | | | | |
| | 22.2 ይዘቶቹ ለተማሪዎች ይመጥናሉ/ይስማማሉ | | | | | | |
| | 22.3 ይዘቶቹ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ያሟላሉ | | | | | | |
| | 22.4 ይዘቶቹ ከአካባቢው ሁኔታዎች ጋር የተዛመዱ ናቸው | | | | | | |
| | 22.5 የትምህርቱ ይዘቶች ወቅታዊነት አላቸው | | | | | | |
| 23 | የቋንቋው ትምህርት ይዘቶች ቅንብር | | | | | | |
| | 23.1 ይዘቶቹ የማዳመጥ ክሂልን ያዳብራሉ | | | | | | |
| | 23.2 ይዘቶቹ የመናገር ክሂልን ያዳብራሉ | | | | | | |
| | 23.3 ይዘቶቹ የማንበብ ክሂልን ያዳብራሉ | | | | | | |
| | 23.4 ይዘቶቹ የመፃፍ ክሂልን ያዳብራሉ | | | | | | |
| | 2.3.5 ይዘቶቹና ያመቱ ክፍለ-ጊዜያት ይመጣጠናሉ | | | | | | |
| 24 | የቋንቋው ትምህርት ይዘቶች አደራረስ | | | | | | |
| | 24.1 ይዘቶቹ ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ ናቸው | | | | | | |
| | 24.2 ወጥነት አላቸው | | | | | | |
| 25 | ከአቀራረብ ገፅታ አንፃር፡ የቋንቋው ትምህርት መልመጃዎች | | | | | | |
| | 25.1 አይነታቸው የተለያየ ነው | | | | | | |
| | 25.2 በበቂ መጠን ቀርበዋል | | | | | | |
| | 25.3 የደረጃውን ተማሪዎች ያመራምራሉ | | | | | | |
| | 2.5.4 ተግባራዊ የሚሆኑ ናቸው | | | | | | |
| | 25.5 መመሪያዎቹ/ትእዛዞች ግልፅ ናቸው | | | | | | |
| 26 | የቋንቋው ትምህርት ምሳሌዎች/ ስእላዊ መግለጫዎች | | | | | | |

| ተራ ቁ. | አስተያየቶች | ደረጃ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| | አቀራረብ | | | | | | |
| | 26.1 ግልፅነት አላቸው | | | | | | |
| | 26.2 ከያንዳንዱ ርእሰ ትምህርት ጋር ተገቢነት አላቸው | | | | | | |
| | 26.3 ደስ ያሰኛሉ/ይማርካሉ | | | | | | |
| 2.7 | የቋንቋ አቀራረብ | | | | | | |
| | 27.1 የቃሎቹ ደረጃ ለክፍሉ ተማሪዎች ትክክለኛነት አላቸው | | | | | | |
| | 27.2 አረፍተ-ነገሮቹ ግልፅ ናቸው | | | | | | |
| | 27.3 ምንባቦቹ ተነባቢነት አላቸው | | | | | | |
| 2.8 | የቋንቋው መማሪያ መጽሐፍ የሕትመት ዝግጅት | | | | | | |
| | 28.1 የፊደሎቹ መጠን ተገቢ ነው | | | | | | |
| | 28.2 የመፅሀፉ ወረቀት ጥራት አለው | | | | | | |
| | 28.3 መፅሀፉ ላያያዝ ያመቻል | | | | | | |
| | 28.4 አጠራረዙ መልካም ነው | | | | | | |
| | 28.5 መጽሐፉ ሽፋን፣ ስእል/ዲዛይን አለው | | | | | | |

## ክፍል ሦስት

## ለክፍሉ ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት የይዘት ጥቆማ፤

29. የክፍሉ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ሲማሩ ከትግርኛ ቋንቋ ጋር እየተምታቱ የሚያስቸግራቸውን ንጥረ ድምጾች/ፊደሎች/ ከዚህ በታች ይዘርዝሩ

________________________________________
________________________________________
________________________________________
________________________________________
________________________________________

30. የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን ለምን አላማዎች ይማሩ ?

________________________________________
________________________________________
________________________________________
________________________________________

31. ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምን ምን ይዘቶች ይቅረቡ ?

32. የአራተኛ ክፍል ያማርኛ ቋንቋን ትምህርት የተጠናከረና ውጤታማ ለማድረግ ምን መደረግ አለበት ?

33. ተጨማሪ አስተያየት ካለዎት እባክዎን ከዚህ በታች ሃሣብዎን ይግለጹ፡፡

# አባሪ ሁለት

መሳ.02

## በትግራይ ክልላዊ መስተዳድር በሚገኙ የትምህርት ባለሙያዎች/ርእሳነ-መምህራንና ትምህርተ እርትእያን/ የሚሞላ መጠይቅ፣

አላማ፡

የዚህ መጠይቅ አላማ በትግራይ ክልላዊ መስተዳድር አማርኛን በአ-አፍ መፍቻ ቋንቋነት ለሚማሩ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው መጽሀፍ ያካተቷቸውን ይዘቶች ከቋንቋ ትምህርት ትወራ፣ ከስነ-ትምህርት፣ ከስርአተ-ትምህርት አዘገጃጀት መርሆዎችና ከትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ አንፃር ከመስክ የተገኙ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣በማጠናቀርና በመተንተን ለክልሉ የቋንቋው ሥርዓተ-ትምህርት አዘጋጆች የሙያ እገዛ ማድረግ ነው፡፡

ለመልካም ትብብርዎ ከልብ እናመሰግናለን

መመሪያ፣

የትምህርት ጉዳይ የጋራ ነው፡፡ ይህንኑ በመገንዘብ በቀና አመለካከት ሙያዊ ኃላፊነትዎን ይወጡ ዘንድ ትክክለኛ መልስዎንና አስተያየትዎን እንዲሰጡን በትህትና እንጠይቃለን፡፡

ይህ መጠይቅ ሃያ አንድ ዝግና አራት ክፍት መሰረታዊ ጥያቄዎችን አካትቷል፡፡ ስለዚህ፤

- ለያንዳንዱ ዝግ ጥያቄ አማራጭ መልሶች ተሰጥተዋል፡፡ ላማራጭ መልሶቹ አራት ማዕዘን ያላቸው የመልስ መጠቆሚያ ሣጥኖች ተዘጋጅተዋል፡፡ ለያንዳንዱ ጥያቄ የሚመርጡትን መልስ ለመልሱ በተዘጋጀው ቦታ የ /×/ ምልክት ለማድረግ ይጠቁሙ፡፡

- ክፍት የሆኑት ጥያቄዎች ነፃ አስተያየትን የሚሹ ስለሆኑ፣ በጥያቄዎች መሰረት በተሰጡት ክፍት መስመሮች ላይ መልስዎን ይፃፉ፡፡

ጥር 1989 ዓ.ም.

መሳ.02

## ክፍል አንድ፤

## ስለ ርእሰ-መምህሩ/ሯ ወይም ትምህርተ-እርትእይ

## አጠቃላይ መረጃ፤

1.0 ጾታ፣ ወንድ □ ሴት □

2.0 እድሜ ______

3.0 አድራሻ

3.1 ዞባ □

3.2 ወረዳ □

3.3 ከተማ □

4.0 አፍ መፍቻ ቋንቋዎ የትኛው ነው ?

4.1 ትግርኛ □

4.2 አማርኛ □

4.3 ሌላ □ ሌላ ከሆነ ምን ? ______

5.0 ኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ ያውቃሉ ? የሚያውቁ ከሆነ ምን? ______

6.0 የትምህርት ደረጃ

6.1 12ኛ ክፍል + 1 □

6.2 12ኛ ክፍል + 2 □

6.3 የመለስተኛ ኮሌጅ ዲፕሎማ □

6.4 የመጀመሪያ ዲግሪ □

7.0 ያገልግሎት ዘመን ባመት

7. ከ1.5 □

7.2 ከ6.10 □

7.3 ከ11 በላይ □

8.0 የሰለጠኑበት የሙያ ዘርፍ (መልሱ ካንድ በላይ ሊሆን ይችላሉ።)

8.1 በመምህርነት □

8.2 በርእሰ-መምህርነት □

8.3 በትምህርት-እርትእይነት □

8.4 ሌላ ከሆነ ______

መሳ.ፀ2

## ክፍል ሁለት፤

## ስለአራተኛ ክፍል ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት መረጃ፤

9.0 ስለ ትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ

- 9.1 መጠነኛ ግንዛቤ አለኝ ☐
- 9.2 የተሟላ ግንዛቤ አለኝ ☐
- 9.3 ግንዛቤ የለኝም ☐

10.0 የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች ያማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

- 10.1 አላቸው ☐
- 10.2 የላቸውም ☐

11.0 የአራተኛ ክፍል ያማርኛ ቋንቋ መምህራን ቋንቋውን ለማስተማር ተጨማሪ ስልጠና

- 11.1 ተሰጥቷቸዋል ☐
- 11.2 አልተሰጣቸውም ☐

12.0 በክልሉ ውስጥ በስርአተ-ትምህርት ዝግጅት መርሀ ግብር ተሣትፈው ያውቃሉ?

- 12.1 አዎን፣ ተሳትፌያለሁ ☐
- 12.2 የለም፣ አልተሳተፍኩም ☐

13.0 ከትግርኛ ቋንቋ ትምህርት በተጨማሪ ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት በክልሉ መስጠት ምን ያህል ያስፈልጋል?

- 13.1 በጣም ☐
- 13.2 በመጠኑ ☐
- 13.3 አያስፈልግም ☐

14.0 ያካባቢው ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት

- 14.1 ከፍተኛ ነው ☐
- 14.2 መጠነኛ ነው ☐
- 14.3 ዝቅተኛ ነው ☐
- 14.4 አያስፈልግም ☐

15.9 ያካባቢው ወላጆች ልጆቻቸው አማርኛ ቋንቋን እንዲማሩ ያላቸው ፍላጎት

- 15.1 ከፍተኛ ነው ☐
- 15.2 መጠነኛ ነው ☐
- 15.3 ዝቅተኛ ነው ☐
- 15.4 አይፈልጉም ☐

መሳ.02

ከዚህ በታች በዝርዝር የተመላከቱትን አስተያየቶች መሰረት በማድረግ ስለ እያንዳንዱ አስተያየት በሰንጠረዥ ውስጥ ከተቀመጡት ደረጃዎች አንዱን በመምረጥ ደረጃ ይስጡ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5. | በጣም ከፍተኛ | 2. | ዝቅተኛ |
| 4. | ከፍተኛ | 1. | በጣም ዝቅተኛ |
| 3. | መካከለኛ | 0. | አስተያየት መስጠት አልችልም |

| ተራ ቁ. | አስተያየት | ደረጃ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 16 | ከይዘት ገፅታ አንፃር<br>የክፍሉ የቋንቋው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ | | | | | | |
| | 16.1 ይዘቶቹ ከቋንቋው ትምህርት አላማዎች ጋር ይዛመዳሉ | | | | | | |
| | 16.2 ይዘቶቹ ለተማሪዎች ይመጥናሉ | | | | | | |
| | 16.3 ይዘቶቹ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ያሟላሉ | | | | | | |
| | 16.4 ይዘቶቹ ከአካባቢው ሁኔታዎች ይዛመዳሉ | | | | | | |
| | 16.5 ይዘቶቹ ወቅታዊነት አላቸው | | | | | | |
| 17 | የቋንቋው ትምህርት ይዘቶች ቅንብር | | | | | | |
| | 17.1 ይዘቶቹ የማዳመጥ ክሂልን ያዳብራሉ | | | | | | |
| | 17.2 ይዘቶቹ የመማር ክሂልን ያዳብራሉ | | | | | | |
| | 17.3 ይዘቶቹ የማንበብ ክሂልን ያዳብራሉ | | | | | | |
| | 17.4 ይዘቶቹ የመፃፍ ክሂልን ያዳብራሉ | | | | | | |
| 18 | የቋንቋው ትምህርት ይዘቶች አደራረስ | | | | | | |
| | 18.1 ይዘቶቹ ቅደም ተከተላቸውን ይጠበቁ ናቸው | | | | | | |
| | 18.2 ወጥነት አላቸው | | | | | | |
| 19 | ከአቀራረብ ገፅታ አንፃር<br>ቋንቋው ትምህርት መልመጃዎች | | | | | | |
| | 19.1 አይነታቸው የተለያየ ነው | | | | | | |
| | 19.2 በበቂ መጠን ቀርበዋል | | | | | | |
| | 19.3 የደረጃውን ተማሪዎች የሚያመራምሩ ናቸው | | | | | | |
| | 19.4 ተግባራዊ የሚሆኑ ናቸው | | | | | | |
| | 19.5 መመሪያዎቹ ግልፅ ናቸው | | | | | | |

መሳ.፬2

| ተራ ቁ. | አስተያየት | ደረጃ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 20 | የቋንቋው ትምህርት ምሳሌዎች/ስእላዊ መግለጫዎች አቀራረብ | | | | | | |
| | 20.1 ግልፅነት አላቸው | | | | | | |
| | 20.2 ተገቢነት አላቸው | | | | | | |
| | 203 ማራኪ ናቸው | | | | | | |
| 21 | የቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ የህትመት ዝግጅት | | | | | | |
| | 21.1 የፊደሎቹ መጠን ለክፍሉ ተማሪዎች ተገቢ ነው | | | | | | |
| | 21.5 የመፅሀፉ ወረቀት ጥራት አለው | | | | | | |
| | 21.3 መፅሀፉ ከተማሪዎች እድሜ አንፃር ላያያዝ አመቺ ነው | | | | | | |
| | 21.4 አጠራረዙ ጥንካሬ አለው | | | | | | |
| | 21.5 መፅሀፉ ሽፋን፣ ስእል/ ዲዛይን አለው | | | | | | |

## ክፍል ሦስት

## ለአራተኛ ክፍል ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት የይዘት ጥቆማ፤

22. የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን ለምን አላማዎች ይማሩ ?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

23. ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምን ምን ይዘቶች ይቅረቡ ?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

መሳ.02

24. የአራተኛ ክፍል ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተጠናከረና ውጤታማ እንዲሆን ምን መደረግ አለበት ?

________________________________

________________________________

________________________________

________________________________

________________________________

25. ተጨማሪ አስተያየት ካለዎት እባክዎን ከዚህ በታች ሃሣብዎን ይግለጹ።

________________________________

________________________________

________________________________

________________________________

________________________________

# አባሪ ሶስት

ሀ. አማርኛ፣ አራተኛ ክፍል፣ የተማሪው መጽሐፍ ያካተታቸው ይዘቶች፤

- ቃላትን መመስረት
- የቃላት ፍች
- ቃላትን ማንበብ
- አረፍተ-ነገር መመስረት
- አረፍተ-ነገር ማንበብ
- ተመሳሳይ ቃላት
- ጥያቄና አጭር መልስ
- ውይይት
- ንግግር
- ስርአተ-ነጥብ
  . ነጠላ ሰረዝ
  . ድርብ ሰረዝ
  . የጥያቄ ምልክት
  . አራት ነጥብ
- ዘገባ /ሪፖርት/
- ግጥም

ለ. ለቋንቋው ትምህርት በመሳሪያነት የቀረቡ ምንባቦች አርእስት፤

- የቤት እንስሳት
- ደን
- እነ-ሰመረ
- የሰላምታ ልውውጥ
- በተ-ሰብ
- የወንዞች አገልግሎት
- አይጥ
- ታውቁኛላችሁ?
- ቤተ-መፃህፍት
- አርሶ አደር
- ፀሀይ

ምንጭ: አማርኛ፣ 4ኛ ክፍል፣ <u>የተማሪው መጽሐፍ</u>፣ትግራይ ትምህርት ቢሮ፣ 1986

## አባሪ አራት

**In order to fulfil the objectives of education particularly of language learning-teaching policy, the following points have to be considered seriously:**

- proper curirculum development and evaluation
- preparation of appropriate teaching materials
- appropriate man power training.
- teacher's competence
- student's motivation
- language impact and practice
- desired activities in the language

**Untrained teachers or inadequate training lacks the following aspects:**

- good teaching methods
- guide lines on the organization of the contents
- understanding of some of the topics in the syllabus
- communication skills
- mastery of the language
- basic knowledge of grammar
- fluence in the language
- correct pronunciation in the language

These aspects can be divided into two groups.

A. Pedagogic factors B. Linguistic ones

**Related to inadequate preparation of teachers, the followings are the problems of teaching language:**

- lack of textbooks, references, resource materials
- lack of learning attitude and interest on the part of the students
- curriculum is above the students leel
- poor background of the students

These problems can be divided into three aspects

A. Administrative B. Political C. Pedagogic

Source: Rubangumya, C.1990. Language in Education in Africa - pp. 73, 84.

# አባሪ አምስት

## ጥቅሶች በመነሻ ቋንቋቸው

1 Language policies of education are thus a product of the interaction between national objectives as expressed in education objectives, socio-political, history, and the language situation of the country.

/McNab, 1989:7/

2. Language is a system of arbitrary, vocal symbols, which permits all people in a given culture, or other people who have learned the system of that culture, to communicate or to interact.

/Finacchiaro, 1973:3/

3. Language can be akey to meaningful communication among persons or groups, or it can be a barrier to communication. In these days of ethnic pride and growing appreciation of minority groups, educators, govt. officials and missionaries are realizing more than ever.

/Grimes, 1992:vi/

4. - - - - - - the term 'second language' has two meanings. First, it refers to the chronology of language learning. A second language is any language acquired (or to be acquired) later than the native language.

- - - - - - - the second language leearning process takes place at an early age when the native language command is still rudimentary. At the other, it may take place in adult life when $L_1$ acquisition process is virtually completed or slowed down. Or, it may take place at any stage between these two extremes.

/Stem, 1991: 12-13/

5. - - - - -LWC is vital for communities whose primary languages are not widely used outside their own areas. People of such communities need a LWC for purposes such as foreign trade or in order to gain access to scientific, technical and literary materials that do not exist in their own languages.

/Dubin, 1992: 71/

6. - - - - -in a learner - centred system, content should be derived through a process of consultation and negotiation with the learners, the principal consideration being communicative need of the learners.

/Nunan, 1988:55/

7. In addition to consulting the official documentation, it is usually advisable to conduct a survey of:
(a) the overall curriculum (b) the existing textbooks (c) the existing teaching methods (d) teacher training programs, both in-service and pre-paratory and (e) opinions and perceptions expressed by teachers, students and parents.

/Dubin, 1992:11/

8. 'Curriculum' all the learning which is planned and provided for children at school. 'syllabus' is a concise written outline of a course of study.

/UNESCO, 1978:12/

9. - - - - -inorder to motivate the pupils in language, the textbook should describe, situations which socially and intellectually motivate our children to want to use the language in order to learn something, inorder to do something, inorder to be able to express their thoughts, feelings, knowledge and opinions.

/Rubangumya, 1990:66/

10. The quality of education in any given country is reflected in the content of the curriculum resources and the quality of teachers. A curriculum content should therefore reflect the social, political, cultural and economic needs and objectives of that particular community, society or nation. In addition, all curriculum materials must be carefully produced to ascertain their relevance and suitability Vis-a-vis the syllabus.

/UNECA, 1993:27/

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
Addis Ababa, ETHIOPIA

80

ቀን
Date 20/2/89
ቁጥር
Ref.No. ደፕ ተ/ኢ.ቋሥጽ/33/89

<u>አቢሬ ቢዶቢት</u>

በከሰለ አንዱ መስተዳድር
የደቡብ ዞን /ቀጫና/ት/ቢሮ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል የድኅረ-ምረቃ ተማሪ (Graduate Student) የሆነው አቶ ጥላሁን ገብረ ክርስቶስ በክፍል ውስጥ ለሚያቀርበው ሰሚናርና ለመመረቂያ የሚያበቃውን ጽሑፍ ለማዘጋጀት በዞናችሁ ጥናት የሚያካሂድ መሆኑን ገልጸ ትብብር እንዲደረግለት ደብዳቤ እንድንጽፍለት የትምህርት ክፍሉን ጠይቋል ::

አቶ ጥላሁን የድኅረ-ምረቃ ተማሪያችን መሆኑን እየገለጽን ለጥናቱ የሚረዳውን ሁሉ ትብብር ይደረግለት ዘንድ በትህትና እንጠይቃለን ::

ከሰላምታ ጋር

ይልማ ከበደ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል
ሊቀመንበር

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ADDIS ABABA UNIVERSITY
DEPARTMENT OF ETHIOPIAN LANGUAGE AND LITERATURE

ቍፅ ጽ/ህ/1089/60/55
ዕለት 02/03/89

ናብ ስንቆጦኒ ወረዳ ክፍሊ ትምህርቲ

ማይጨው፤

ቀ ኒ ኑ፦ ኪዴተ ተሰሁን ገ/ክርስቶስ ይተምት፤

ልዕሊ ክብሊ ሽሞም ዝተጠቕሰ ኣብ ኣዲስ ኣበባ ዩኒቨርሲቲ ናይ ኢትዮጵያ ቛንቋታት ስነ-ፅሑፍ ክፍሊ ዲግሪ ምረቓ ትምሃሮ ንዘቕረቦ ናይ በጽር ፅሑፎም ኣብ ወረዳኹም ኣብ ዝርከብ ኣብያተ ትምህርቲ ናይ ስምሪትና ቛንቋ ትምህርቲ ብዝ ጠመተ 48 ክፍሊ መምህራን ከምኡውን ናይ ቤት ትምህርቲ'ር መምህራንን ናይ ወረዳ ክፍሊ ትምህርቲ ትምህርት ፕሮግራም ወይ ሱፐርቫይዘርን ስለ ሙያ ዝምልከት ቅጥዒን ናይ ቃል መጠይቕ ስለዘቕረቡ ኣድላዪ ምትሕብባር ክገብረሎም ነተሓባበብ፡፡×=×=

= ምስ ሰላምታ =

ደሰታ ከበሬ

ትም/ቲ ፕሮ/ማ ክፍሊ

ሐሰሬ

ቅ ዳ ሐ//

ኪዴተ ተሰሁን ገ/ክርስቶስ

ኣብ ዘለውዮ፤

ኪ/ተ

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

ቴሌ Tele. 55 08 44 | ፖስታ P.O.B 1176 | ቴሌክስ Telex. 21205 | ቴሌግራም Cable AAUNIV

82

ቀን Date ጥር 30,1989

ቁጥር Ref.No. ኢቋ ተ/ኢቋሥጽ/105/89

በትግራይ ክልል

ለ ________ ዞባ ትምህርት ቢሮ

የክፍላችን የድኅረ ምረቃ ተማሪ ጥላሁን ገ/ክርስቶስ ‹‹ትግርኛ የአፍ መፍቻቸው ለሆነ ተማሪዎች ከትምህርትና ስለጠና ፖሊሲው አንፃር ያገደና አርከን በመጀመሪያው ንኡስ አርከን |፬ና ክፍል| ምርና ቋንቋ ትምህርት የሚያካትታቸው ይዘቶች ጥናት›› በሚል ርዕስ የመመረቂያ ጽሑፍ /ጥናት/ ለማካሄድ የሚረዳውን መረጃ ለመሰብሰብ ይችል ዘንድ ትብብር እንድታደርጉለት እየጠየቅን ለሚደረግለት ትብብር በቅድሚያ እናመሰግናለን ::

ከሰላምታ ጋር

ይለጸ ከ[illegible]
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል ሊቀመንበር

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
DEPARTMENT OF ETH[illegible] LANGUAGES AND LITERATURE
ADDIS ABABA UNIVERSITY

ቁፅሪ :........................................

ዕለት :....19/06/89....



● ናብ ማርያም ሸዊቶ ገ፬ ብርኪ ቤት ትምህርቲ

<u>ዓድዋ፤</u>

**ምህንፃ መትሕብባር ምልክት፤**

ኣብ ላዕሊ ብኣርእስቲ ከምዝተጠቕሰ ኣይተ ተላሁን ገብረክርስቶስ ዝተባህሉ ካብ ኣዲስ ኣበባ ቤትምህርቲ ጸሀረ መረዳ ብዘዐበ ናይ ተማሃራይ ሳይክል 4ይ ክዝ ክፍሊ ኣመሓድርና ዕንገት ንመከዳዲ ስለዝጸለዩ ኣብ ኣብያተ ትምህርቲ ከይደም ወገናት ንመከዳጺ ትሕብብር ንክንገብረሎም ካብ ኣዲስ ኣበባ ቤትምህርቲ ብዕለት 30/05/89 ብቑፅሪ ተዋ/ኣተምድ/105/89 ዝተፃሕፈ ደብዳቤ በፂሑና፡፡

ስለዝኾነ ስሞም ኣብ ላዕሊ ዝተጠቕሱ ናይ ጸሀረ መረዳ ትምህርቲ ኣብቲ ዝበልዎ ክፍሊ መፅሓፍን ዕንገት ንክገብሩ ትሕብብርኩም ንክህቡ ንሓብር፡፡

ዝበለ ብ18/6/89 ብቑፅሪ ማዝ2/1–2070/23/35 ዝተፃሕፈ ደብዳቤ ካብ ማ/ዘበ ትምህርቲ ተጻሒፉልና ፡፡

ስለዚ ዘድሊ መትሕብባር ክትገብሩሎም ንሓብር፡፡ ────────────

● ምስ ሰላምታ ●

ገብሩ በርሀ

ሰራሕ መከየዲ

<u>ቅዳሕ፤</u>

● – ኣይተ ተላሁን ገብረክርስቶስ

<u>ዓድዋ፤</u>

ዓዲግራት፣

ቍጽሪ [illegible]/3-904/4/3935

ዕለት 14-6-89

• ናብ ኣርብ ወረዳ ክ/ትም/ቲ

ኣሊተና፣

• ናብ ጋ/ኣፈሽም ወረዳ ክ/ትም/ቲ

ዓዲግራት፣

• ናብ ሳ/ፁዕዳ እምባ ወረዳ ክ/ትም/ቲ

ፍረወይኒ፣

ዋኒኑ፣ ተሕብበር ይጥዖት ፣

ኣብ ኣዲስ ኣበባ ዩኒቨርስቲ ናይ ድህረ ምረቓ ተምሃራይ ዝኾነ ኣይተ ጥላሁን ገ/ክርስቶስ "ትግርኛ የአፍ መፍቻቸው የሆኑ ተማሪዎች ከትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው አንፃር ያገደናው እርከን በመጀመሪያው ገለጣ እርከን ሄዳናው ክፍለ ምሕርና ቋንቋ ትምህርት የሚያስከትሏቸው ይዘቶች ጥናት" ብዝብል ርእሲ ናይ መመረቒ ፅሑፍ/ፅንዓት/ ንምክያድ ዝሕግዞም መረዳእታታት ንምእካብ ክከኣሉ ተሕብብር ንክንገብረሎም ናይ ኣዲስ ኣበባ ዩኒቨርስቲ ዕለት 30/1989 ዓ.ም ብቑ. ፅሕ ተ/ኢያሙጸ/108/89 ፅሒፉ ኣተሓሳሲቡና ኣሎ፡

ስለዚ ኣብ ወረዳኹም ወፃእ ብዛዕባ ዝገብሩዎ ትም/ቲዊ ምርምር ፅንዓቶም ብዝኸኣለ መጠን ገበኦ ሓገዝን ምትሕብባርን ክትገብሩሎም ንሓብር፡፡x=x=x=x=x=x=x=x=x=

ምስ ሰላምታ

ተኸስተ ሓጎስ ሃይሉ

ምም/ሓዩድገስ ገልጋሎት

ሓላፊ

ቅዳሕ/

• ንዞባና ወም/ቢ ሓላፊ

• ንዞባና ትም/ቲ ፕሮግራማት ዋና ክፍሊ

• ንኣይተ ጥላሁን ገ/ክርስቶስ

ዓዲግራት፣

ቁጥር ... 104/1607/150/35
ቀን ... 21-6-89

● ለህንፀት 1ኛ ደረጃ ት/ቤት
መ ቀ ለ ፤

ጉዳዩ ፡- አቶ ተሳሁን ገ/ቂርቆስ የደህረ ወረቃ ተማሪ
ን ይመለከታል፤

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋ ደህረ ወረቃ ተማሪ የሆኑት አቶ ተሳሁን ገ/ቂርቆስ በዞናችን በሚገኙ ት/ቤቶች ትግርኛ የአፍ መፍቻቸው ለሆነ ተማሪዎች ከትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው አንፃር ፡ የመመረቂያ ፅሁፍ ለማዘጋጀት ጥናት ለማድረግ እንዲችሉ እንድንተባበራቸው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቁጥር ድተ/ሊቋሥድ/106/89 በቀር 30,1989 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ገልፀልናል፡፡

ተማሪው በህንፀት ት/ቤት ላይ ጥናቱን ማከናወን እንደሚፈልጉ የገለፁ በመሆኑ ለጥናታቸው አስፈላጊ የሆኑት መረጃዎችም ሆነ መፃሕፍት በመስጠት እን ትተባበሩዋቸው እያሳሰብን ይህንን ደብዳቤ ለባለ ጉዳዩ በገልባጭ እንዲደርሳቸው ዘገበናል፡፡=x=x=x=x=x=x=x=x=x=x=x=x=x=x=x=x=

● ከሰላምታ ጋር ●

ደስታ ገብረሕይወት ምራጭ
DESTA GEBREHIWET MIRACH
ዋምርሒ ትምህርቲ
ሓላፊ

ገልባጭ፤
ለአቶ ተሳሁን ገ/ቂርቆስ የአ.አበባ ደህረ ወረቃ ተማሪ.
መ ቀ ሌ ፤

አበ.ገ.

ጀዘ1/5052/57/35

ቍጽሪ......

ዕለት..................

• ናብ ወረዳ፡ኣ ንዓ..ን ቤት ትምህርቲ
<u>ዓዲጉደም</u>

• ናብ ወረዳ ራያ ዓዘቦ ቤት ትምህርቲ
<u>መ ኾ ኒ</u>

ናይ ካዝ ኣበባ ቀዝኪስቲ ናይ ደረ ምረጃ ተምሃሪ የሰሁን ገ ሰርስጠ ደንደ ክንሬና ናይ ካፍ መሸረቱም ዘሎ ናይ 1ይ ብደብል ብካንጁሬ ኣቲ ፊዓሽ ትምህርቲ ፖሊሲ መሰረት ከም ኡ'ውን ናይ ካምፏሮ 4ይ ብፍሉ ሪገዓት ንክዘይቀ ናብሎ ይመጹ ብስዘለዎ ኣዩ ክብቤሎ ዜሬበብ 1ይ ብሬኪ ብካቢ ቀረቢዎ ኣቲ ሪገዓት ክዘይቀ ኢዩ። ምስ ከምስክሮ ናይ ወረዳ ብፍሉ ትምህርቲ'ውን ክዛፊ ረቡ ኢዩ ዘይብሉ ምትሕብባር ይገብረልና።።xxxxxxxxxxxxxxxx

• ምስ ሰላምታ •

ዘስ ፍ ሃ ጦርዮም
ሓላፊ መምርሒ ት/ቲ ዞባ
ደቡብ

ቅ ዳ ለ//

• ንደንጎል 1ይ ብሬኪ ቤት ት/ቲ
<u>መ ኾ ኒ</u>

• ንቀብረ ደረጃ 1ይ ብርኪ ቤት ት/
<u>መ ኾ ኒ</u>

• ንተምሃሪ የሰሁን ገ ሰርስጠ
<u>ኣ/ዘለዎት</u>

ክ/ተ

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የግል ስራዩ መሆኑን፣ በጥናቱ ውስጥ የተመላከቱትን መረጃ ፅሁፎች፣ምንጮችና ከመስክ የተገኙ መረጃዎችን ባግባቡ የተጠቀምኩ መሆኔን በፊርማዩ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፣ ጥላሁን ገ/ክርስቶስ

ፊርማ፣

ቦታ፣ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ቀን፣ 27-04-90